# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አፈፃፀም በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ግንቦት 2016 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# ማውጫ


የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ ....... i

ክፍል አንድ ....... 1

መግቢያ ....... 1

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አመሠራረት ....... 1

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ ....... 2

ራዕይ (Vision) ....... 2

ተልዕኮ (Mission) ....... 2

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር ....... 2

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት ....... 4

የሰው ኃይል ....... 4

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ....... 5

የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ....... 6

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ....... 6

የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ....... 6

የኦዲት ወሰንና ዘዴ ....... 7

የኦዲቱ ወሰን ....... 7

የኦዲቱ ዘዴ ....... 7

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አሰራር ስርዓት መግለጫ /Process description/ ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡ ....... 8

ክፍል ሁለት ....... 9

ግኝቶች ....... 9

ሀ/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን ለመቆጣጠር ሥርዓቶች መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤ ....... 9

የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን ለማሳለጥ የህግ ማእቀፎች መዘጋጀቱን በተመለከተ ....... 9

የመሰረታዊ ሸቀጦች እና የሲሚንቶ የስርጭት ስርአት መዘርጋቱ በተመለከተ፡ ....... 11

የመሰረታዊ ሸቀጦችን በተመለከተ፡- ....... 12

የሲሚንቶ ምርት በተመለከተ፡- ....... 14

የመሰረታዊ ሸቀጦችን አስመጪዎች/ አቅራቢ ድርጅቶች አመራረጥ ሂደት በተመለከተ ....... 16

በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች የሥርጭት ሂደትን በተመለከተ፤ ....... 18

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን አቅርቦትና ስርጭትን ለመደገፍና ከአምራቾችና ከአቅራቢዎች ጋር መስራቱን በተመለከተ ........ 24

የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡ ........ 25

*ለ/ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት፣ ክፍፍል፣ አቅርቦት ለማከናወን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን መገምገም፤* ........ 27

የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ከከተማ አስተዳደሮች እና ከክልሎች ጋር የጋራ እቅድ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤ ........ 27

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከግብረ ኃይል ኮሚቴው ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፡........ 30

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችን በጥናት መለየቱን በተመለከተ........ 34

መሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦትና ሥርጭት ላይ የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ፡ ........ 37

የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አምራች ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ለማምረት የሚያስችል ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ........ 42

*ሐ/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭት፣ ክፍፍልና አቅርቦትን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማደረጉን መገምገም፤* ........ 46

የሲሚንቶ እና የዘይት ፋብሪካዎች የመሸጫ ዋጋ ቁጥጥርና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤........ 46

የመሰረታዊ ሸቀጦችና የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች በሚያቀርቡት ምርት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤........ 50

የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ከተቀመጠው የስርጭት ስርዓት ውጭ በሚሰሩ ተቋማት ላይ እርምጃዎችን መውሰዱን በተመለከተ፤........ 52

በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ለሚሰሩ የንግድ ዘርፍ እና የሸማቾች ማህበራት የግንዛቤ፣ የትምህርትና የስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፤........ 54

መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ኮታ ወቅታዊ ማድረጉና ማሰራጨቱን በተመለከተ፤........ 56

የመሰረታዊ ሸቀጦችና የሲሚንቶ ስርጭት ሴቶችን እና ድጋፍ የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረጉን በተመለከተ፡ ........ 57

**ክፍል ሶስት** ........ 60

***መደምደሚያ*** ........ 60

**ክፍል አራት** ........ 65

***የማሻሻያ ሃሣቦች*** ........ 65

**አባሪ 1፡- *የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች*** (Audit Evaluative Criteria) ........ i

**አባሪ.2 *የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር*** ........ xi

**አባሪ፡-3. *የሲሚንቶ ምርት እጥረት መኖሩና ተቋማት ሲጠይቁ የሚሰጣቸው አንሰተኛ መጠን ለማሳያነት፡-*** ........ xii

አባሪ፡-4 ጥራት የሌለው የስኳር ምርት ለማሳያነት፡-........................................................................xiv

# የክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ

1. በሀገራችን የግንባታ ዘርፍ ማደግን ተከትሎ የሲሚንቶ ምርት በተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ከፍ ያለ ልዩነት እየሰፋ የዋጋ ንረቱ እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ሲሚንቶን በቀጥታ ከፋብሪካው የመግዛት እድል ያገኙ አካላትና ተጠቃሚዎች በዋጋም ሆነ በአቅርቦት ተጠቃሚ መሆን የቻሉ ቢሆንም በተመረጡ አቅራቢዎች ህብረተሰቡ እንዲዳረስ የተደረገው የሲሚንቶ ሥርጭት የተጠቃሚውን ፍላጎት ያላሟላ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ህገወጥ አሠራሮች የተጋለጠ ሆኗል፡፡ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር በመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 19 (4) መሠረት መመሪያዎች እያወጣ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡
2. ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከመሰረታዊ የንግድ እቃዎች መሀከል ለህብረተሰቡ ለምግብ ፍጆታ ከሚውሉት ሸቀጦች ስኳር፣ የፓልም የምግብ ዘይት፣ ስንዴና የስንዴ ዱቄት ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እየታየባቸው እና ይህም ክስተት በህብረተሰቡ የዕለት ዕለት ኑሮ ላይ አሉታዊ የኑሮ ውድነት ተፅእኖ ያስከተሉ መሆናቸውን በጥናት በመለየት ግብይታቸውና ስርጭታቸው ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ የታመነበት በመሆኑ መንግስት ገበያውን ለማረጋጋት ወጥነት ያለው አፈፃፀም፣ ክትትል፣ ድጋፍ አሰጣጥና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ በ2008 እና በ2011 ዓ.ም የመሰረታዊ ሸቀጦች መመሪያዎች አውጥቶ ተግባራዊ አድርጓል፡፡
3. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን አፈፃፀም ውጤታማ መሆኑን ለመገምገም ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የአሰራር ክፍተቶችን መንስኤያቸውን በመለየት ችግሮቹን ለመቅረፍ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠትና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡
4. ከላይ ለተገለፀው የክዋኔ ኦዲቱ አላማ ለመገምገም የሚያስችሉ ሶስት ለክዋኔ ኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተዘጋጁ ሲሆን እነሱም፡-
    - በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤
    - የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት፣ ክፍፍል፣ አቅርቦት ለማከናወን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን መገምገም፤

- ሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭት፣ ክፍፍልና አቅርቦትን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማደረጉን መገምገም፤ የሚሉት ናቸው፡፡

5. የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Supreme Audit Institutions (ISSAI) እና በመንግስት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በተሰጠው አዋጅ ቁጥር 982/2008 መሠረት ነው፡፡ዝርዝር የክዋኔ ኦዲቱ ወሰን በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከ2013-2016 በጀት ዓመት የሩብ ዓመት ድረስ ያለውን የሥራ ክንውኖች መሰረት በማድረግ ሲሆን ለኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎች በማሰባሰብ፣ በመተንተን እና የተለያዩ የኦዲት ዘዴዎችን በመከተል ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

በኦዲቱ ወቅት የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን አፈፃፀም ውጤታማ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ክፍተቶች ታይተዋል፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ለማሳለጥና ተግባራዊ ለማድረግ በተለይ በፍራንኮቫሎታ (የራሳቸው የውጪ ምንዛሬ ያላቸው ዲያስፖራዎች) ሸቀጦችን ወደሃገር እንዲያስገቡ ፈቃድ በተሰጣቸው አስመጪዎች የሚመጡ ሸቀጦች የስርጭት፣ የግብይትና የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋላቸው መሆኑ እና ምርቶቹ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የስርጭትና የግብይት ሰንሰለቱ የማይታወቅና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑ፤ እንዲሁም የሲሚንቶ መመሪያዎች በግብይቱ ሂደት ላይ ክፍተትን በሚፈታ መልኩ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ሀገራዊ ጥናት በማካሄድ ሁሉም አካታች በሆነ መልኩ የማይዘጋጁ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች፣ አምራቾችና አከፋፋዮች/ ቸርቻሪዎችን እና የሲሚንቶ አምራቶች አሁን ካለው የምርት ከፍተኛ የአቅርቦት እጥረት፣ መቆራረጥና ፍላጎት አንፃር ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ የማይጣጣም መሆኑ፤ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች እና የሲሚንቶ አምራቶች የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ ስርጭት እና በተዘረጋው ሰንሰለት መሰረት ምርቱን እየቀረበ አለመሆኑ እንዲሁም የሲሚንቶ ምርትም በየጊዜው አፈጻጸሙን እየተቆጣጠረ አለመሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ 2001 ዓ.ም የተደለደለ ሲሆን ይህ የኮታ ድልድል ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ ክለሳ ያልተደረገበት መሆኑ፤ ሆኖም በዚሁ የኮታ ድልድል መሰረት እየተከናወነ አለመሆኑ፤ የሲሚንቶ የኮታ መነሻ በግልፅ የተቀመጠ ሁኔታ እንደሌለ

እና ክልሎችና ከተማ አስተዳደር መሰረታዊ ሸቀጦች ምርቶቹ ካለመኖራቸው የተነሳ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅድ እና የአቅርቦት ጥያቄ ምላሽ የተሰጣቸው አለመሆኑ፡

- የኢትዮጵያ እህል ንግድ ኮርፖሬሽን ከ2007 እስከ 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ በአማካይ መጠኑ ከ400,000 እስከ 600,000 ቶን ስንዴ ከውጭ እያስገባ የገበያ ጉድለቱን ሲሞላ የቆየ ቢሆንም ከ2012/2013 ዓ.ም ጀምሮ የአሰራር ሥርዓቱ የተቀየረ መሆኑና ቀደም ሲል ትስስር ተፈጥሮላቸው ዱቄትና የዱቄት ውጤቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ሲያቀርቡ የነበሩ ፋብሪካዎች ትስስር የተቋረጠ በመሆኑ ፋብሪካዎቹ ስራ በማቆም ላይ መሆናቸው፤ በአዲሱ የገበያ ትስስር በሀገር ውስጥ የስንዴ ምርት ትስስሩ እንዲቀጥል በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም መልስ ያልተሰጣቸው መሆኑ፤
- የሲሚንቶ ምርት ኮታ በአምራቾች ፍላጎት እየተወሰነ መሆኑ፤ አከፋፋዮች ምርቱን በሚፈልጉት ወቅት ሳይሆን አምራቹ በሚፈልገው ጊዜ በአነስተኛ መጠንም እንዲወስዱ የሚያዟቸው መሆኑ እና አከፋፋዮች ሁሉም በሚባል ደረጃ አዲስ አበባ እየመጡ የሚሸጡ መሆኑ፤ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች በህገ-ወጥ ከደላላ እየተረከቡ ያለደረሰኝ የሚሸጡ መሆኑ፣ በፋብሪካዎች አካባቢ ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር መኖሩ እና የሲሚንቶ የሰርጭት ክፍተቶች መፍትሄ እያገኙ አለመሆኑ፤
- የተጠቃሚውን ፍላጎት በማጥናት ፍላጎት መሰረት ያደረገ ዓመታዊ እቅድ በማዘጋጀት እና የአምራቾችንና የአቅራቢዎች እቅድ በእቅዱ የሚያካትትበት እና ምርቶቹ ባለቁ ጊዜ እንዲተኩ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤ለማሳያ፡
    - ❖ የስኳር ምርት ክምችት እያለቀ በመሆኑ እንዲተካና ከውጭ ግዥ እንዲካሄድ የስኳር ግሩፕ ኢንዱስትሪ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደጋጋሚ እያሳወቀ የነበረ ቢሆንም ለ2013 ዓ.ም 200,000 ሺህ ቶን ግዥ እንዲፈፀም ታቅዶ 100,000 ሺህ ቶኑ ብቻ ግዥ የተፈፀመ እና በ2014 ዓ.ም የተሰራጨ መሆኑ፤ በ2014 ዓ.ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአነስተኛ መጠን የምርቱ ፍላጎት ለሟሟላት 300,000 ሺህ ቶን ከውጭ እንዲገዛ ታቅዶ እስከ 2016 ሁለተኛው ሩብ ዓመት ያልተከናወነ መሆኑ፤
- የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት ቢኖርም ምርቶቹ ቀጣይነትና ወጥነት ባለው መልኩ በገበያው እየተገኙ አለመሆኑ፣ ህብረተሰቡ የሚገዛበት አቅምና ዋጋ አቅርቦትና ፍላጎት ከፍተኛ አለመጣጣም መኖሩ፤ መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትና ግብይት በመንግስት ድጋፍ የሚቀርቡት እና የግል

አቅራቢዮች የሚሰጡት ዋጋ ልዩነት ባለመኖሩ እንዲሁም አልፎ አልፎም ከገበያ ዋጋ በላይ ስለሚሆን የህብረተሰቡ የቅሬታ ምንጭ መሆኑ፤

- ስንዴ ከመሰረታዊ ሸቀጥነት ስለመውጣቱ ወይም በመሰረታዊ ሸቀጥነት ስለመቀጠሉ ካለው ወቅታዊ የምርት ፍላጎት አኳያ ሙያዊ ጥናት ሳይጠና እና ከመሰረታዊ ሸቀጥነት መውጣቱ ይፋ ሳይደረግ ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች የሚቀርበው አቅርቦት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ መሆኑና የስንዴ ምርት ከፍተኛ ፍላጎትና አቅርቦት እጥረት መኖሩ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅርቦት ክፍተቱ በጥናት ለይቶ ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል የመፍትሄ ሃሳቦች ለሚኒስትሮች ም/ቤት ያላቀረበ መሆኑ፤
- ስንዴ ከመሰረታዊ ሸቀጥነት መውጣት እና በነፃ ገበያ መገበያየት ቢኖርበት እንኳን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ይህን የመሸከም አቅም ስለመኖሩ፣ አቅም የሌላቸውን ለመደገፍ የሚያስችል ቅድመ ዝግጅት እና ችግራቸውን ለመቅረፍ የሚያስችል ዕቅድ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያላቀረበ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦች በልዩ ሁኔታ ጊዜውንና በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱን ለሕብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ድጋፍ እንዲያገኙ እና ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ከአስፈጻሚ አካላት (ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ብሄራዊ ባንክ፣ ንግድ ባንክ፣ ገቢዎች ሚ/ር፣ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወዘተ የቅንጅት ስራው የተጠናከረ አለመሆኑ፤ በተለይ ድፍድፍ ዘይት ምርቱን ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ ከተፈቀደላቸው በኃላ አፈፃፀሙን ክትትል የማያደርግ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አምራች ተቋማት በሙሉ አቅማቸው ማምረት እንዲችሉ እና ችግር የሚፈቱ አማራጮች እንዲኖሩ እና ውጤታማ የገበያ ትስስርና ሰንሰለት እንዲኖር በቂ ድጋፍ ያላደረገ መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
    - የዘይት፣ የስኳር፣ ዱቄትና የዳቦ እንዲሁም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የውጪ ምንዛሬ እና ብድር የማያገኙ መሆኑ፤ ለፋብሪካዎች ግብዓትነት የሚውሉ የአረምና የማሽነሪ ኬሚካል (የስኳር)፣ ስንዴ ለድቄትና ዳቦ ፋብሪካዎች፣ ድንጋይ ከሰል (ለሲሚንቶ)፣ የቅባት እህሎች (የዘይት)እንዲሁም ለሁሉም ፋብሪካዎች ማሽነሪዎች፣ ብቁ ባለሞያዎች (የጥገና፣ መለዋወጫ ወዘተ) ድጋፎች ያለማግኘት፤ የፀጥታ ችግር በመኖሩ በተለይ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች 24 ሰዓታት ያመርቱ የነበሩ እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ብቻ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች መኖራቸው፤

- የሲሚንቶ የተዘረጋው የገበያ ትስስር ሰንሰለት ውጤታማ አለመሆኑ፤ ምርቶቹ በህገወጥ ደላሎች ከፋብሪካ በር ጀምሮ የሚያሰራጩ መሆኑን እንዲሁም አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች በተዘረጋው ሰንሰለት ምርቱ እየወሰዱ አለመሆኑን አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በመጋቢት 20/2015 ሲሚንቶ ከፋብሪካዎች (ዳንጎቴና ሙገር የሲሚንቶ ፋብሪካዎች) አከፋፋዮች ላይ ባደረገው ቁጥጥር ያረጋገጠ መሆኑ፤
- የሲሚንቶ በየስድስት ወሩ እና የድፍድፍ ዘይት በየሶስት ወሩ የሚተመነው የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ከላይ ለተጠቀሱት ግኝቶች መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ተሰጥተዋል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ለማሳለጥና ተግባራዊ ለማድረግ በተለይ የፍራንኮቫሉታ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ሸቀጦችና ምርቶች ወደ ስርዓት የሚያስገባ የስርጭትና የግብይት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እና ምርቶቹ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የስርጭትና የግብይት ሰንሰለቱ አስቀድሞ በታወቀ የግብይት ሥርዓት እንዲከናወን ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የሲሚንቶ መመሪያዎች በግብይቱ ሂደት ላይ ክፍተትን በሚፈታ መልኩ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ ሀገራዊ ጥናት በማካሄድ መመሪያዎች ማዘጋጀት እና ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች፣ አምራቶችና አከፋፋዮች/ቸርቻሪዎችን እና የሲሚንቶ አምራቶች አሁን ካለው የምርት ከፍተኛ የአቅርቦት እጥረት፣ መቆራረጥና ፍላጎት አንፃር ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ እንዲጣጣም ማድረግ፤ የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ ስርጭት እንዲካሄድ እና በተዘረጋው ሰንሰለት መሰረት ምርቱን መቅረቡን በየጊዜው አፈጻጸሙን መቆጣጠር ይኖርበታል፤፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ 2001 ዓ.ም የተደለደለው ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሆን ክለሳ ማድረግ፤ በኮታው መሰረት ስርጭቱ እንዲከናወን ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ እህል ንግድ ኮርፖሬሽን ስንዴ ከውጭ እያስገባ የገበያ ጉድለቱን ሲሞላ የነበረው ከ2012/2013 ዓ.ም ጀምሮ ትስስር ተፈጥሮላቸው ዱቄትና ዳቦ በተመጣጣኝ ዋጋ ሲያቀርቡ የነበሩ ፋብሪካዎች

አሁን በተዘረጋው ትስስር ምርቱን ከሃገር ውሰጥ የስንዴ ምርት የሚያገኙበት፤ ሰንሰለቱም ለአምራቹ/ለአቅራቢው እና ምርቱ በግብአትነት ለሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ምቹ፣ ግልፅና የሚያበረታታ እንዲሆን፤ እንዲሁም ለተጠቃሚው ህብረተሰብ በሚፈልገው መጠን፣ ወቅት እና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያገኝበት ትስስር ሊፈጥር ይገባል፡፡

- የዘይት ምርትን አቅርቦትና ፍላጎትን በተጣጣመ መልኩ እንዲቀርብ ሃገራዊ ኢንዱስትሪዎችን በማሳደግ እና ቀጣይነት /ዘላቂ የምርት አቅርቦት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡
- የሲሚንቶ ምርት አከፋፋዮች ምርቱን በሚፈልጉት ወቅት እና መጠን የሚያገኙበት በኮታ አወሳሰን መመሪያ እና ተጠቃሚውን መሰረት ያደረገ ኮታ በሚመለከተው አካል እንዲወሰን ሊያደርግ፤ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች እጥረት እንዳይገጥም አከፋፋዮች ንግድ ፈቃዳቸው ባወጡበት /አከባቢያቸው የሚያከፋፍሉበት፣ አከፋፋዮችና ቸሪቻሪዎች በተዘረጋው ሰንሰለት ምርቱ የሚያገኙበት እና በደረሰኝ ብቻ ግብይት እንዲኖር የተጠናከረ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እና በፋብሪካዎች አካባቢ ያለው ከፍተኛ የአቅርቦት ለችግሩ መፍትሄ የሚያገኝበት መንገድ መፍጠር ይኖርበታል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦች በልዩ ሁኔታ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ጊዜውን ጠብቀው ምርቱን ለህብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ድጋፍ እንዲያገኙና ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ከአስፈጻሚ አካላት (ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ብሄራዊ ባንክ፣ ንግድ ባንክ፣ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወዘተ የቅንጅት ስራው ሊያጠናክር ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አምራች ተቋማት በሙሉ አቅማቸው ማምረት እንዲችሉ እና ችግር የሚፈቱ አማራጮች እንዲኖሩ እና ውጤታማ የገበያ ትስስርና ሰንሰለት እንዲኖር፣ የውጪ ምንዛሬ እና ብድር፣ ለፋብሪካዎች ግብዓትነት የሚውሉ ግብአቶች፣ ማሽነሪዎች፣ ብቁ ባለሞያዎች (የጥገና፣ መለዋወጫ ወዘተ) እንዲያገኙ ማመቻቸትና መደገፍ ይገባል፡፡
- የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት ቢኖርም ምርቶቹ ቀጣይነትና ወጥነት ባለው መልኩ በገበያው እንዲገኙ፣ ህብረተሰቡ የሚገዛበት አቅምና ዋጋ ያገናዘበ እንዲሆን እና የስንዴ ከፍተኛ ፍላጎት እና ዋጋ

ውድነት ክፍተቱ ለመሙላት የሚያስችል ጥናት ተከናውኖ ለሚንስትሮች ምክር ቤት ለውሳኔ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

- የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች በየስድስት ወሩ እና በየሶስት ወሩ የሚተመነው የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ በየወቅቱ ሊከለስ ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

### የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አመሠራረት

1. የሃገሪቷን የንግዱ ዘርፍና የኢንዱስትሪውን ዘርፍ አስተባብሮ ለመምራት የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ሚኒስቴር በመባል ይታወቅ የነበረው መሥሪያ ቤት የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስቴር እና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር በመባል ተከፋፍሎ የነበረ መሆኑና በ1983 ዓ.ም ደግሞ እንደገና የንግድ ሚኒስቴር በሚል ስያሜ እንዲዋሃዱ ተደርጓል፡፡
2. በ1987 ዓ.ም ደግሞ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በአዋጅ ቁጥር 4/1987 በመዋሃድ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በመባል እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ይህ መ/ቤት በ1994 ዓ.ም 10 ተጠሪ መሥሪያ ቤቶችን በሥሩ ይዞ እንዲያስተባብርና እንዲመራ በአዋጅ ቁጥር 256/1994 በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ነበር፡፡ ሆኖም እንደገና በአዋጅ ቁጥር 411/1996 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሥሩ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለሥልጣን፣ የፌዴራል የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ኤጀንሲና የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትን ተቆጣጣሪ ሆኖ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡
3. የፌዴራል አስፈፃሚ አካላት አደረጃጀትን፣ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሰረት የንግድ ሚኒስቴር እንደገና ተቋቁሟል፡፡ በ2010 ዓ.ም ደግሞ እንደገና በአዋጅ ቁጥር 1097/2010 የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተቋቋመ ሲሆን የንግድ ዘርፉ የሀገሪቱን ራዕይ ከማሳካት አኳያ የንግድ ዘርፉን የልማት ሠራዊት በማጠናከር የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም የመገንባት፣ ዘመናዊ የንግድ መረጃ ሥርዓት የመዘርጋት፣ ሃገሪቱ የአለም ንግድ ሥርዓቱ አካል የማድረግ እና የገበያ ማስፋፋትና ትስስር ሥራዎችን በማጠናከር የአገሪቱን የውጪ ምንዛሪ ግኝት የማሳደግ፣ በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥርዓት የማስፈን ሥራዎች የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫዎች እንዲተገበሩ በ2014 ዓ.ም. ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሆኖ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት ከቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተለይቶ ከቀድሞ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለስልጣን እና ከንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በመዋሃድ እራሱን ችሎ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

4. ለሚኒስቴር መ/ቤቶች የተሰጡ የወል ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው የውጪ እና የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና እንዲዘምን፣ ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን፣ የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ለመቆጣጠር፣ የኢንስፔክሽን አሠራሮችንን ለማጠናከር የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት የመዘርጋትና የማዘመን፣ የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ የማጥናት፣ የአገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን የማስተባበር፤ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን የመቆጣጠር እና ከንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን እና ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን በአዋጅ የተሰጡትን ተግባራት በመስራት በንግድ አሰራሩ ላይ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን በማስተካከል ተገልጋዮችን ለማርካት በትኩረት እየሰራ ይገኛል።

## የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ራዕይ እና ተልዕኮ

**ራዕይ** (Vision)

5. በ2022 ዓ.ም የንግድ ዘርፍ በአፍሪካ ደረጃ ዘመናዊና ተወዳዳሪ ሆኖ ማየት፤

**ተልዕኮ** (Mission)

6. የንግድ አሰራርን በማዘመን፤ ግልፅ፣ ተደራሽና ፍትሀዊ ውድድር የሰፈነበት እንዲሆን በማድረግ፤ ቀጣናዊ ትስስርን በማጠናከር፤ የወጭ ንግድን በማስፋፋትና በማሳደግ፤ የዕቃዎችን የጥራት ደረጃ በማዘጋጀትና በመቆጣጠር የሸማቹን፣ የንግዱን ማህበረሰብ እና የሀገርን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የንግድ ስርአት መገንባት፤

## የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ስልጣንና ተግባር

7. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም፡-

- ❖ የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድን የሚመለከቱ ቀጠናዊ በተለይም ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖር የንግድና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን በቀጣይነት የሚያረጋግጡ፣ ሀገራዊ የጥራት መሠረተ ልማቶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ሕጎችን ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

- የሀገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋና እንዲዘምን፣ ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፤ በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤
- የሀገሪቱ የወጪ ንግድ የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ እንዲያቀርቡ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የውጭ ንግድ ግንኙነቶችን ይመሠርታል፣ የንግድ ስምምነቶችን በሕግ መሠረት ይፈራረማል፣ ሲጸድቅም ያስፈጽማል፤
- የወጪና ገቢ ንግድ ዕቃዎችን ጥራት ይቆጣጠራል፣ ተፈላጊውን የደረጃ መሥፈርት የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ወይም ከሀገር እንዳይወጡ ይቆጣጠራል፤
- የወጪና ገቢ ዕቃዎች በትክክለኛ ዋጋ ስለመሸጣቸው ወይም ስለመገዛታቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ክትትል ያደርጋል፤
- ቀላል፣ ወጪ ቆጣቢና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል፤
- የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ መሠረታዊ የንግድ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ዋጋ እያጠና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤
- የንግድና የዘርፍ ማህበራት፣ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል፣ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤
- የሀገሪቱን ሕጋዊ ሥነ-ልክና ተስማሚነት ሥርዓት ለመተግበር እንዲቻል አስፈጻሚ አካላትን ያስተባብራል፤
- አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ማሟላታቸውን ይቆጣጠራል፣ በሌሎች አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶች የሚሠራባቸው አስገዳጅ ደረጃዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበሩ ያደርጋል፤

- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ስትራቴጂካዊ ትኩረት በሚሰጣቸው ዘርፎች የሀገሪቱን ምርቶች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ረገድ የታቀደውን እድገት ለማምጣት የሚያስፈልጉ ጥናትና ምርምሮች ያካሂዳል፣ ይተገብራል፤
- አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፣ የተሰጡ የንግድ ፈቃዶች ለተሰጠባቸው ዓላማ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፤
- የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ሥራን ይሠራል፤
- በአዋጅ ቁጥር 551/1999 ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን የተሰጡ ከዳኝነት ችሎት ሥራ ውጪ ያሉ ተግባርና ኃላፊነቶችን በሥራ ላይ ያውላል፤
- በንግድ ውድድር እና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 ለንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን ተሰጥተው የነበሩ ከዳኝነት ችሎት ሥራ ውጪ ያሉ ተግባርና ኃላፊነቶችን በሥራ ላይ ያውላል፤
- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለንግድ ውድድሮችና ሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን፣ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን እና ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጡ ንግድን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዚህ አዋጅ ለተቋቋመው የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተሰጥተዋል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል አደረጃጀት

8. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሚመራና የሚተዳድር ሲሆን፤ ተጠሪነቱም ለሚኒስተሮች ምክር ቤት ሆኖ ሶስት (3) ዘርፎች እነርሱም የንግድ ትስስርና ወጪ ንግድ፣ የንግድ ስርዓትና ላይሰንሲንግ እና የጥራት መሠረተ ልማትና ማረጋገጫ ዘርፎች ናቸው፡፡ እንዲሁም ሃያ (20) ስራ አስፈጻሚ እና ሃያ አራት ዴስኮች (24) አሉት፡፡ ከሃያ ስራ አስፈፀሚ አራቱ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ኃላፊ ስር፣ ሰባቱ በስራ አመራር ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሲሆኑ የቀሩት ሰባቱ በሶስቱ ዘርፎች ስር ናቸው፡፡ አስራ ሰባት (17) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና ስድስት (6) ተጠሪ መ/ቤቶች አሉት፡፡ የሚኒስትር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

**የሰው ኃይል**

9. የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከ2015-2016 በጀት አመት በመዋቅር የተፈቀደለት የሰው ኃይል ብዛት 833፤ በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ወንድ 402፣

ሴት 298 በድምሩ 700 ሠራተኞች አሉት፡፡ በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመዋቅሩ ከተፈቀደለት የሰው ኃይል 84% ያሟላ ሲሆን 133 (16%)ቱ በሰው ኃይል ያልተሞላ ነው፡፡ ይህም በትምህርት ደረጃ ሲገለፅ ዶክቶሬት 1፣ በማስተርስ ሴት 23 ወንድ 69፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ሴት 163 ወንድ 348፣ በዲፕሎማ ሴት 76 ወንድ 99፤ ከ12ኛ በታች ሴት 115 ወንድ 83 በስራ ላይ የሚገኙ የሰው ኃይል መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር የሚያከናውነው መንግሥት በሚመደብለት መደበኛ እና ካፒታል በጀት ሲሆን፣ ከ2013 እስከ 2016 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ በጀት ዓመት የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ዝርዝር ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

| በጀት አመት | የተመደበ መደበኛ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀት | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2013 | 380,931,978.60 | 308,722,121.65 | 72,209,856.95 | 81.04% |
| 2014 | 687,636,813.07 | 563,736,298.53 | 123,900,514.44 | 81.98% |
| 2015 | 356,251,754.85 | 108,325,966.00 | 247,925,788.85 | 63.41% |
| 2016 ግማሽ አመት | 289 625 986.00 | 15961456.32.00 | 227884 481.22 | 41% እስከ 3/4/216 |
| ድምር | 1,424,820,546.52 | 980,784,386.18 | 444,036,160.24 | 68.8% |

| በጀት አመት | የተመደበ ካፒታል በጀት | ሥራ ላይ የዋለ | ሥራ ላይ ያልዋለ | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2013 | 782,065,372.74 | 726,031,337.90 | 56,034,034.84 | 92.84% |
| 2014 | 1,372,430,189.17 | 331,779,171.85 | 1,040,651,017.42 | 24.17% |
| 2015 | 788 000 000.00 | 625 291 421.38 | 162 708 578.62 | 79.35 |
| 2016 ግማሽ አመት | 744 000 000 | 484 934 985.30 | 259 065 014.70 | 65.18 እስከ 30/4/216 |
| ድምር | 3,642,778,191.27 | 1,510,476,040.05 | 2,132,302,151.32 | 82.41% |

**ማብራሪያ**: የ2014 በጀት ዓመት የካፒታል በጀት አጠቃቀም 24% የሆነበት ምክንያት የጥራት መሰረት ልማት የግንባታ ፕሮጀክት በመቋረጡ ምክንያት መሆኑን ገልፃዋል፡፡

## የኦዲቱ አላማ

11.የክዋኔ ኦዲቱ አላማ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች (ስንዴ፣ ዘይት፣ ስኳር) ስርጭትን አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ የወጡ ሕጎች እና መመሪያዎች መሰረት በተቀላጠፈና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ ማድረጉን ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየት የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረብና ተጠያቂነትን ለማስፈን ነው፡፡

**የኦዲት አካባቢ (Audit Area)**

12.ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ " የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አፈጻጸም" ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

13.ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም፡-

1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤
2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት፣ ክፍፍል፣ አቅርቦት ለማከናወን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን መገምገም ፡፡
3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭት፣ ክፍፍልና አቅርቦትን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማደረጉን መገምገምን የሚሉት ናቸው፡፡

## የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria)

14.በኦዲት ቡድኑ የተመረጡ ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚረዱ አስራ ሰባት (17) የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀርቦ ምላሽና አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ ቁጥር 1263/2014፣ የንግድ ውድድርና ሸማቶች ጥበቃ ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 813/2006 በ2013 በጀት ዓመት የተዘጋጀ የአስር፣ የአምስትና የመካከለኛ ዓመት ስትራቴጂክ እቅዶች፣ በ2008፣ በ2011፣ በ2014 እና 2015 ዓ.ም የተዘጋጁ መመሪያዎች፣ የቅዳሜና እሁድ ገበያን በተቀናጀ መልኩ ለመምራት የተዘጋጀ ማኑዋል፣ የሀገር ውስጥ ንግድና ሸማቾች ጥበቃ መሪ ስራ አስፈፃሚ የስራ መደብ፣ በ2014ና 2015 በጀት ዓመት የስሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ የተጠኑ ጥናቶች ናቸው፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ 1 ተያይዘዋል

## የኦዲት ወሰንና ዘዴ

### የኦዲቱ ወሰን

15.የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፍ የዋና ኦዲተር መ/ቤቶች የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (International Standards of Superem Audit Institutions (ISSAI) እናለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 እና በ1146/2011 እንደተሻሻለው በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡


16.የኦዲቱ ወሰን ከ2012 በጀት ዓመት እስከ 2016 ሁለተኛ ሩብ አመት ድረስ ያለውን ጊዜ ሲሆን ከሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የተከናወኑ ሥራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች፣ አከፋፋዮች እና ቸሪቻሪዎች፤ የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እና የዞኖችና ከተሞች የንግድ ቢሮዎች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች (የኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን እና የስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ) ባለድርሻ አካላት (ማዕድን ሚኒስቴር፣ ብሄራዊ ባንክ፣ ገቢዎች ሚኒስቴር) እና የሸማች ማህበራት (ዩኒዮኖች) ላይ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

### የኦዲቱ ዘዴ

17.ኦዲቱን ለማከናወን ከተቀመጠው የኦዲት አካባቢ ጋር ተያያዥ የሆኑ ማስረጃዎችን ከሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች፣ በናሙና ከተመረጡ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ዞኖች፣ ከተሞች በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎችና አከፋፋዮቻቸውና ቸሪቻሪዎቻቸው፣ የሸማቾች

ማህበራት (ዩኒዮኖች) መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በመከለስ፣ በመተንተን እና ሌሎች የኦዲት ዘዴዎችን በመጠቀም ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

**የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አሰራር ስርዓት መግለጫ /Process description/ ቀጥሎ ተመልክተዋል፡፡**



# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## ሀ/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን ለመቆጣጠር ሥርዓቶች መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤

### የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን ለማሳለጥ የህግ ማእቀፎች መዘጋጀቱን በተመለከተ

18. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን የሚያሳልጡ የህግ ማእቀፎችን (ፖሊሲ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ወዘተ) ሊያወጣ እና ሊተገብር ይገባል፡፡

19. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች ዞኖችና ከተሞች፣ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- የንግድ ፖሊሲ ረቂቅ ለፕላንና ልማት ሚኒስቴር በሰኔ 2015 ዓ.ም የተላከ ቢሆንም ኦዲቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያልፀደቀ መሆኑ፤
- የመሰረታዊ ሸቀጦች በተለያዩ አማራጮች በዲያስፖራ አካውንት ባላቸው ባለሃብቶች በፍራንኮቫሉታ እንዲገቡ የሚፈቀድ ሲሆን፤ ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ ካስገቡ በኋላ የስርጭት፤የቁጥጥር እና አስመጪዎቹ በየጊዜው ሪፖርት የሚያደርጉበት ስርዓት ያልተዘረጋላቸው መሆኑ እንዲሁም ከክልል እና ከተማ አስተዳደሮች ጋር የምርቶቹ የግብይት ትስስር ያልተደረገላቸው መሆኑ፤
- አስመጪዎቹም በውስን አካባቢ ብቻ የሚገኙ መሆኑና ሁሉም አካባቢ ተደራሽ እንዲያደርጉ የሚያስችል አሰራር አለመኖሩ እና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፍራንኮቫሉታ አስመጪዎች የዲያስፖራ የውጪ ምንዛሬ የባንክ ሂሳብ በመጠቀም ምርት ማስገባት እንደሚችሉ መስፈርቱ ሟሟላታቸውን ብሄራዊ ባንክ ስማቸውን በመጥቀስ ደብዳቤ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያሳውቅ ሲሆን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱም በፍራንኮቫሉታ ያስገቡትን አስመጪዎች መረጃው እንዲልክለት ለጉምሩክ ባለስልጣን እና መረጃው

እንዲደርሳቸው ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በግልባጭ በደብዳቤ ያሳውቃቸው የነበረ ሲሆን ይህ የደብዳቤ/መረጃ ልውውጥ ስርዓት ከታህሳስ 2014 ቁ.011-18/8725 በተፃፈ ደብዳቤ የተቋረጠ መሆኑ እና ማንነታቸው እንዳይታወቅ፣ ቁጥጥር እንዳይደረግባቸው እና የመረጃ ክፍተት እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑ፤

- በ2008 ዓ.ም የወጣ የመሰረታዊ ሸቀጦች መመሪያ እና በ2011 ዓ.ም የወጣ የምግብ ዘይት አቅርቦት እና ስርጭት ማስፈፀሚያ መመሪያ ለማሻሻል የተጀመረ ቢሆንም ተጠናቅቆ ያልወጣ መሆኑ፤
- በሲሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ግብይት ላይ የተጠኑ ጥናቶች መኖራቸው የሚያበረታታ ቢሆንም በጥናት የተገኙ ክፍተቶች እየተፈቱ አለመሆኑ፣ ለምሳሌ፡- የሲሚንቶ መመሪያዎች በግብይቱ ሂደት ላይ ክፍተትን በሚፈታ መልኩ የሚመለከታቸውን አካላት በማሳተፍ የማይወጡ በመሆኑ የተሻሻለው መመሪያ በየጊዜው (ቶሎ ቶሎ) የሚቀያየር መሆኑ እና መመሪያዎቹ ግልፅ፣ ወጥ፣ ሁሉንም አካታች ያላደረጉና ክፍተት ያለባቸው መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎችና በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው አካላት የገለፁ መሆኑ፤
- የሲሚንቶ መመሪያ ቁጥር 940/2015 ረቂቅ መመሪያ ሲዘጋጅ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያልተሳተፉ መሆኑ እና በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ፤
- የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች መመሪያዎች የማይደርሳቸው መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

20. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ማጠቃለያ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ላይ በሰጡት ምላሽ የንግድ ፖሊሲ በረቂቅ ደረጃ ላይ መሆኑ እና በሌሎች ሃገራዊ ፖሊሲዎች እየተጠቀሙ እንደሚገኙ፤ የፍራንኮቫሉታ የስርጭት፣ የግብይትና የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋው ግብይታቸውን ነፃ ለማድረግ መሆኑ እና ቁጥጥር የማይደረግባቸው መሆኑ፤ በ2008 ዓ.ም የወጣ የመሰረታዊ ሸቀጦች መመሪያ እና በ2011 ዓ.ም የወጣ የምግብ ዘይት አቅርቦት እና ስርጭት መመሪያ ለማሻሻል ተጀምሮ እንደነበረ ገልፀዋል፡፡
21. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የፍራንኮቫሉታ የስርጭትና የግብይት የሚያስተዳድር ሥርዓት የሚያስፈልግ በመሆኑ እና ምርቶቹ ከቀረጥ ነፃ ገብተው

ለህብረተሰቡ ህጋዊና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ስለመሰራጨታቸው የቁጥጥር እና ትስስር ስርዓት አስፈላጊ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አዳጋች ያደርገዋል፡፡

22. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች ስራውን /ስርጭቱን/ ለማቀላጠፍ የሚያስችሉ የህግ ማእቀፎች፣ የንግድ ፖሊሲ ፀድቆ ባለመተግበሩ ፓሊሲውን ተከትሎ የንግድ ህጉን ለመምራት የሚያስችሎ ህጎችና መመሪያዎች እንዳይወጡ፣ ግልፅነት እና ወጥነት እንዳይኖራቸው እና ጤናማ ግብይትና ስርጭት ሥርአት እንዳይዘረጋ አድርጓል፡፡ እንዲሁም የፍራንኮቫሉታ አስመጪዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ ቢፈቀድላቸውም የስርጭትና የግብይት ስርዓት ባለመዘርጋቱ የኑሮ ውድነቱ እንዳይቀንስ፣ ገበያው እንዲይረጋጋ፣ በፍራንኮቫሉታ ሊሸፈን የታሰበው የመሰረታዊ ሸቀጥ ፍላጎት/ጉድለት/ እንዳይሸፈን ከማድረጉ በተጨማሪ ተጠያቂነትና ፍትሃዊነት የሰፈነበት የግብይትና የስርጭት ሰንሰለት እንዳይኖር እና ምርቶቹ ለሁሉም አከባቢዎች ተደራሽ እንዲሆኑ የቁጥጥር እና ትስስር ስርዓት እንዳይኖር አድርጓል፡፡

23. እንዲሁም የሲሚንቶ መመሪያዎች የሚመለከታቸው አካላት በማሳተፍና ክፍተትን በሚፈታ መልኩ የማይዘጋጁ በመሆኑ የግብይትና የስርጭት የሚታዩት ችግሮች እንዳይፈታ፤ ሁሉም ተዋናይ አካታች እንዳይሆኑ፣ መመሪያዎች በፍጥነት እንዲቀያየሩና ተግባራዊ እንዳይሆኑ በማድረግ በህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዳይሆን እና ፍትሃዊ የሆነ የሲሚንቶ ስርጭት እንዳይኖር አድርጓል፡፡

**የመሰረታዊ ሸቀጦች እና የሲሚንቶ የስርጭት ስርአት መዘርጋቱ በተመለከተ፡**

24. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች፣ ቸርቻሪዎችን እና የሲሚንቶ አምራቾች የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ የስርጭት ስርአት ሊዘረጋ እና በየጊዜው አፈጻጸሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

25. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦትን መሰረት ያደረገ የስርጭት ሥርአት አለ ለማለት አዳጋች መሆኑ፤ የአቅርቦትና የፍላጎት ከፍተኛ ልዩነት

መኖሩ እና ምርቶቹ ለረጅም ጊዜ መዘግየት፣ የስርጭት መቆራረጥና እጥረት መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታይቷል፤

**የመሰረታዊ ሸቀጦችን በተመለከተ፡-**

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በፍራንኮቫልታ/አስመጪዎቹ በአቅርቦት፣ በግብይትና በአሰራር ባሉት ክፍተቶች ላይ በ2014 እና 2016 የዳሰሳ ጥናት መደረጉ ጥሩ ቢሆንም የተለዩ ክፍተቶቹ አሁንም ያልተፈቱ መሆኑና ለምሳሌ ምርቶች በየዙሩ ግዥ ከተፈፀመ በኃላ በከፊል/ግማሽ ምርቱ ብቻ ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚገባ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የአቅርቦትና የግብይት ችግር መኖሩ፣ በፍራንኮቫልታ/አስመጪዎቹ የንግድ አድራሻቸው ተለዋዋጭና የማይታወቅ መሆኑ፣ የስርጭት ሰንሰለቱ የማይታወቅ መሆኑ እና ምርቶቹ ቀጥታ ወደ ህብረተሰቡ ስለመድረሱ ቀጣይነት ያለው ክትትል የማይደረግ መሆኑ በጥናቶች፣ በቃለ-ጉባኤ እና በቃለ-መጠይቆች ላይ የተገኙ ቢሆንም ችግሩ መፍትሄ ያልተሰጠው መሆኑ፤
- እንዲሁም ሃገር ውስጥ ያሉ ምርቶችም ጭምር የግብይት ሂደቱን በማዛባት፣ አየር በአየር መሸጥ፣ ምርቱ ወደ ገበያ አለማውጣትና እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ዋጋ መጨመር፣ ያለደረሰኝና ከዋጋ በታች አድርጎ ደረሰኝ መቁረጥ ክፍተቶች መኖራቸው በጥናቶች፣ በቃለ-ጉባኤ እና በቃለ-መጠይቆች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች፣ አምራቶችና አከፋፋዮች/ ቸርቻሪዎችን እና የሲሚንቶ አምራቶች አሁን ካለው ፍላጎት፣ አቅርቦትና እጥረት አንፃር ተደራሽ ለማድረግ ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ እንዲጣጣም ያልተደረገ መሆኑ፤
- የፍራንኮቫሉታ ሂሣብ የከፈቱ አቅራቢዎች ምርቶቹ ወደ ሃገር ውስጥ ሳያስገቡ በወደብ ላይ ምርቶቹ እንዲቆዩ በማድረግ የሀገር ውስጥ መሸጫ ሲጨምር ምርቶቹን የሚያስገቡ መሆኑ በጥናቶች፣ በቃለ-መጠይቆች እና በቃለ ጉባኤዎች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- የፍራንኮቫሉታ አስመጪዎች የውጭ ምንዛሬ አላቸው ተብሎ ምርቶች እንዲያስገቡ የሚፈቀድላቸው ቢሆንም አብዛኞቹ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እንዳለባቸውና ምንጫቸው ጥቁር ገበያ መሆኑና የሚገዙትም በጥቁር ገበያ መሆኑ ይህም በዋጋ እንዳይቀንስ እያደረገ መሆኑ እና ሀገር ውስጥ በሕጋዊ

መንገድ የሚነግደውን የወጪ ምርት እና ቀጥታ ወደ ሃገር ውስጥ ባንክ ይገባ የነበረ የውጪ ምንዛሪ ሃገሪቷን እንድታጣ እያደረገ መሆኑ፤ ያስገኙት ውጤትም እየተገመገመ እና ቁጥጥር ምርመራ እየተደረገ አለመሆኑ በጥናቶች፣ በቃለ-መጠይቆች እና በቃለ ጉባኤዎች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤

- በፍራንኮቫሉታ/በአስመጪዎቹም የቢሮክራሲ መብዛት እና አላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪዎች እያወጡ መሆኑ፡ ለምሳሌ በየኬላው የሚከፈል እና ለልማት ተብሎ በየቦታው የሚከፈሉት ክፍያዎች፣ በጸጥታ አካላት ምርቱን እንዲታሽግ እና በአስመጪዎች ላይ ወከባ በመፍጠር ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅ በትራንስፖርት ዋጋ መጨመሩ እና እነዚህም የዋጋ ንረት የሚያስከትሉ መሆኑ በጥናቶች እና በቃለ ጉባኤ ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- እንዲሁም ምርቶቹ ወደብ ላይ እንዲከማች የማድረግ እና እዛ የመሸጥ ሁኔታዎች መኖራቸው በተለይ የምግብ ዘይት በሁሉም አስመጪዎች ጅቡቲ ላይ እንዲቆይ በማድረግ ምርቱን ጅቡቲ ላይ የሚሸጡት መሆኑ በጥናቶች እና በቃለ ጉባኤ ላይ የተገለፀ መሆኑ፤

ለማሳያ በመጋቢት 2014 እና 2016 በጀት ዓመት የተጠኑ ጥናቶች፡-

- ✓ ቀመር ረዲን የተባሉ የአስመጪ በቢሮክራሲ ምክንያት ወደ 40,000 ኮንቴነር ግዥ ፈጽመው ለማምጣት ስጋት ስለፈጠረባቸው ጅቡቲ ላይ ያስቀመጡት መሆኑ፣
- ✓ በተመሳሳይ አቡልከኒ መሃመድ የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ፓልም የምግብ ዘይት ባለ 20 ሊትር በሊትር መጠን 2477 ጀሪካን፣ባለ 3 ሊትር ፓልም መጠን 1028 ካርቶን፣ፓልም ባለ 5 ሊትር 4012 ካርቶን፣ሰንፍላወር ባለ 5 ሊትር 3044 ካርቶን እና ሰንፍላወር ባለ 1 ሊትር 7922 ሊትር በጠቅላላ 217086 ሊትር ግዥ ተፈጽሞ ጅቡቲ ላይ በመጋዘን ታሽጎ ያለ መሆኑንና ወደ ሀገር ውስጥ ምርቱን ለማስገባት ስጋት መሆኑን፣
- ✓ በተጨማሪም ምርቱን ህጉን በተከተለ መልኩ ህጋዊ ሽያጭ ደረሰኝ ቢኖረውም በመንግስት አካል 217,086 ሊትር በላይ ስለታሸገበት ለከፍተኛ ኪሳራ መዳረጉን የገለፀ መሆኑ አሁንም ችግሮቹ ስለመፈታታቸው የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ፣ በጥናቶች፣ በቃለ-መጠይቆች እና በቃለ ጉባኤዎች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤

**የሲሚንቶ ምርት በተመለከተ፡-**

- ❖ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለአከፋፋዮችና ለቸርቻሪዎች በተዘረጋላቸው ሰንሰለት ምርቱ እየቀረበ አለመሆኑ በጥናቶች፣ በቃለ-መጠይቆች፣ በአካል ምልከታ ሪፖርቶች እና በቃለ ጉባኤዎች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- ❖ የሲሚንቶ አቅርቦት በተዘረጋው የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ የስርጭት ስርዓት መሰረት ያደረገ ሳይሆን የምርቱን ፈላጊዎች መሰረት ያደረገ መሆኑ እና በተለይ የመንግስት ተቋማት የሲሚንቶ ምርቱን አናገኝም በማለት ከሚያስፈልጋቸው በላይ የአቅርቦት ጥያቄ የሚያቀርቡ መሆኑ እና ባለው ከፍተኛ የአቅርቦት እጥረት ላይ አርተፊሻል እጥረት እያስከተሉ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ በቀረበላቸው አካላት የገለፁ መሆኑ፤
- ❖ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎች የሲሚንቶ ስርጭትን ግልፅ አለማድረጉ እና ምርቱን ከየት እንደሚመጣ ምንጩ የማይታወቅ መሆኑን በቃለ-መጠይቆች እና በተከለሱ ማስረጃዎች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- ❖ የጅምላ አከፋፋይ የሌላቸው ክልሎችም መኖራቸው ለምሳሌ የሃረር ክልል ከአዳማ፣ ከአዲስ አበባና ከአማራ ክልል አከፋፋይ እንደተመደበላቸው የተገለፀላቸው ቢሆንም አከፋፋዮቹ በክልሉ እንደሌሉ፤ በክልሉ የሚገኙ ቸርቻሪዎች ምርቱ በህገ-ወጥ ደላላ እየተረከቡ ለህብረተሰቡ የሚሸጡ መሆኑ የክልሉ ንግድ ቢሮ እና ቸርቻሪዎቹ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፤
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመጋቢት 2015 በቁ.01-01-811/43293 በተፃፈ ደብዳቤ በመመሪያው መሰረት ለሁሉም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለመንግስት ፕሮጀክቶች ቢያንስ 30 በመቶ ቅድሚያ እንዲሰጡ እና የተሰጠውም ሲሚንቶ ስራ ላይ ስለመዋሉ አፈፃፀሙ ከሚመለከተው አካል ጋር በጋራ የክትትል እንደሚያደርጉ በደብዳቤው ቢገልፅም ክትትል ስለመደረጉ ማስረጃው አለመቅረቡ፤
- ❖ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ 90 በመቶ ለአባይና ለሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች እንደሚያቀርብና ለረጅም ጊዜ ከመንግስት ጋር ውል መግባቱን ቢገለፅም ማሰረጃው/ውሉ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤ ለመረዳት ተችሏል፡፡

26.ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ በፍራንኮቫሉታ የተሰማሩ ነጋዴዎች ምርቱን በተከታታይነት ለማስመጣት ከሚያጋጥማቸው ችግሮች ውስጥ የውጪ ምንዛሪ እጥረት፣ የትራንስፖርት ማጓጓዣ እጥረት፣ የጉምሩክ ኮሚሽን ፎርማሊቲ እና በመሳሰሉ ችግሮች ምርቱ ጊዜውን ጠብቆ ወደ ሃገር ውስጥ እያስገቡ አለመሆኑ፤
- ❖ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ በፋብሪካዎች የተመረጡ ዝርዝር የጅምላ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች ነጋዴዎች ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ክትትል እንዲያደርጉ በደብዳቤ የተላከ መሆኑን፤ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በየጊዜው ከአቅርቦት ብሎም ስርጭት ጋር ተያይዞ ችግሮች ሲያጋጥሙ እንደአስፈላጊነቱ የምርት አቅርቦት እና ስርጭት መመሪያዎችን በማውጣት ክትትል እና ቁጥጥር እያደረጉ መሆኑ፤
- ❖ የሲሚንቶ ምርት የአቅርቦት እጥረት በመኖሩ እየቀረበ ያለው ከ1/3 ያልበለጠ መሆኑ እና የስርጭት አፈጻጸም በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ ማድረግ አስቸጋሪ መሆኑ፤ ግብይቱም ግልጽ እንዲሆን በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ለማድረግ ለረጅም ጊዜ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ሲሰራ የነበረው ሲስተም ተጠናቆ በሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ የጀመረ መሆኑ፤

ገልፀዋል፡፡

27.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ሲሚንቶ በፋብሪካዎች የተመረጡ ጅምላና ቸርቻሪዎች ነጋዴዎች ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከተላከላቸው ዝርዝር የተሟላ አድራሻ የሌላቸው እንዳሉ እና ዋጋ ያልተቀመጠላቸው መሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቴሌ ብር ግብይት ለማስጀመር የፋብሪካዎቹ ጅምላና ቸርቻሪዎች መረጃ በጥር 2016 ዓ.ም ጠይቆ ያልላኩ ፋብሪካዎች በመኖራቸው ክፍተት መኖሩ ማሳያ በመሆኑ፣ ለመቆጣጠር እንዳስቸገራቸው እና እየተቆጣጠሯቸው ባለመሆኑ፣ በመስከረምና በጥር 2015 ዓ.ም ከቀረበው የመስክ ምልከታ ሪፖርት በስተቀር የስርጭት ቁጥጥር የተደረገበት ማስረጃም ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

28.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች የምርቱ አቅርቦት መነሻ ያደረገ ግብይትና ስርጭት ባለመኖሩ ህብረተሰቡ ለከፍተኛ የምርት እጥረት፣ አለመረጋጋት፣ ለዋጋና ኑሮ ውድነት ተጋላጭ አድርጎታል፡፡

**የመሰረታዊ ሸቀጦችን አስመጪዎች/ አቅራቢ ድርጅቶች አመራረጥ ሂደት በተመለከተ**

29. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችን አስመጪዎች/አቅራቢ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መመረጣቸውን የሚቆጣጠርበት እና ቅሬታዎችን የሚያስተናግድበት ስርዓት ሊዘረጋ እና ሊተገበር ይገባል፡፡

30. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን አስመጪዎች፤ አቅራቢ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መመረጣቸውን የማያረጋግጥ እና የማይቆጣጠር መሆኑ፤
- ❖ ሚስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች (የዘይት) ከ2013 ዓ.ም እና የሲሚንቶ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ አከፋፋዮች ሲመረጡ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአመራረጡ ላይ የማይሳተፉ መሆኑ፤ በአከፋፋይነት ተመርጦ እየሰሩ ያሉ አከፋፋዮች በመመሪያው መሰረት ስለመመረጣቸው በግልፅ የማያሳውቁ መሆኑ እና አከፋፋዮቹ ከሌላ አከባቢ በሚመጡ ጊዜ ከፍተኛ ቅሬታ መፍጠሩ እና ክልሎች ለመቆጣጠርም ክፍተት እየፈጠረባቸው መሆኑ፤ ለማሳያ፡-
  - ✓ የሃረር ክልል ፒያኖር የሚባል የጅምላ አከፋፋይ በክልሉ በጥሩ ሁኔታ ለቸርቻሪዎቹ ሲያከፋፍል የቆየ ሲሆን ባልታወቀ ምክንያት ከክልሉ መውጣቱ እና ከአዳማ፣ ከአዲስ አበባና ከአማራ ክልል የሲሚንቶ የጅምላ አከፋፋይ የተመደበላቸው መሆኑ፤ ይህም ሆኖ አከፋፋዮቹ ሆነ ወኪሎቻቸው በክልሉ እንደሌሉ እና ክልሉና በክልሉ የሚገኙ የሲሚንቶ ቸርቻሪዎች/ነጋዴዎች ከፍተኛ ቅሬታ እንዳደረባቸው በኦዲቱ ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፤
  - ✓ በደቡብ ምዕራብ ህዝቦች ክልልና ሌሎች ክልሎች የፍጆታ እቃዎች ዘይትና የስኳር አቅራቢዎች ከተመደቡ በኋላ ካፒታል የሌላቸው

በመሆኑ በመሃል እየጠፉ መሆኑ እና አከፋፋዮች የመቀየር ሁኔታ ቢኖርም መስፈረቱ ሟሟላታቸው የማይረጋገጥ መሆኑ፤

- ❖ በሲሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት እና አከፋፋዮች አመራረጥና አመዳደብ ከክልል ክልል በየወቅቱ የሚለዋወጥ፣ ግልፅነትና ወጥነት የሌለው መሆኑ፣
- ❖ ክልሎች የተመደቡበት የስኳር ፋብሪካዎች ርቀት ፋብሪካዎቹ ያለማምረት ችግር ቢኖርም እያመረቱ ባሉ ፋብሪካዎች ሚዛናዊ በሆነ አመዳደብ ላይ ክፍተት መኖሩ ክልሎች ቅሬታ እያቀረቡ መሆኑ ለምሳሌ ለድሬዳዋ፣ ሃረር፣ ሱማሌ ክልሎች መተሃራ መመደብ ሲኖርባቸው ኦሞ ኩራዝ የተመደቡ መሆኑ፤ አዲስ አበባ መተሃራ ተመድቦ ትግራይ ኦሞ ኩራዝ መመደብ ሚዛናዊ አለመሆኑ እና ምርቱ ዘግይቶ እንዲደርስ፣ በየመንገዱ የደህንነት ችግር እና በዋጋ ጭማሬና የምርት እጥረት ላይ ተፅእኖ እየፈጠረ መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎች የተገለፀ መሆኑ፤

ለማወቅ ተችሏል፡፡

31.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው የማጠቃለያ ጥያቄና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ የምግብ ዘይት ከ2013 መጨረሻ ጀምሮ ከድፍድፍ ጥሬ ዕቃ የምግብ ዘይትን በሀገር ውስጥ እንዲቀርብ አከፋፋዮችን በመምረጥ ፋብሪካዎችና በክልሎች የጋራ ስምምነት ላይ ደርሰው ክልሎች አፋፋዮችን ውል በማስገባት ወደ ስርጭት የሚገቡ መሆኑንና የውል ስምምነት ናሙና ማስረጃ ማቅረባቸው፤
- ❖ ከመሰረታዊ ሸቀጦች ውስጥ ስኳር በመመሪያ ቁጥር 02/2008 በአቅራቢነት እንዲሳተፉ የሚፈቅደው ለሕብረት ሥራ ማሕበራት ዩኒየን ሲሆን ሁሉም በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የተመረጡት መሆኑ እና የመመሪያ ለውጥ /ከክልል ክልልም የሚፈጸም ተለዋዋጭ አሰራር እንጂ አከፋፋዮች አመራረጥና አመዳደብ ከክልል ክልል በየወቅቱ የሚለዋወጥ አለመሆኑ፤

ገልፀዋል፡፡

32.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የዘይት ከ2013 እና የሲሚንቶ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ አከፋፋዮቹ በፋብሪካዎች እና በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመረጡ መሆኑ እና ክልሎች በአመራረጡ ላይ የማይሳተፉ በመሆኑና ቅሬታ እያቀረቡ በመሆኑ፣ እንዲሁም በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው

አካል ጋር ችግሩ እየፈታ ስለመሄዱ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ባለመቅረቡ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

33.በመሆኑም የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችን እና የሲሚንቶ አስመጪዎች፣ አቅራቢ፣አከፋፋይ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መስፈርት አሟልው መመረጣቸው ባለማረጋገጡና ባለመቆጣጠሩ እና ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በአመራረጡና በሰንሰለት ዝርጋታው ላይ ክልሎች ተሳታፊ ባለማድረጉ የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭት ክልሎች ገበያ ላይ ያለው ምርት እና ዋጋ እንዳይቆጣጠሩ እንዲሁም ምርቶቹ በተዘረጋላቸው ሰንሰለትና በታለመላቸው አላማ ህብረተሰቡ ጋር እንዳይደረሱ፣ የምርቶቹ ስርጭት የቅሬታ ምንጭ እንዲሆኑ እና የኑሮ ውድነት እንዲባባስ አድርጓል፡፡

34.እንዲሁም ቅሬታዎች ሲፈጠሩ የሚፈታበት የአሰራር ሥርአት አለመዘርጋቱ ተጠያቂነት እንዳይጠናከር እና አቅራቢዎችም ሆኑ አከፋፋዮች የህብረተሰቡን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲያሳድሩ አድርጓል፡፡

**በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች የሥርጭት ሂደትን በተመለከተ፤**

35.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ኮታ ሊደልደል፣ የፋብሪካዎች፣ የአስመጪዎች፣ እና አቅራቢ ድርጅቶች የሚያከፉፍሉባቸውን አካባቢዎች ሊወሰንና ሊያሳወቅ ይገባል፡፡

36.ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ 2001/2003 ዓ.ም በወጣው የኮታ ድልድል የሚተገበር ሲሆን ይህ የኮታ ድልድል ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ አለመሆኑ፤ እንዲሁም የሲሚንቶ ኮታ ድልድል በጥናት የተደገፈ ግልፅ የሆነ የኮታ መነሻ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክልሎችን እና ከተማ አስተዳደሮችን የመሰረታዊ ሸቀጥ አቅርቦትን በተመለከተ ጥያቄ ሲያቀርቡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦች ምርቶቹ ሲኖሩ እናቀርባለን እንጂ እቅድ አታቅዱ እና የአቅርቦት

ጥያቄ አታቅርቡ የተባሉ መሆኑ በቃለ-ጉባኤዎችና በኦዲቱ ወቅት በቀረበለቻቸው በቃለ-መጠይቅ ላይ የተገለፀ መሆኑ፣

- መሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት የኮታ ድልድል በ2001/2003 ዓ.ም መሰረት እየተከናወነ ቢሆንም፣ በኮታው መሰረት የሚቀርበው ምርት እየቀነሰ መምጣቱ ለምሳሌ ከ2012/2013 ዓ.ም አንድ ሶስተኛ (1/3)፣ ከ2014 እና 2015 ዓ.ም ለወራት በተለይ (ድፍድፍ ዘይት) ለበርካታ ወራት እስከ አንድ ዓመት ክልሎች እንዳልደረሳቸው የገለፁ መሆኑ፣
- የስኳር አቅርቦት ክልሎች በኮታቸው መሰረት የማይቀርብላቸው መሆኑ በተለይ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ እየቀነሰ 1/4፣ 1/5 እና 1/6 እየሆነ ወደ ዜሮ እየመጣ መሆኑ፣ ከሰኔ 2015 ዓ.ም ጀምሮ አቅርቦቱ ወጥነት የሌለው መሆኑ እንዲሁም በየተራ ለሁሉም ክልሎች/ህብረተሰብ ማዳረስ እየተቻለ አለመሆኑ፣
- የትግራይ ክልል ንግድና ኤክስፖርት ኤጀንሲ ቢሮ ለክልሎች በየ45 ቀኑ ከሚላክላቸው በ6ኛው ዙር 3,928 ኩንታል ስኳር በኢትዮጵያ ንግድ ስራዎች ኮርፖሬሽን በኩል እንደተላከላቸው ቢገለፅም በቀን 04/12/2015 በደብዳቤ ቁጥር 03/323/15 ደብዳቤ እንዳልደረሳቸው በመግለፅ ሚኒስቴር መ/ቤቱን የጠየቁ መሆኑ እና ይህ ችግር እንደተፈታ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- እንዲሁም የ2013/2014 ዓ.ም የትግራይ ክልል መሰረታዊ ሸቀጦች የ17 ወራት ያልተላከላቸው መሆኑ እና ተፈናቃዮች ግምት ያስገባ ምርት እየቀረበላቸው አለመሆኑ በደብዳቤዎችና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥር 2016 ዓ.ም በተደረገው በክትትል ሪፖርት ላይ ቅሬታ ያቀረቡ መሆኑ፣
- ለክልሎች በየ45 ቀኑ ከሚላክላቸው የስኳር ምርት የወላይታ ዳሞታ ገበሬዎች ኅብረት ስራ ዩኒዬን በ80ኛ ዙር 5119 ኩንታልና በ83ኛ ዙር 3,840 ኩንታል ስኳር በድምሩ 8,959 ኩንታል ስኳር ለወላይታ ህብረተሰብ ለማቅረብ የተፈቀደውን እና የተላከው ስኳር ለህብረተሰቡ አለመድረሱ የኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በቀን 27/04/2015 በደብዳቤ ቁጥር ማዘ/245/15 ያረጋገጠ መሆኑ እና እንዲደርሳቸው ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- የዘይት ምርት አቅርቦት እስከ 2011 ዓ.ም በመንግስት 80 በመቶ ሳይቆራረጥና በተመጣጣኝ ዋጋ ይቀርብ የነበረ ቢሆንም ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ 5 በመቶ መውረዱ እና በውድ ዋጋ እየቀረበ መሆኑ እና ከ2015/2016 በጀት

ዓመት ጀምሮ ለዘይት ምርት የሚቀርብ የውጭ ምንዛሬ የተቋረጠ መሆኑ፤ ይህም ከ2011/2012 ጀምሮ የመሰረታዊ ሸቀጦች በፍራንኮቫሉታ በተወሰነ መልኩ እየገቡ የነበረ ቢሆንም ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በጊዜያዊ መፍትሄ ተብሎ 95 በመቶ ምርቶቹ በፍራንኮቫሉታ እንዲገባ የተደገረ ቢሆንም ምርቶቹ ተደራሽ አለመሆናቸው እና አሁንም የምርት እጥረትና የዋጋ ውድነት መኖሩ፤

- ❖ የኢትዮጵያ እህል ንግድ ኮርፖሬሽን እስከ 2010 ዓ.ም ባለው ጊዜ በአማካይ መጠኑ ከ400,000 እስከ 600,000 ቶን ስንዴ ከውጭ እያስገባ የገበያ ጉድለቱን ሲሞላ የቆየው የውጪ ስንዴ ግዢ በሃገር ምርት ለመሸፈን መታሰቡ (ጥረት መደረጉ) ጥሩ ቢሆንም ከ2012/2013 ዓ.ም ጀምሮ ትስስር ተፈጥሮላቸው ዱቄትና ዳቦ ሳይቆራረጥ በተመጣጣኝ ዋጋ ሲያቀርቡ የነበሩ ፋብሪካዎች ያለምንም ቅደመ ሁኔታ ትስስሩ የተቋረጠ መሆኑ፤ የህብረተሰቡ የዱቄት ፍላጎቱ ከፍተኛ መሆኑና በቂ አቅርቦት የሌለ መሆኑ፣ የዋጋ ውድነት እና ከፍተኛ እጥረት የተፈጠረ መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎች /በጥናቶች፣ በቃለ-ጉባኤዎች፣ ደብዳቤዎ፣ በቃለ-መጠይቆች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- ❖ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች እና አቅራቢ ድርጅቶች ፋብሪካዎቹም ጭምር እንዲሁም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች አከፋፋዮች የሚያከፋፉሉባቸውን አካባቢዎችን ተደራሽ አለመሆናቸው ለምሳሌ የሲሚንቶ አከፋፋዮች እና የፍራንኮቫሉታ አስመጪዎች ገበያ ያለበት አካባቢ ብቻ የሚገኙ መሆኑ፤ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ከፍተኛ እጥረት መኖሩ፤ በተለይ የሲሚንቶ አከፋፋዮች ሁሉም በሚባል ደረጃ አዲስ አበባ እየሄዱ እየሸጡ መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎች የተገለፁ መሆኑ፤
- ❖ የሲሚንቶ ምርት ኮታ ስርጭት በመመሪያ ያልተወሰነ በመሆኑ አከፋፋዮች ምርቱን በሚፈልጉበት ወቅት ሳይሆን አምራቹ በሚፈልገው ጊዜ በመጠንም አነስተኛ እንዲወስዱ የሚያዟቸው መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎች የተገኘ መሆኑ፤

የመሰረታዊ ሸቀጦችና የሲሚንቶ የአቅርቦት እጥረት መኖሩን

ለማሳያ፡-

- ✓ ደቡብ ብ/ብ/ህዝቦች ክልል በ2015 በጀት ዓመት የአምስት ወራት ስኳር 173,924 ኩንታል እንዲቀርብ ከተሰጠው ኮታ ውስጥ 28,697 (16.5%) ብቻ የቀረበ መሆኑ፤ እንዲሁም ፓልም የምግብ ዘይት

15,133,166 ሊትር ለማቅረብ ታቅዶ 2,078,601 (14%) ብቻ በማቅረብ እንዲሰራጭ መደረጉ፤

- ✓ እንዲሁም በመጋቢት 28/2015 በክልሉ ያሉት የመንግስት ልማት ድርጅቶችና የቅርንጫፍ ተቋማት 9500 ሰራተኞች ኮታ ውስጥ ሳይገቡ እንደነበር በመጥቀስ በአጠቃላይ 19,500 ሰራተኞች መኖራቸው እና የስኳር ኮታው እንዲስተካከል በ22/7/2015 ተጠይቆ 380 ኩንታል ለአንድ ጊዜ ብቻ የተፈቀደላቸው መሆኑ፤
- ✓ በአፋር ክልል ንግድ ቢሮ በየካቲት 20/2015 በቁጥር ደከሰ/311/2015 ዓ.ም በተፃፈው ደብዳቤ በጦርነቱ ምክንያት የግብይት ስርዓቱ/ኮታው መቋረጡ እና ከፍተኛ የመሰረታዊ ሸቀጦች እጥረት ያስከተለ መሆኑና አሁንም የምርቶቹ እጥረት መኖሩ፤ እና ችግሩ ስለመፈታቱ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ ፤
- ✓ በ2015 በጀት ዓመት ጋምቤላ የሲሚንቶ ምርት የወር ከተፈቀደላቸው 87,000 ኩንታል ውስጥ 19,000 ኩንታል (21 በመቶ) ብቻ የደረሰው መሆኑ፤ ስኳር የ1ኛ ዙር ከ5858 ኩንታል ኮታ ውስጥ 1662 ኩንታል የተሰራጨ መሆኑ እንዲሁም በ2ኛ ዙር 810 ኩንታል ብቻ ቀርቦ የተሰራጨ መሆኑ፤
- ✓ በ2015 በጀት ዓመት ቤንሻንጉልም የሲሚንቶ የወር ኮታ 87000 ኩንታል ሲሆን እየደረሳቸው አለመሆኑ፤
- ✓ የጋንቤላ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ 2015 በጀት ዓመት ስኳር በኩንታል እንዲሰራጭ የታቀደው 44,200 ሲሆን የተሰራጨው 3308 (7 በመቶ) መሆኑ፤ ስንዴ በኩንታል 248,000 እንዲሰራጭ ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑ፤ የምግብ ዘይት በሊትር 4,000,000 እንዲሰራጭ ታቅዶ 467,486 (12 በመቶ) ብቻ የተሰራጨ መሆኑ፤
- ✓ የሲሚንቶ ምርት በ2013 ዓ.ም 11,840,000 ኩንታል እቅድ/ፍላጎት የነበረ ሲሆን የተመረተውና የተሰራጨው 7,420,898 መሆኑ፤ በ2014 ዓ.ም 13,163,712 እቅድ/ፍላጎት የነበረ ቢሆንም የተመረተውና የተሰራጨው 4,404,050 መሆኑና የተፈጠረ ልዩነቱ /እጥረት 8,759,662 መሆኑ፤ የ2015 እና 2016 በጀት ዓመትም በጥናት የተደገፍ ባይኖርም የፍላጎቱና አቅርቦቱ ልዩነት እየሰፋ መምጣቱ

በተከለሱ ማስረጃዎች፣ በኦዲቱ ወቅት በቀረበላቸው በቃለ-መጠይቆች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤ የሲሚንቶ ምርት እጥረት መኖሩ ለማሳይነት (በአባሪ 3 ተመልክቷል)

37.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች በቀረበላቸው የማጠቃለያ ቃለ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፡-

- ❖ የመሰረታዊ ሸቀጦች የኮታ ድልድል የተጀመረው በ2003 ዓ.ም ሲሆን ከህዝብ ቁጥር መጨመርና ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ፍላጎት ማደግ ጋር ተያይዞ ኮታው ወቅታዊ ሁኔታን ያገናዘበ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ❖ የስንዴ ምርት ለረጅም ጊዜ ከውጪ ሀገር በግዢ እየገባ እና ድጎማ እየተደረገበት ለሸማቹ ይቀርብ የነበረ ሲሆን መንግስት በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ምርቱ ከውጪ እንዳይገባ የተከለከለ በመሆኑ ግብይቱ በነጻ ገበያ እየተፈጸመ መሆኑ፤
- ❖ ከ2013 ዓ.ም በፊት በየወሩ በቋሚነት የውጭ ምንዛሪ ተመድቦ 40 ሚሊዮን ያለቀለት ዘይት ይቀርብ የነበረ የተቋረጠ በመሆኑ እና በሀገር ውስጥ ትላልቅ ፋብሪካዎች ድፍድፍ ዘይት እንዲገባ ተፈቅዶ የሚመደበው የውጭ ምንዛሪ እየቀነሰ በመሄድ እና የሚቆራረጥና በወቅቱ የማይፈቀድ በመሆኑ ስርጭቱ ላይ መቆራረጥና ወጥነት እንዳይኖረው ማድረጉ፤ የስኳር አቅርቦት በዋናነት በፋብሪካዎች የማምረት አቅም የተመሰረተ መሆኑ፤
- ❖ የሲሚንቶ ኮታ ድልድል መነሻ ለመመሪያ ቁጥር 908/2014 ሲዘጋጅ የሲሚንቶ አምራች ማህበር አስተያየት የሰጡበት በሃምሌ 1/2014 ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተላከ ደብዳቤ ማስረጃ የቀረበ መሆኑ፤
- ❖ የሲሚንቶ ምርት በ2015 በጀት ዓመት በወጣው መመሪያ ቁጥር 908/2014 መሠረት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ሁሉንም አካባቢዎች ባማከለ መልኩ አከፋፋዮችን እየመለመሉ ስርጭት ይደረግ እንደነበር እና በመመሪያ ቁጥር 940/2015 አቅርቦትና ሥርጭት በኮታ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን መደበኛ የገበያ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ መሆኑና የአቅርቦት ሁኔታው የማምረት አቅም ላይ የተመሠረተ መሆኑ፤ ከ2015 በጀት ዓመት በፊት በነጻ ገበያ ስርዓት ውስጥ ግብይት ይፈጸም የነበረ መሆኑን እና በአጠቃላይ በሲሚንቶ ግብይት ላይ የሚታየው ህገ-ወጥ ተግባራት በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለ ከፍተኛ ልዩነት በመኖሩ ከፋብሪካዎች በተደጋጋሚ ውይይት

መደረጉ እና ክልሎችም ከተመረጡ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች ውይይት እንዲያደርጉና ሪፖርት እንዲልኩ መደረጉን፤

ገልፀዋል፡፡

38.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የሲሚንቶ ኮታ ድልድል መነሻ የተባለው ለመመሪያ ቁጥር 908/2014 ሲዘጋጅ የሲሚንቶ አምራች ማህበር ውይይት አድርጎ አስተያየት የሰጡበት ደብዳቤ እንጂ የፍላጎት ጥናት መሰረት በማድረግ ኮታ የደለደሉ ባለመሆኑ፤ በሲሚንቶ ግብይት ላይ የሚታየው ህገ-ወጥ ተግባራት ከላይ እንደገለጽነው በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለ ከፍተኛ ልዩነት መኖሩ ከፋብሪካዎች ጋር በተደጋጋሚ ውይይት መደረጉን የሚያሳዩ ቃለ ጉባኤዎች ባለመቅረባቸው፤

39.ክልሎችም ከተመረጡ ከአከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች ውይይት አድርጎ የውይይት ሪፖርቱ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ እና ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከአከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች እንደማያውቋቸው የገለፁ መሆኑ እና በሲሚንቶ ምርት ግብይትና ስርጭት ዙሪያ ግልፅ የሆነ አሰራር ባለመኖሩ በክልሎች የክትትል ስራ እየሰሩ እንዳልሆነ ለኦዲት ቡድኑ የገለፁ በመሆኑ፤ እንዲሁም ክፍተቶቹ አሁንም የቀጠሉ በመሆኑ፤

40. እንዲሁም የመሰረታዊ ሸቀጦች በተመለከተ ከውጪ የሚመጣው የስንዴ አቅርቦት በሀገር ውስጥ የስንዴ ምርት ተተክቷል ቢባልም ምርቱን በግብአትነት የሚጠቀሙት ፋብሪካዎች ትስስር ያልተደረገላቸው እና በራሳቸው መንገድ እንዲያገኙ ያልተመቻቸላቸው በመሆኑ፤ እንዲሁም የስኳር ምርት በሀገር ውስጥ የሚመረተው አናሳ በመሆኑ ጉድለቱ እንዲሞላ ድጋፍ ያልተደረገ ባለመሆኑ ባለመደረጉ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

41.በመሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል እስከ 2011/2012 በየወሩ ሳይቆራረጥ በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ይቀርቡና ይሰራጩ የነበሩ መሰረታዊ ሸቀጦች ማለትም ስንዴ በመቋረጡ ፣ ዘይትና ስኳር በከፍተኛ መጠን እየቀነሰ በመምጣት ወደ መቋረጥ ደረጃ እየደረሱ በመሆኑ በተለየ ለዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ከፍተኛ እና በረሃማ የሆኑ አካባቢዎች ከአኗኗራቸው አንፃር በኑሮአቸው ተፅእኖ እንዲፈጠር በማድረጉ እንዲሁም ምርቶቹ በተለይ የፍራንኮቫሉታና የሲሚንቶ አከፋፋዮች ገበያ ባለበት አካባቢ እንጂ ሁሉም ክልሎች ተደራሽ ባለመሆናቸውና ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር ትስስር ባለመደረጉ የምርቶቹ እጥረት እንዳይፈታ እና ህብረተሰቡ ለከፍተኛ የኑሮ ውድነት እንዲጋለጥ አድርጎታል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን አቅርቦትና ስርጭትን ለመደገፍና ከአምራቾችና ከአቅራቢዎች ጋር መስራቱን በተመለከተ**

42. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን በየዓመቱ ፍላጎት እያጠና የአምራቶችንና የአቅራቢዎች በእቅዱ የሚያካትትበት፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ስለሚሰራጩበት፣ ስለሚሸጡበትና ከቦታ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ሊወሰንና ሸቀጦቹ ባለቀ ጊዜ እንዲተኩ የሚያደረግበት ስርዓት ሊዘርጋ ይገባል፡፡

43. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- ❖ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን የተጠኑ ጥናቶች ቢኖሩም የተጠቃሚው ፍላጎት መሰረት ያደረገ እቅድ በማዘጋጀት እና ተከታታይነት ባለው መልኩ ጥናት በማድረግ የአምራቾችንና የአቅራቢዎች እቅድ በእቅዱ የሚያካትትበት እና ምርቶቹ ባለቀ ጊዜ እንዲተኩ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፤

  ለማሳያ፡ የስኳር ምርት ክምችት እያለቀ በመሆኑ እንዲተካና ከውጭ ግዥ እንዲካሄድ ለሚመለከታቸው አካላት አንገብጋቢነቱ በተደጋጋሚ የስኳር ግሩፕ ኢንዱስትሪ እያሳወቀ መሆኑ ለምሳሌ ለ2013 ዓ.ም 200,000 ቶን ግዥ እንዲፈፀም ታቅዶ 100,000 ቶኑ በ2014 ዓ.ም የተሰራጨ መሆኑ፤ በ2014 ዓ.ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአነስተኛ መጠን የምርቱ ፍላጎት ለሟሟላት 300,000 ቶን ከውጭ እንዲገዛ ታቅዶ ያልተከናወነ መሆኑ እና 2015/2016 የግዥ እቅድ ያልታቀደ መሆኑ፤

- ❖ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የድፍድፍ ዘይት ምርት በተመለከተ በእቅድ ተካተተ የተባለው ከተፈቀደው የውጪ ምንዛሪ ውስጥ ምን ያክል ተመረተ የሚል መረጃ እንጂ የፋብሪካዎቹ እቅድ በእቅዱ የማያካትት መሆኑ፤ ከ2016 ዓ.ም የሲሚንቶ ምርት እቅድ በስተቀር ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ በእቅዱም ያላካተተ መሆኑና ወይም ለብቻው የሲሚንቶ ምርት እቅድ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤

❖ ምርቶቹ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የምርቶቹ ስርጭትና ሽያጭ፣ ከቦታ ወደ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ በየመንገዱ የሚገኙ ህጋዊ ያልሆኑ ኬላዎች ላይ እርምጃ እንዲወስዱ እንዲሁም ህጋዊ ኬላዎች ላይ ፍተሻ እንዲቀንስ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም አሁንም ችግሩ ያልተፈታ መሆኑ፣ ይሁንና አሁንም ኬላዎች ቀረጥ እየጠየቁ መሆናቸው ለምሳሌ መተሃራ ኬላ ለአንድ ኩንታል ስኳር 8 ብር የሚጠይቁ መሆኑ፣ የስንዴ ግብይት ከቦታ ቦታ አንቀሳቅሶ ለመሸጥ ሲሞከር በህጋዊም ይሁን ከህግ ውጪ የተቋቋሙ ኬላዎች ያልተገባ ክፍተኛ ክፍያ የሚጠየቁ መሆኑ፣

ለመረዳት ተችሏል፡፡

44. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው የማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ 2014፣ በ2015 እና 2016 በጀት ዓመት ምርቶች ላይ ጥናት መካሄዱና ጥናቶችም ለኦዲት ቡድኑ እንዳቀረቡ ገልፀዋል፡፡

45. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ ጥናቶቹ ቢጠኑም በጥናቶቹ የተገኙ ችግሮች እየተፈቱ አለመሆኑ እና ዓመታዊ የተጠቃሚው ፍላጎት እየተጠና የአምራቶችና የአስመጪዎች እቅዶች በእቅዱ የማያካትት በመሆኑ እና በእቅዳቸው መሰረት እንዲያሰራጩ ባለማድረጉ ምላሹን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

46. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዓመቱ የተጠቃሚ ፍላጎት በማጥናት እና በአምራቶች የሚመረተውና ከውጪ የሚገባውን ምርት በእቅዱ አካትቶ እንዲሁም ይህንን እቅድ ተግባራዊ እንዲሆንና ምርቶቹ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ (ሳይቆራረጥ) ለህብረተሰቡ እንዳይቀርቡ አድርጎታል፡፡

**የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፡**

47. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትና ግብይት እንዲሳለጥና እንዲዘምን ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን የግብይት ሥርዓቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት አለመዘርጋቱ እና ለክትትልና ለቁጥጥር ምቹ አለመሆኑ፣
- የመሰረታዊ ሸቀጦች የግብይት ሥርዓቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በአዲስ አበባ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በሁለት ክፍለ ከተማ (አራዳና የካ) የሙከራ ጅምር ስራ እየሰሩበት ቢሆንም እስከ አሁን ወደ ሌሎች ክፍለ ከተሞች፣ ክልሎች እና የከተማ አስተዳደር ከተሞች ያልተስፋፋ መሆኑ፣
- የፓልም ዘር (kernel) ላኪ ሃገራት ወደ ሀገራችን ዘሩን በማስገባት ወደ ዘይትነት መቀየር የሚያስችል ቴክኖሎጂ ገጥመው ማምረት የሚያስችላቸውን ጥናት እንዲሁም ከሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ለዘይት የሚሆን ዝርያ ማምረት የሚቻልበትን ሁኔታና አዋጭነቱን ለመፈተሽ እንደሚገባ በ2014 በተጠናው ጥናት ቢቀመጥም ያልተተገበረ መሆኑ፣
- የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት እንዲዳረስ ከማድረግ አንፃር በትክክል ተደራሽ በሆነ መልኩ ወደ ህብረተሰቡ ማቅረቡ ላይ ክፍተት መኖሩ ለምሳሌ ስኳር አከፋፋዮች ከስኳር ኮርፖሬሽን የተመደበላቸው ከወሰዱ በኋላ በትክክል ተደራሽ የማያደርጉ መኖራቸውን፣

ለመረዳት ተችሏል፡፡

45.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው የማጠቃለያ ቃለ-መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ የሲሚንቶ ምርት ስርጭትን ለማዘመን ከ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ሲሰራ የቆየ መሆኑንና በሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ሙከራ ትግበራ (Cement supply chain management system) በሌሎች ፋብሪካዎችም ስልጠና እየተካሄደ መሆኑ፣ የስኳር እና ዘይት ግብይትን ለማዘመን ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮ ቴሌኮም ጥያቄ ቀርቦ በ2015 በጀት አጋማሽ ላይ ተጠናቆ የነበረ ቢሆንም ኢትዮ ቴሌኮም ባገጠመው ችግር ተግባራዊ መሆን ባለመቻሉና በመጓተቱ ከንግድ ባንክ ጋር እየተሰራ መሆኑ እንዲሁም ክልሎች የህብረት ስራ ማህበራት ለህብረተሰብ በአግባቡ ስለማዳረሳቸው ክትትል እያደረጉ መሆኑና የሱፐርቪዥን ስራ የሚደረግ መሆኑ፣ገልፀዋል፡፡

46.የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ የቴሌ ብር ሺያጭ ሙከራ መደረጉ የሚያበረታታ ቢሆንም ሁሉም ፋብሪካዎችም ያልጀመሩ መሆኑ እና የስርጭትና የግብይት ሥርዓቱ የቴክኖሎጂ መረጃ አያያዝ

ስርዓትን መሰረት ያላደረገ በመሆኑና ሁሉም የሚሰሩ ስራዎች ለክትትልና ለቁጥጥር ምቹ በማድረግ ባለማዘመኑ እንዲሁም የመሰረታዊ ሸቀጦችም ከንግድ ባንክ እየተሰራ ያለው የማዘመን ስራ የሚያሳይ ማሰረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ እና ምርቶቹ ተደራሽ ማድረግ ላይም ክፍተት በመኖሩ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

47. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ዘመናዊ ባለማድረጉ በትክክል ህብረተሰቡ ላይ ተደራሽ ስለመሆኑ እንዳይታወቅ እና ችግሮችንና ክፍተቶችን በፍጥነት መፍታት ላይ ክፍተት የሚፈጥር ሆኗል፡፡

## ለ/ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት፣ ክፍፍል፣ አቅርቦት ለማከናወን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን መገምገም፤

**የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ከከተማ አስተዳደሮች እና ከክልሎች ጋር የጋራ እቅድ ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤**

49. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በማሳተፍ እና ከሚመለከታቸው አካላት መረጃ ሊሰበስብ፣ የጋራ እቅድ ሊያዘጋጅ እና የአፈፃፀሙን ውጤታማነት ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

50. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎቻቸ እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በማሳተፍና መረጃ በመሰብሰብ ላይ ክፍተት መኖሩ፤
- ከክልሎች ጋር በመሆን በዓመት ሁለቴ የክትትል ስራ እንደሚሰራ የተገልፀ ቢሆንም የሰኔ 2015 እና 2016 በጀት ዓመት የሱፐርቪዥን ሪፖርት ለኦዲት ቡድኑ የቀረበ ቢሆንም ከ2013 እስከ 2015 በጀት ዓመት በእቅዱ መሰረት ክትትል እና ቁጥጥር መደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የጋራ እቅድ እንዳላቸው የገለፀ ቢሆንም የ2013 እና የ2014 ዓ.ም በጋራ ስለመታቀዱ ማስረጃው ለኦዲተሮች ያልቀረበ መሆኑ እንዲሁም የ2015-2016 ዓ.ም የጋራ እቅድ ለሁሉም

ክልሎች የተሰጠ ተብሎ የቀረበውን የ2015 ዓ.ም የሰባት ክልሎች ብቻ የቀረበ ሲሆን የየትኛው ክልል መሆኑ የማይገልፅ መሆኑ፣ የ2016 ዓ.ም የዘጠኝ ክልሎች ብቻ የቀረበ ቢሆንም የስድስቱ ያልተፈራረሙበት መሆኑና የቀሩት የሶስቱም የማን ክልል መሆኑ የማይገልፅ መሆኑ፤

- በናሙና በተመረጡ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የጋራ እቅድ መኖሩ ተጠይቀው እንደሌላቸው የገለፁ መሆኑ እና በግብረ-ኃይል ኮሚቴ በየ45 ቀን በሚካሄደው ስብሰባ ላይ የጋራ እቅድ እንዲኖር ሃሳብ የሚያነሱ መሆኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፤
- የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከ2013 እሰከ 2015 በጀት ዓመት እቅድ ያልቀረበ መሆኑና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ከ2015 በጀት ዓመት ውጪ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የምርቶቹ ስርጭት የአፈፃፀም ውጤታማነት ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ አለመሆኑ፣
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስርጭት ዙሪያ የሚፈለጉ ማስረጃዎች ከፋብሪካዎቹ እና ከሚመለከታቸው አካላት በተፈለገው ጊዜና ጥራት ለማግኘት እየተቻለ አለመሆኑ፤
- የፍራንኮቫሉታ አስመጪዎቹ ምርት ከውጭ ሲያስገቡ መረጃቸው ጉምሩክ ባለስልጣን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በአብዛኛው ጊዜ የሚልክለት በየአስራ አምስት ቀኑ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱም የተላከለትን መረጃ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚላከው ተከታታይነትና ወጥነት የሌለው መሆኑ፤

  ይሄውም ነሃሴ 2014 ዓ.ም በቁጥር 01-1-18-1/10401፤ መስከረም፣ ጥቅምት፣ ጥር፣ የካቲት፣ ሰኔና ነሃሴ 2015 ዓ.ም በቁጥር 01-1-18-1/12338 እና ህዳር 7/2016 በቁጥር 0/-1-18/12735) ብቻ መሆኑ እና መረጃውም ለአዲስ አበባ፣ ለኦሮሚያ፣ ለሃረር፣ ለአፋር፣ ለአማራ፣ ለድሬዳዋ እና ለሱማሌ ክልሎች ብቻ የተላከ መሆኑ፤
- በተጨማሪም ለክልሎች የተላኩ ደብዳቤዎች የአስመጪዎች ብዛት፣ ያስገቧቸው የምርቶቹ ዓይነት እና መጠን የያዘች አንድ ገፅ አባሪ እንጂ ሙሉ አድራሻቸው/መረጃቸው የቲን ቁጥራቸውና ንግድ ፈቃዳቸው ጭምር ሙሉ አድራሻቸውና ወቅታዊ መረጃ እንደማይላክላቸው ምርቱ ከተሸጠ ብኃላ መረጃው የሚደርሳቸው መሆኑ፤

❖ የጉምሩክ ባለስልጣን መረጃ የፍራንኮቫሉታ አስመጪዎች ወደ ሀገር እናስገባለን በሚል የሚያሳውቁት መጠን እንጂ ያስገቡትን የምርት መጠን የማይታወቅና ወደ ሀገር ገብቶ ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ስለመሆኑ የማይረጋገጥ መሆኑ፤-

**ለማሳያ፡-**በ2014 ዓ.ም በፍራንኮቫሉታ ከውጭ ወደ ሀገር የገባ የዘይት መጠን ከጉምሩክ ባለስልጣን የተገኘው መረጃ 1,118,161,074 ሊትር ሲሆን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ የተገኘው ደግሞ 284,822,305 ሊትር መሆኑ በሁለቱም ያለው የመረጃ /የሊትር ልዩነት 284,822,305 ሊትር መሆኑ ተቀናጅቶ የመስራት እና ምርቱ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከስርጭቱ ድረስ አስመጪዎቹን ለይቶ የማወቅና የመከታተል ስራ ላይ ክፍተት መኖሩ፤

❖ የሲሚንቶ የስርጭት መረጃ ፋብሪካዎቹ ዘግይቶ እና አጠራቅሞ አንድ ላይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የመላክ ሁኔታዎች መኖራቸውና እያንዳንዱ የስርጭታ ሁኔታና ሂደቶች እንዳይታወቅ ማድረጉ፤

❖ ፋብሪካዎቹ አከፋፋዮች መርጠው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሚልኩ ቢገለፅም ለመከታተል በሚያመች መልኩ አስፈላጊ መረጃዎችና አድራሻዎች ተሟልተው የማይላክ መሆኑ፤ ይሄው መረጃ ለክልሎች የሚላክ በመሆኑ ክልሎቹ ተመረጡ የተባሉትን አከፋፋዮች የማያውቋቸው እና የማይቆጣጠሯቸው መሆኑ፤ አከፋፋዮቹና ቸርቻሪዎቹ ዝርዝር ለሁሉም ክልሎች ስለመላኩ የተሟላ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

51.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው የማጠቃለያ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ክልሎች በስርጭት አፈጻጸም የሪፖርት ቅብብሎሽ፣ በሩብ፣ በግማሽ እና በዓመት የጋራ መድረክ ግምገማ መኖሩ፤ የ2013 እና 2014 ዓ.ም የክፍሎች ዕቅድ እና አፈጻጸም ሪፖርት መኖሩ፤ የክልል ሱፐርቪዥን ስራዎች ሪፖርት 2014፣ 2015 እና የ2016 በጀት ዓመት ሰነድ ያቀረቡ መሆኑ እና በየዓመቱ ከክልሎች ጋር የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀትና በመፈራረም ወደ ስራ የሚገባ መሆኑን እንዲሁም በጥቅምት 2016 ዓ.ም የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከፌደራል ኅብረት ስራ ኮሚሽን እና ከኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በመቀናጀት የተዘጋጀ የግብርና የምግብ ምርቶች የአቅርቦት ሰንሰለት አስተዳደር ስርዓት መኖሩን ገልፀዋል፡፡

52. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የሰኔ 2015 እና 2016 በጀት ዓመት የሱፐርቪዥን ሪፖርት እንጂ ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም በዓመት ሁለት ጊዜ ተደረገ የክትትል ባለመቅረቡ፣ የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከ2013 እስከ 2016 በጀት ዓመት እቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ከ2015 በጀት ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት የተወሰኑ ክልሎች ውጪ ማስረጃዎቹ ባለመቅረባቸው፣ የጋራ እቅዶች የ2013 እና የ2014 ዓ.ም ማስረጃዎቹ ባለመቅረባቸው፣ የ2015 እና የ2016 ዓ.ም ከቀረቡት የጋራ እቅዶች ክልሎች ያልፈረሙበት እና የማን ክልል መሆኑ የማይገልፅ መሆኑ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በጥቅምት 2016 ዓ.ም ተዘጋጀ የተባለው ለወደፊቱ ጥሩ ቢሆንም ከላይ ለተጠቀሰው ግኝት ምላሽ ባለመሆኑ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

53. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በማሳተፍ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በእቅዱ መሰረት በዓመት ሁለት ጊዜ ክትትልና ቁጥጥር ባለማድረጉ፣ ከክልሎችና ከ/አስተዳደሮቹ ኃላፊነትና ተጠያቂ ያለው ጠንካራ የጋራ እቅድ ባለማዘጋጀቱ፣ እና የክልሎችና የከ/አስተዳደሮቹ እቅድና የፈፃፀም ሪፖርቶች ልውውጥ ክፍተት በመኖሩ በዓመቱ የሚከሰቱ ክፍተቶች ለመለየት አስቸጋሪ እንዲሆን እና ወቅታዊ በሆነ መልኩ የአፈፃፀሙን ውጤታማነት ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዳይቻል ያደርጓል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከግብረ ኃይል ኮሚቴው ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፡**

54. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወርሃዊ፣ የሩብ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ እቅዶችንና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለግብረ ኃይል ኮሚቴና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያቀርብ፣ መደበኛ የጋራ ውይይት፣ የግምገማና ግብረ-መልስ እንዲኖር ሊያደረግ እና የሲሚንቶን መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን በቅንጅት ሊሰራና ሳይቆራረጥ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

❖ የግብረ ኃይል ኮሚቴው ከሚሰራቸው ስራዎች ውስጥ የኮንትሮባንድና ህገ-ወጥነትን መከላከል፣ የአምራቶች የማምረት አቅማቸውን ማሳደግ፣ የምርቶች አቅርቦት እንዲጨምር ማድረግ፣ ገበያው ማረጋጋትና ህብረተሰቡ ከኑሮ ውድነት መታደግ፣ መሠረታዊ ሸቀጦች በልዩ ትኩረት ሳይቆራረጥ እንዲቀርብ ማድረግ፣ ከፍራንኮቫሉታ ጋር መድረክ መፍጠርና በቅርበት መወያየት፣ ከአምራቾችና ከአስመጪዎች ትስስር በመፍጠር ለሕብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያቀርቡ ማድረግ እና ወዘተ ሲሆን በእቅድ መመራት ላይ ክፍተት መኖሩ፣ ውይይቶችና ግምገማዎች በማድረግ ጥረቶች እንዳሉ ቢገለፅም ከኑሮ የውድነት እና ከምርቶች አቅርቦት አንፃር የሚፈለገውን ውጤት እያመጣ አለመሆኑ በግብረ ኃይል ኮሚቴው ከቀረቡ ማስረጃዎች ጭምር እና በሚመለከታቸው አካላት የተገለፀ መሆኑ፤

ለማሳያ፡-

- ✓ መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ገበያውና አቅርቦቱ ቀጣይነት እንዲኖረው እና ህጋዊ ሽያጭ/በደረሰኝ እንዲሆን አለማድረግ፣ ገበያው ከነጋዴዎችና ደላሎች ነፃ ስለመሆኑ በየጊዜው ክትትል አለማድረግ፣ ሌሎች ነጋዴዎች ምርቶቹ በቅናሽ እየገዙ በውድ የሚሸጡ ነጋዴዎች መኖራቸው እና የአቅርቦት ከፍተኛ እጥረት መኖሩ፤ አምራቹ እና ሸማቹ በቀጥታ የሚገበያዩበት መንገድ ወጥ በሆነ እና በተዘረጋ ሥርዓት የሚመራ አለመሆኑና ለህገ ወጥ የንግድ ተዋንያን ጣልቃ ገብነትና የአየር በአየር ንግድ የተስፋፋ በመሆኑ ምርቶች ሸማቹ ጋር ሲደርሱ መሸጥ ከሚገባቸው ዋጋ በላይ እየገዛ መሆኑ እና ጥረቶች ቢኖሩም ቀጣይነት ባለው ችግሮቹ እየተፈቱ አለመሆኑ፤
- ✓ ከ2012 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ እየባሰ የመጣው በገበያ ላይ ያለው የሲሚንቶ ስርጭት የዋጋ ንረትና በፋብሪካዎች አካባቢ ከፍተኛ የአቅርቦት ችግር መኖሩ፣ ግብይቱና ሰንሰለቱ ውስጥ ባሉ ህገ ወጥ ተዋንያን ያልተገባ የግብይት ሂደት መኖሩ (ያለደረሰኝ ሽያጭ፣ ዋጋ ማናርና ወዘተ.)፣ ቸርቻሪዎች በህገ-ወጥ /ከደላላ ውጪ ምርቱ ማግኘት አለመቻላቸው፣ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን በሲሚንቶ ፋብሪካዎቹ የማይተገበር መሆኑ፤ ግብይቱ መፍትሄ ያልተገኘለት እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከተው አካል በመሆን ችግሩን የሚፈታበት ስርዓት

ያልዘረጋ መሆኑ በተከለሱ ማስጃዎች በቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤

- የግብረ ኃይል ኮሚቴው ከ2014-2016 ዓመታዊ እቅዶች፣ የ3 ወራት እስከ ነሐሴ 15/ 2015 ዓ/ም የተጠቃለለ ሪፖርት፣ የመስከረም 2016 ዋና ዋና ተግባራት እና በ2014 ዓ.ም አካላዊ ምልከታ ለማድረግ የተዘጋጀ ቼክ ሊስት ለኦዲት ቡድኑ ቢቀርብም ከ2013 እስከ 2015/2016 የአፈፃፀምና የክትትል ሪፖርቶች እና ከክልሎችና ከሚመለከታቸው አካላት የግብረ ኃይል ኮሚቴ በየሳምንቱ የሚላከው የአፈፃፀም ሪፖርት እና የተጠቃለለ ዓመታዊ የእቅድ አፈፃፀም ማስረጃዎች ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የወርሃዊ፣ የሩብ፣ የግማሽ ዓመት እና ዓመታዊ እቅዶችንና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የሲሚንቶና መሰራዊ ሽቀጦች ላይ ለሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት (ለምሳሌ ማዕድን ሚ/ር፣ ብሄራዊ ባንክ፣ ገቢዎች፣ ጉምሩክ ባለስልጣን) እና ለግብረ ሀይል ኮሚቴው የማያቀርብ መሆኑ እና የጋራ ግኑኝነት ላይም ክፍተት መኖሩ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ ግምገማ እንደሚሳተፉ እና የግብረ ሀይል ኮሚቴው እቅዶች ለክልሎች እንደሚልክ ቢገልፅም ይህንን የሚያሳይ ማስረጃዎች ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረቡ መሆኑ፤
- ከክልሎች ጋር በየሶስት ወሩ ግምገማ እንደሚካሄድ ቢገለፅም ከ2013 እስከ የ2015/2016 በጀት ዓመት በየሶስት ወሩ የሚደረገውን የግምገማ ሪፖርት/ቃለጉባዔ የተሟላ ማስረጃ እና ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጥነት ያለው የግብረ-መልስ ስርዓት ስለመዘርጋቱ የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

56.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው የማጠቃለያ መጠይቅ እና በነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ

- ከ2013 እሰከ 2016 የግብረ-ኃይል እቅድ፣ የዋጋ ግሽበት የ3 ወራት እስከ ነሐሴ15/ 2015 ዓ/ም የተጠቃለለ ሪፖርት እና በ2014 ዓ.ም አካላዊ ምልከታ ለማድረግ የተዘጋጀ ቼክ ሊስት፣ የግንቦት 2015 የኑሮ ውድነት ማቃለያ የድርጊት መርሀ ግብር፣ በ17/12/2013 ዓ.ም በህገ-ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር በፌደራል ደረጃ የተቋቋመው ግብረ-ሀይል  የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ

እና በግንቦት 2015 ዓ.ም የምግብና የምግብ ነክ ምርቶች አስመጪዎች የውይይት መድረክ የጥሪ ደብዳቤ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ የቀረበ መሆኑ፤

- ❖ ከ8.09 ቢሊዮን ብር በላይ በተመቻቸ የተዘዋዋሪ ፈንድ/ብድር ሕብረት ሥራ ማህበራት በተፈጠረ የገበያ ትስስር ምርት እንዲያቀርቡ የተደረገ ድጋፍ፣ ዝቅተኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ያደረጉ እንደ ሀገር የተደራጁ 913 የሰንበት ገበያ ማዕከላት እንዲኖሩ መደረጉ፤
- ❖ የህገ ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድ ቁጥጥር እና ደላላን ከንግድ ሰንሰለቱ የማስወጣት ሥራዎች፣ በፍራንኮቫሉታ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀዱ 5 ምርቶች፣ የግብረ ሀይሉ እንቅስቃሴ የኑሮ ውድነቱን ማረጋጋት የተሰራ ስራ እና የኑሮ ውድነቱ ጫና መንስዔዎች ዓለም አቀፋዊ ጭምር ስለሆነ እና የብዙ አካላትን ተሳትፎ ጭምር የሚጠይቅ በመሆኑ ውጤቱም በሀገራዊና በዓለማቀፋዊ መለኪያ ቢታይ እንዲሁም ከክልሎች ጋር የጋራ ዕቅድ እንዳላቸው ማስረጃውን ለኦዲተሮቹ ማቅረባቸው ገልፀዋል፡፡

57.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የግብረ-ኃይል ኮሚቴው በኑሮ ውድነትና በኮንትሮባንድ ያሉት ክፍተቶች ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶች የሚያበረታታ ቢሆንም የ2013 ዓ.ም የአራት የንግድ ተቋማት የንቅናቄ እቅድ፣ ከ2014 እስከ 2016 የግብረ-ኃይል እቅድ፣ በዋጋ ግሽበት ላይ የተሰሩ ስራዎች የ3 ወራት እስከ ነሐሴ 15/ 2015 ዓ/ም የተጠቃለለ ሪፖርት፣ የመስከረም ዋና ተግባርት 2016 ሪፖርት እና በ2014 ዓ.ም አካላዊ ምልከታ ለማድረግ የተዘጋጀ ቼክ ሊስትና ከሰኔ 14-27 የተደረገ ክትትል፤ የግንቦት 2015 የኑሮ ውድነት ማቃለያ የድርጊት መርሀ ግብር፣ በ17/12/2013 ዓ.ም በህገ-ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር በፌደራል ደረጃ የተቋቋመው ግብረ-ሀይል የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ማስረጃዎች ለኦዲት ቡድኑ ቢቀርቡም በእቅዱ መሰረት በመደበኛ ቀጣይነት ባለው መልኩ የተሰሩ ስራዎች እና የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶች ማስረጃዎች የክልሎችና የሚመለከታቸው አካላትም ጭምር ዓመታዊ እቅዶች እና በየሳምንቱ ከክልሎች የሚላኩ ሪፖርቶች እና የተጠቃለለ ዓመታዊ የአፈፃፀም ሪፖርቶች ያላቀረቡ በመሆኑ እና

- ❖ ከ8.09 ቢሊዮን ብር በላይ በተመቻቸ የተዘዋዋሪ ፈንድ/ብድር ሕብረት ሥራ ማህበራት በተፈጠረ የገበያ ትስስር ምርት እንዲያቀርቡ የተደረገ ድጋፍ መቼና የተሰራውን ስራ የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ፣ እንደ ሀገር የተደራጁ 913 የሰንበት ገበያ ማዕከላት አፈፀፀማቸው ዝቅተኛ በመሆኑ፣ የሌላቸው ክልሎች መኖራቸው (አፋር ክልል) እና ግብይቱ ላይም ክፍተት በመኖሩ፣

የሰንበት ገበያው የክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አፈፃፀማቸው 44 በመቶ መሆኑ ለማሳያ ቤንሻንጉልና ጋምቤላ 3፣ ሱማሌ 9፣ አማራ 15፣ ሃረሪ 23 እና ሲዳማ 35 በመቶ መሆኑ፤ ከሚመለከታቸው መዋቅሮች እና ምርቱ ከሚያቀርቡ (ህብረት ስራ ዩኒየኖች፣ ፋብሪካዎችና አስመጪዎች) በቅንጅት ባለመስራቱ፤

- ❖ እንዲሁም በሀገር ውስጥ የሚመረት ምርትም ሆነ ከውጪ ሀገር የሚገባው ከአቅራቢው እስከ ሸማቹ ድረስ ሁሉን የህብረተሰብ ክፍል የሚያሳትፍ፣ ግልጽ እና የሚታወቅ የገበያ ትስስር ባለመደረጉ የተሰጠ ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

58.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅዶችንና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለግብረ ኃይል ኮሚቴና ለሚመለከታቸው አካላት በማቅረብ በእቅዱ መሰረት የተሰሩ ስራዎች እንዲልኩ ባለመደረጉ፣ መደበኛ ግብረ-መልስ ባለመኖሩ እና የቅንጅት ስራው ክፍተት በመኖሩ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት እየተቆራረጠ የሚቀርብ በመሆኑ ህብረተሰቡ በጥቁር የውጭ ምንዛሪ እና በጥቁር ገበያ በውድ በሚገባ ምርት እንዲሸምት አድርጎታል፡፡

**ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችን በጥናት መለየቱን በተመለከተ**

59.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስርጭቱ ሁኔታ እና የገበያ ፍላጎት የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ የመሰረታዊ ሸቀጦች ጥናት በማጥናት ለሚኒስትሮች ም/ቤት ሊያቀረብ እና ዝርዝራቸውንና ዋጋቸውን በሕዝብ ማስታወቂያ (በሚድያ) የዋጋ ሊያሳወቅ እና ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

60.ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎቻቸው እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስንዴ ምርት ከመሰረታዊ ሸቀጥነት እንዲወጣ ወይም እንዲካተት ለማድረግ ተገቢውን ጥናት ስለማከናወኑ ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤ ስንዴ ከመሰረታዊ ሸቀጥነት መውጣት እና በነፃ ገበያ መገበያየት ቢኖርበት እንኳን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ይህን የመሸከም አቅም ስለመኖሩ፣ አቅም የሌላቸውን ለመደገፍ የሚያስችል ቅድመ

ዝግጅት እና ችግራቸውን ለመቅረፍ የሚያስችል ዕቅድ በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል ያላቀረበ መሆኑ፤

- የዱቄት እና የስንዴ ግብአት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ ምርቱ ማግኘት ባለመቻላቸው ስራ እያቆሙ መሆኑ፤ ለምሳሌ ድሬዳዋ 11 እና በአዲስ አበባ ከ300 ፋብሪካዎች ከ2013 ዓ.ም በፊት ትስስር ተደርጎላቸው ለህብረተሰቡ ምርቱ ሳይቆራረጥና በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ የነበረ ቢሆንም ትስስሩም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የተቋረጠ መሆኑ 28 የሚሆኑ ፋብሪካዎች የቀሩ መሆኑ፣
- የኢትዮጵያ የዱቄትና ውጤቶቹ ማህበር፣ ፋብሪካዎቹ፣ ከተማ አስተዳደሮቹ እና ክልሎች የነበረው ትስስር በሃገር ውስጥ ምርት እንዲቀጥል ወይም ፋብሪካዎቹ በግላቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች እና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያቀርቡ በደብዳቤዎችና በየመድረኩ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርቡም መልስ ያላገኙ መሆኑ፤
- የመሰረታዊ ሸቀጦችን ለማቅረብ ፍራንኮቫሉታ ገበያን እንዲያረጋጋ ተብሎ ቢፈቀድም በጥናት የተመሰረተ አለመሆኑ፣
- ምርቶች በየደረጃው ግብይት ሲፈጸምባቸው በተለይም የመሰረታዊ ሸቀጦች ሽያጭ የሚፈጽሙ የንግዱ ተዋንያን በምርቶቻቸው ላይ ዋጋ ለጥፈው እንዲሸጡ የሚያስችል ወጥ የሆነ አሰራር አለመዘርጋት እና ዋጋቸው በሚድያ እንዲታወቅ እየተደረገ አለመሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

61. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ

- መሰረታዊ ሸቀጦች ውስጥ ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት ያለው እና በገበያ የማይገኙው ከመሰረታዊ ሸቀጥ አንዱ ዘይት ሲሆን የዘይት ምርት በገበያ ላይ በበቂ መጠን የሚገኝና ዋጋውም ተመጣጣኝ በመሆኑ በመንግስት እየቀረበ የሚገኘው የዘይት ምርት ክልሎች ለማንሳት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ፋብሪካዎች እያሳወቁ መሆኑ እና የአለም ዋጋ ተለዋዋጭነትን ድፍድፍ ዘይት የሚያስገቡ ፋብሪካዎች የማምረት ሂደቶች ውስጥ የአለም ዋጋ ሲቀንስ የግል አስመጭዎች ዝቅ ባለ ዋጋ ለገበያ ሊያቀርቡ የሚችሉበት ወቅት ሊያጋጥም የሚችል መሆኑ፤

- የስኳር ምርት በሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች የማምረት አቅም መቀነስና በአለም ገበያም በተለያዩ ምክንያቶች የአቅርቦት ውስንነት በመኖሩ ምክንያት በፍራንኮቫሉታ የሚገባው ምርት ጭምር የዘይት ያህል በበቂ መጠን ገበያው ላይ ያለመገኘት ችግር መኖሩና ይህንን ችግር ለመፍታት የስኳር ኢንዱስትሪ ጉሩፕ የሀገር ውስጥ የማምረትና የማሰራጨት አቅም እንዲጨምርና ከውጭ ማስገባት እንዲችል ጥረቶች እየተደረጉ መሆኑ፣
- የስንዴ ምርት ምርታማነት ለመጨመር በተያዘው ዕቅድ ከሀገር ፍላጎት በተጨማሪ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተሰራ በመሆኑ የውጭ ምንዛሪ በመመደብ ድጎማ በማድረግ ይቀርብ የነበረው በሀገር ውስጥ እንዲተካ የአቅርቦት ውሳኔ በማክሮ ደረጃ የሚታይ እና አቅጣጫ የሚቀመጥ መሆኑ ከግምት ውስጥ ቢወሰድ በማለት ገልፀዋል፡፡

62. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ መሰረታዊ ሸቀጦች (ስንዴ፣ ስኳርና ዘይት) ከፍተኛ የገበያ ፍላጎትና ህብረተሰቡ የመግዛት አቅም አንፃር በገበያ በተመጣጣኝ ዋጋ እየተገኙ ስለመሆኑ ጥናትን መሰረት ያደረገ ማስረጃ ያላቀረቡ መሆኑ፣ በመንግስት የድፍድፍ ዘይት ዓላማው ገበያው ካለው ዋጋ በቅናሽ ማቅረብ ቢሆንም እየቀረበ የሚገኘው የዘይት ምርት የዓለም ገበያ ዋጋ በሚረጋጋበት ወቅት ጥናት እየተደረገ ግዥ ባለመፈፀምና የቅንጅት ክፍተት በመኖሩ ምክንያት በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ እና ገበያ ካለው ዋጋ ከፍ በሚልበት ወቅት ህብረተሰቡ ከመግዛት አቅሙ አንፃር ዋጋ የሚቀንሰውን የሚገዛ በመሆኑ ፋብሪካዎችም መስራት አለመቻላቸው፣ እንዲሁም የሱማሌ ክልል በፃፈው ደብዳቤ የፋብሪካው ዘይት በብር 126.40 ገበያው ካለው ዘይት በሚበልጥ ዋጋ የቀረበ በመሆኑ ሕብረተሰቡ ላይ ምርቱን ለመግዛት አቅሙን እየተፈታተነው በመሆኑ፣

63. የስኳር ምርት ከውጭ ለማስገባት የስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ በተደጋጋሚ የጠየቀ ቢሆንም እስከ 2016 ዓ.ም ድረስ ምርቱ ወደ ሃገር እንዲገባ ያልተደረገ መሆኑ፣ የስንዴ ምርት ከፍተኛ ፍላጎትና አቅርቦት እና የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም የሚታወቅ በመሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስንዴ/በዱቄት የተቋረጠው የትስስርና ሰንሰለት እና የአቅርቦት ክፍተቱ በጥናት ለይቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት በማቅረብ የድርሻው ስራ ባለማወጣቱ ህብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ መምጣቱና የመግዛት አቅሙን እያዳከመ በመምጣቱ እና መግዛት የማይችል በርካታ ዜጋም መኖሩ በቀረቡ ማስረጃዎች እና ክልሎችና ከተማ

አስተዳደሮች፣ ዞኖችና ከተሞች የገለፁ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

64. የስንዴ ምርት ከፍተኛ ፍላጎትና አቅርቦት እጥረት መኖሩ እና የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ከፍተኛ ልዩነት በመኖሩ እንዲሁም ስንዴ/ዱቄት በመንግስት ድጎማ እየቀረበ የገበያ ጉድለት ይሞላ የነበረው ምርት፣ ትስስርና ሰንሰለት እና አቅርቦት የተቋረጠውን ሚኒስቴር መ/ቤቱ ትስስሩ በሃገር ውስጥ ምርት እንዲቀጥል እና የገበያ ክፍተቱ በጥናት ለይቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ባለማቅረቡ ዝቅተኛ ገቢ ያለው ህብረተሰቡ የመግዛት አቅም በመፈተን ሸቀጦቹን ገዝቶ መጠቀም እንዳይችል አድርጓል፡፡

**መሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦትና ሥርጭት ላይ የሚደረጉ ድጋፎችን በተመለከተ፣**

65. ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦች በልዩ ሁኔታ ጊዜውን ጠብቀው በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ድጋፍ (የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት) እንዲያገኙና ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ወዘተ) ማድረጉን፣ አፈፃፀሙ ሊከታተል፣ አስፈጻሚ አካላትን እና ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሃገር ውስጥና የውጭ ተቋማት ሊያስተባብር፣ ግንኙነት ሊመስርት እና የቅንጅት ስራን ሊየጠናክር ይገባል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- መሰረታዊ ሸቀጦች በልዩ ሁኔታ በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረብ እንዲችሉ ከአስፈጻሚ አካላት (ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ብሄራዊ ባንክ፣ ንግድ ባንክ፣ ገቢዎች ሚ/ር፣ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ወዘተ የቅንጅት ስራው የተጠናከረ አለመሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ አሁን ካለው የዓለም አቀፍ ነባራዊ ክስተተት ጋር ተያይዞ የምግብ ዘይት ዋጋ አሁን ካለበት የመግዣ ዋጋ ከሚጠበቀው በላይ እየናረ የመጣ መሆኑ እና በሌላ አማራጭ ለውጪ ገበያ የሚቀርቡ የቅባት እህሎችን (ሱፍ፣ ሰሊጥ፣ ወዘተ) በጥናት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ የተወሰነውን መጠን በማስቀረት እና ሀገር ውስጥ ባሉ በአነስተኛ፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ፋብሪካዎች በቀላሉ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉና

እንዲያመርቱና ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ እንዲያገኙ እያመቻቸ/እያስተባበረ አለመሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎችና በቃለ-መጠይቆች የተገለፁ መሆኑ፤

ለምሳሌ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዝያ 2014 ዓ.ም ባጠናው ጥናት የዘይት ፋብሪካዎች ወደ ውጪ ከሚላከው የተወሰነው መጠን የቅባት እህሎች እንዲያገኙ ቢደረግ እስከ ሚያዝያ 2014 ዓ.ም እንኳን 300,000,000 ሊትር ዘይት ሊያመረቱ ይችሉ እንደነበረ የዋጋ ንረቱና የምርት እጥረቱ በቀጣይነት ይረጋጋ እንደነበረ በጥናቱ ቢገለፅም ጥናቱ ወደተግባራ ለመቀየር የሚያስችል ስራ አለመሰራቱና ድጋፍ እንዲያገኙ አለመደረጉ፤

- በአሁን ወቅት የምርቶቹ ከፍተኛ የፍላጎት እና አቅርቦት ልዩነት ለመሸፈን በአብዛኛው የሚሆን ድርሻ (95 በመቶ) በየጊዘው በሚወሰን በቀረፅ ነፃ ፍራንኮቫሉታ አስመጪዎች እንዲሸፈን የታቀደ ቢሆንም የህብረተሰቡ ለግብይት ችግሮች (ለአቅርቦት እጥረት፣ ለዋጋ ንረት) ወዘተ ያልተፈታ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎችና እና በቃለ-መጠይቆች መገለፁ፤
- አስመጪዎች/ አምራችና አቅራቢ ድርጅቶች/ የመሰረታዊ ሸቀጦች ጊዜውን ጠብቀው በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱን ለህብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ድጋፍ /የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን እንዲያገኙ ከማድረግ ጀምሮ ምርቱ ወደ ሃገር እስኪገባ ድረስ የክትትል ክፍተት መኖሩ እና ዶላር ተፈቅዶላቸው የድፍድፍ ዘይት የሚያስገቡ ፋብሪካዎችም የብሄራዊ ባንክና ጉምሩክ ባለስልጣን ተናብቦ የመስራት ክፍተት በመኖሩ ምርቶቹ ዘግይቶ የሚገቡ መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እና ቃለ-መጠይቆች የተገለፀ መሆኑ፤

  ለምሳሌ ከውጪ የሚመጣ በሃገር ውስጥ የሚመረት ድፍድፍ ዘይት ለበርካታ ወራት (እሰከ 2015 ግማሽ ዓመት አከባቢ ባለው በአማካይ እሰከ 8 ወር ድረስ) እየቀረበ እንዳልነበረ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዓመት የውጭ ምንዛሬ እንዲመደብላቸው ካደረገ በኋላ የማይከታተል መሆኑ፤
- ምርቶቹ ከውጪ ሀገር ሲገቡ /በመንግስት ድጋፍ ከሚገቡ ለምሳሌ የድፍድፍ ዘይት በመስከረምና ጥቅምት ወቅት የዓለም አቀፍ ገበያ በሚረጋጋበት ወቅት በርከት አድርጎ ለማስገባት እንደሃገር ታስቦበት ዶላር የማይፈቀድላቸው መሆኑ፤ በአንፃሩ በመጋቢትና በሚያዝያ የዓለም አቀፍ ገበያ በሚንርበት ወቅት ሲፈቀድ የምርቱ መጠንና ዋጋ ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ እያሳደረ በመሆኑ

እና ከሌላ የገበያ ዋጋ ጋር ተመሳሳይ ወይም ከፍተኛ በሚሆንበት ወቅት አከፋፋዮችና የመንግስት ልማት ድርጅቶች (የኢንዱስትሪ ግብአቶች ድርጅት) ጭምር ምርቱ /ዘይቱ ከፋብሪካዎች የማይገዙ/ የማያነሱ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎችና ቃለ-መጠይቆች መገለፁ፤

❖ የመሰረታዊ ሸቀጦች(ዘይት) ላይ የውጪ ምንዛሪ እንዲያገኙ ድጋፍ የተሰጣቸው ፋብሪካዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ያለመ ቢሆንም በገቢያ ላይ ያለው የዋጋ ልዩነት ተመሳሳይና አልፎ አልፎም ገበያ ካለው ምርት ዋጋ የሚጨምር በመሆኑ ህብረተሰቡ ቅሬታ እያስነሳ መሆኑ፤

<u>ለማሳያ፡-</u>

- የተከማቸ የዘይት ሽያጭ በተመለከተ በህዳር 2015 በቁጥር 01-1-18-10824 ለፌበላ፣ ለሸሙ፣ ለሐማሬሳ እና ለአል ኢምፔክስ ፋብሪካዎች በተፃፈ ደብዳቤ የዓለም ዋጋ በከፍተኛ ዋጋ ጨምሮ በቶን 1900 ዶላር ገዝቶ ያመረቱት ምርት በህዳር 9/2015 ዓ.ም የዓለም ዋጋ በቶን ወደ 1200 ዶላር በመቀነሱ በውድ በተገዛ ድፍድፍ የተመረተው ዘይት የመሸጫ ዋጋ ከገበያ ካለው ዋጋ በመጨመሩ አምስት ሚሊየን (5,000,000) ሊትር ዘይት የሚጠጋ የተመረተ ዘይት ያልተነሳ/ያልተሰራጨ/ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች መኖሩ፤
- በሱማሌ ክልል በጥር 2016 በቁጥር ኤክስጂጂ/044129/16 ከፋብሪካዎች የመጣ ዘይት ካለው የገበያ ዋጋ በ126.40 የሚበልጥ በመሆኑ መፍትሄ እንዲሰጥ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፃፈ ደብዳቤ የሚያሳይ መሆኑ፤

❖ የዘይት አምራች ፋብሪካዎች የራሳቸውን ጥሬ እቃ/ግብዓት አምርተው መጠቀም እንዲችሉ እና የፓልም ዘይት ተክሉ በሀገር ውስጥ በመትከል የውጭ ምንዛሪ የሚያስቀርና ምርቱ በበቂ እና በተፈለገው ጊዜ እንዲደርስ ይቻል የነበረ ቢሆንም ከሚመለከታቸው ዘርፎች ጋር በመሆን በእቅድ ተይዞ መስራትና ከመንግስት የውጭ ምንዛሪ ጠባቂነት እንዲሻገሩ ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑ እና የፓልም ተክል ሃገር ውስጥ ለመትከል ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ውይይት ከተደረገ የቆየ ቢሆንም በቅንጅት መስራት ላይ ክፍተት መኖሩ፤ ከተከለሱ ማስረጃዎችና በቃለ-መጠይቆች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤

❖ የመሰረታዊ ሸቀጦች ከቦታ ቦታ ምርቶች እንዲዘዋወሩ የኬላ አሰራር ጋር ተያይዞ የሚጠየቁ የኬላ ክፍያዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን

እንዲቀንሱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ደብዳቤ ቢፅፍም በቅንጅት ተናቦ መስራት ላይ ክፍተት መኖሩ፤

- ❖ የፋብሪካዎችን የመሸጫ ዋጋ እንዲሁም በተዋረድ በግብይት ሰንሰለቱ ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገም ማስተካከያ በማድረግ የተረጋጋ፣ ተደራሽ እና ወጥ የሆነ የግብይት ሥርአት እንዲኖር ለማስቻል የሚረዱ ተግባራትን ከዘርፉ ተዋናዮች ጋር በቅርበት፣ በትብብር እና በቅንጅት የሚሰሩ ስራዎች ላይ ክፍተት መኖሩ፤
- ❖ ገበያ የማረጋጋትን ስራ ከክልሎች ጋር የሚገናኙበት ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፤ በቅንጅት ለሚሰሩ ሥራዎች ወጥ የሆነ እና ቅደም ተከተል ያለው ስራ እየተሰራ አለመሆኑ እና በደራሽ ሰራዎች የሚጠመዱ መሆኑ እንዲሁም የህብረተሰቡ ተጠቃሚነትም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- ❖ የኦዲት ቡድኑ ለስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ ባደረገለት ቃለ-መጠይቅ እና በመጋቢት 1/2014 በቁጥር 01/5303/435 ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ በ2013 ዓ.ም በሃገር ውስጥ ባጋጠመው እጥረት ለመሙላት ከውጭ በግዢ ለማስገባት በእቅድ ከተያዘው 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ሜትሪክ ቶን) 100,000 (አንድ መቶ ሺ ሜትሪክ ቶኑ) ስኳር በማይክሮ ኢኮኖሚ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት Lc at site ሆኖ የውል ማሻሻያ ተደርጎ ኤል.ሲ ለመክፈት ብድር ቢጠይቁም ንግድ ባንክ ያልፈቀደ መሆኑ፤ 100,000 (አንድ መቶ ሺ ሜትሪክ ቶን) የስኳር ምርት ግዥ የተፈፀመው 2013 ዓ.ም ቢሆንም በ2014 በጀት ዓመት የተሰራጨ መሆኑ፤ በ2014 እና 2015 ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርቱ ክምችት እንዳለቀ/ እንደሌለ በተደጋጋሚ ቢጽፉም የትብብር ድጋፍ ባለማግኘቱና ግዢ ሳይፈፀም የቀረ መሆኑ እና የስኳር እጥረት መከሰቱ የተገለፀ መሆኑ፤
- ❖ እንዲሁም የጉዳዩ አሳሳቢነት ታውቆ መፍትሄ እንዲደረግለት በድጋሜ በታህሳስ 18/2014 በቁጥር 01/3622/341 እና የካቲት 28/2014 በቁጥር ማዘ/0877/14 በተፃፉ ደብዳቤዎች እና በ2014 በጀት ዓመት እጥረቱ እንዳይቀጥል የተያዘው 100,000 ሜትሪክ ቶን ግዢ ሳይፈፀም መቅረቱ፣ የነበረው የስኳር ምርት ከአንድ ወር ጥቅም በላይ የማያስኬድ መሆኑ የባሰ ክፍተት ሳይፈጠር አስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጥና በተለየ ሁኔታ አስቸኳይ ግዢ እንዲፈፀም ጠይቀው የነበረ ቢሆንም ሳይገዛ የቀረ መሆኑ፤

- በ2014 በጀት ዓመትም የስኳር ፍላጎት 10 ሚሊዮን ኩንታል የነበረ ቢሆንም የተሰራጨው 250,143 ቶን (2.5 በመቶ) መሆኑ፤ በ2015 በጀት ዓመት በሚኒስቴር መ/ቤቱ የስኳር ምርት የውጭ ምንዛሬ እቅድ ተይዞ በአነስተኛ መጠን የስኳር ፍላጎት ለሚሟላት 300,000 ቶን እንደሚያስፈልግ እና ከውጭ እንዲገዛ አቅዶ የነበረ ቢሆንም ያልተከናወነ መሆኑ፤
- ከ2013/2014 ዓ.ም ጀምሮ የመሰረታዊ ሸቀጦች ምርት ቀጣይነት ባለው መልኩ (ሳይቆራረጥ) ለህብረተሰቡ እየቀረቡ አለመሆኑ እና አፈፃፀሙ ላይ የሚደረገው ክትትል አነስተኛ መሆኑ፤
- በአማራ ክልል የሚቀርበው ስኳር በፀጥታ ምክንያት ዩኒዮኖቹ ለተጠቃሚው ማቅረብ ያልቻሉ መሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥር 2016 ዓ.ም በተደረገው በክትትል ሪፖርት ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- በመሰረታዊ ሸቀጦች አከፋፋዮች ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣው መመሪያ ከ 3-5 የትርፍ ህዳግ ተጠቅሞ እንዲሸጡ የሚያዝ ቢሆንም ገቢዎች ሚኒስቴር ደግሞ ከዋጋ በታች እየሸጣችሁ ነው በማለት ቅጣት የሚቀጣ መሆኑ፣ ሁለቱም ተቀናጅቶ የጋራ የአሰራር ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑን አከፋፋዮች በተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ የገለፁ መሆኑ፤
- በሀገር ውስጥ የተመረተውን የስንዴ ምርት ነጋዴው በመግዛት ምርቱን ወደ ጥቁር ገበያ ውስጥ በማስገባት የመሸጥ ስራ እየሰሩ መሆኑ፤ የምርቱ አቅርቦት መስተጓጎል እና ያልተገባ ከፍተኛ ዋጋ መጨመሩ ለምሳሌ በ2014 ዓ.ም ብር 3500 ለአንድ ኩንታል የነበረ ሲሆን በ2015 ዓ.ም ብር 7500 መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

67.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ

- የዓለም አቀፍ የምግብ ዘይት ዋጋ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ምክንያቶች የሚዋዥቅ መሆኑና የአቅርቦቱ ሁኔታም የውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ወቅቱን ጠብቀው ግዢ ለመፈጸም አስቸጋሪ ቢሆንም የአለም ዋጋ ቅናሽ በሚሆንበት ጊዜ መግዛት እንዲችሉ ምንዛሪው እንዲፈቀድላቸው ለብሔራዊ ባንክ የተፃፈ 1 ገጽ ደብዳቤ የቀረበ መሆኑ፤
- በሲሚንቶ ግብይት ሰንሰለት የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት ከባላድርሻ አካላት ጋር(ማዕድን ሚኒስቴር፣ የሲሚንቶ አምራቾች ማህበርና ከሲሚንቶ

ፋብሪካዎች) ጋር በመሆን የተሰሩ ስራዎች መረጃ ከላይ በተሰጡ ምላሽ አባሪ የተደረገ መሆኑን፤

- ❖ በአብዛኛው የስኳር ምርት የሚቀርበው በሀገር ውስጥ በሚያመርቱ ፋብሪካዎች ሲሆን የምርት እጥረት ሲያጋጥም ተጨማሪ ግዥ ከውጭ እንዲፈጸም በማክሮ ኮሚቴ ውሳኔ ተሰጥቶ የስኳር ኢንዱስትሪ ጉሩፕ ግዢ በመፈጸም ማሳወቅ ያለበት ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤታችን ሂደቱን በተደጋጋሚ ሲጠየቅ የነበረ ቢሆንም ድጋፍ እንዲደረግ የጠየቀበት ሂደት ሆነ ድጋፍ ባለመጻፉ ግዢ ሊስተጓጎል የሚችልበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ እና ለክልሎችና ለዩኒቨርሲቲዎች ምርት እንዲቀርብ ሲጠየቅ ክምችት እንደሌለ የሚያሳወቁ መሆኑን፤ በአብዛኛው ምርት እያመረቱ የሚገኙት ፋብሪካዎች በደቡብ ኦሞ የሚገኙ ፋብሪካዎች በመሆናቸው የስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፑ በነዚህ ቦታዎች የሚመድብ መሆኑ፤
- ❖ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያልወሰዱት የዘይት ምርት በተመለከተ፡- በወቅቱ በአምስት ፋብሪካዎች በሽያጭ ላይ የነበረ የዘይት ምርት ዋጋ የዓለም ዋጋ ቅናሽ በማሳየቱ ምክንያት በገበያ ላይ ካለው ዋጋ ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ ክልሎች ለማንሳት ፍላጎት ያልነባራቸው እና ቅሬታ የቀረበ በመሆኑ ከክልሎች ጋር በመነጋገር ፋብሪካዎች በራሳቸው አማራጮች እንዲሸጡ የተደረገ መሆኑ፤
- ❖ ለገበያው ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ህጋዊ ነጋዴዎችና ደላላዎች ቢሆኑም ባልተፈቀደላቸው የንግድ አይነቶች ሰንሰለቱን የሚያረዝሙ ደላሎች እንዲወጡ የማድረግና የመከታተል ስራዎች እየተሰሩ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

68. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ አምራቾች፣ አስመጪዎች እና አከፋፋዮች ምርታቸውን ለማቅረብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚያስፈልጋቸው ድጋፍ እና ክትትል ባለመደረጉ ምርቶቹ ለህብረተሰቡ በወቅቱና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዳይቀርቡ አድርጓል፡፡

**የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አምራች ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው ለማምረት የሚያስችል ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ**

69. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች አምራች ተቋማት በሙሉ አቅማቸው ማምረት እንዲችሉ ሊያደረግ እና ችግር የሚፈቱ አማራጮች እንዲኖሩ እና ውጤታማ የገበያ ትስስርና ሰንሰለት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- የዘይት፣ የስኳር፣ ዱቄትና የዳቦ እንዲሁም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የውጪ ምንዛሬ እና ብድር የማያገኙ መሆኑ እና ለግብዓትነት የሚውሉ የአረምና የማሽነሪ ኬሚካል (የስኳር)፣ ስንዴ፣ ድንጋይ ከሰል (ለሲሚንቶ)፣ የቅባት እህሎች (ለዘይት)፤ የፋብሪካዎቹ ማሽነሪዎች፣ ብቁ ባለሞያዎች (የጥገና፣ መለዋወጫ ወዘተ) የማግኘት ችግሮች ያሉባቸው መሆኑን እንዲሁም የፀጥታ ችግር ምክንያት 24 ሰዓታት ያመርቱ የነበሩ 12 ሰዓት ብቻ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች መኖራቸው፤
- ከ2013 እስከ 2014 እና 2015 በጀት ዓመት በከፊል በሃገር ውስጥ የሚመረተው የድፍድፍ ዘይት የውጭ ምንዛሬ እቅድ ላይ በሙሉ አቅማቸው ለማምረት የሚያስችላቸው በየዓመቱ 993,335,700 ዶላር ጥያቄ የሚያቀርቡ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣት በ2015/2016 የተቋረጠ መሆኑና ፋብሪካዎቹ ከማምረት አቅማቸው በታች እያመረቱ መሆኑ፤
- የኢትዮጵያ ዱቄትና የዱቄት ውጤቶች አምራቾች ማህበር የዱቄትና የዱቄት ውጤቶች በዱቄት ፋብሪካዎች በኩል ለማህበረሰቡ ሲያቀርብ የቆየ ቢሆንም ኦሮሚያ ክልል በ17/04/2015 ባወጣው አዲስ መመሪያ ከክልሉ መግዛት የሚቻለው ከዩኒየኖች ብቻ ብሎ በመገደቡ እና ከዩንየኖች ማግኘት የሚችሉበት አሰራር ዝግ በመሆኑና ፋብሪካዎች ምርቱ ማግኘት ባለመቻላቸው ችግሩ እንዲፈታ ማህበሩ በቁጥር ኢ.ዱ.አ.ማ/1135/1-1/2015 በቀን 19/05/2015 ዓ.ም በደብዳቤ ጠይቆ መልስ ያልተሰጠ መሆኑ፤
- የስንዴ ምርት በግብአትነት የሚጠቀሙ በየክልሉ የሚገኙ ፋብሪካዎች በሃገር ውስጥ ከሚመረተው ምርት ትስስር ያልተፈጠረላቸው ሲሆን ምርቱን በራሳቸው መንገድ እንዲያገኙ ያልተመቻቸላቸው በመሆኑ ፋብሪካዎቹ ምርቱን በውድ ዋጋ ከጥቁር ገበያ ብቻ ሲያገኙ የሚያመርቱ መሆኑን በተከለሱ ማስረጃዎችና በቃለመጠይቆች ላይ የተገለፀ መሆኑ

  ለምሳሌ 300 በአዲስ አበባ እና 11 በድሬዳዋ የዱቄት ፋብሪካዎች ከ2012/2013 ዓ.ም በፊት ትስስር የነበራቸው ቢሆንም ከዛ በኃላ የገበያ

ትስስር የተቋረጠ መሆኑ እና ችግሩ እንዲፈታላቸው በዱቄትና የዱቄት ውጤቶች አምራቶች ማህበር፣ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢቀርብም ችግሩ ያልተፈታ መሆኑን በተከለሱ ማስረጃዎችና ቃለ- መጠይቆች ላይ የተገለፀ መሆኑ፤

❖ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ትልቁ ወጪ (65 በመቶ አካባቢ) ለማምረት የሚጠቀሙት የሀይል ወጪ በመሆኑ የሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል በብዛት እና በጥራት ማምረት ላይ ገና መሆኑና በጥራት ጉድለት የባሰ ማሽኖቻቸው እየተበላሸባቸው በመሆኑ ማምረት የሚያቋሙባቸው ወቅቶች እየተፈጠረ መሆኑ፤

የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ፋብሪካዎች ከማምረት አቅማቸው በታች እያመረቱ ስለመሆኑ ለማሳያነት፡-

- ሸሙ የዘይት ፋብሪካ (500,000 ሊትር ለማምረት 25,000 ዶላር ብቻ የተፈቀደለት መሆኑ እና ዶላር ሲለቀቅለት የሚያመርት መሆኑና ሳይለቀቅለት ሲቀር ደግሞ እያቆመ መሆኑ፣ ሌሎች አማራጮች እንዲጠቀም የግብአት፣ የብድር ድጋፍ እንዲያገኝ ያልተደረገ በመሆኑ ከ 4 ቀን 1 ቀን ብቻ (25 በመቶ) እያመረተ የነዳጅ ፍጆታው ከፍተኛ መሆኑና ለማሽነሪዎቹ ቀጣይነት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑ፤
- የዱቄት ፋብሪካዎች ምርቱን በጥቁር ገበያ ከገበያ ዋጋ በላይ እንዲገዙ መገደዳቸው በግብአት እጥረት ምክንያት የምርቱ ግብአት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች ማምረት በማቆም ላይ መሆናቸውና ማምረት ከሚችሉት አቅም ላይ በአማካኝ እስከ 30% እያመረቱ መሆኑ፤
- የሰኳር ፋብሪካዎች ከማምረት አቅማቸው በታች እያመረቱ መሆኑ ለምሳሌ በተሻለ ሁኔታ እያመረተ የነበረው ፊንጫ የስኳር ፋብሪካ የማምረት አቅሙን አንድ አራተኛ (1/4) እያመረተ መሆኑ፤
- የደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ፋብሪካ ለአባይ ግድብና ሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች 90% እያቀረበ ቢሆንም ከማምረት አቅሙ ከ30-35% እያመረተ መሆኑ እና የሌሎች ፋብሪካዎችም የ2015 በጀት ዓመት ክንውናቸው ኢትዮ ሲሚንቶ 46%፣ ካፒታል 12-25%፣ ፓዮኖር 14% እያመረቱ መሆኑ፤

❖ አማራጭ አዳዲስ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እንዲቋቋሙ በተለይ የጥሬ ዕቃ ግብአት ባሉባቸው አካባቢዎች እንዲስፋፉ የማድረግ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፤ የምርቶቹ ስርጭት ውጤታማ የሆነ የገበያ ትስስርና ሰንሰለት ያልተደረገ

መሆኑ በመጋቢት 20/2015 ዓ.ም ከሲሚንቶ ፋብሪካዎች (ዳንጎቴና ሙገር) ምርቱን የወሰዱ አከፋፋዮች ላይ በተደረገ ቁጥጥር የገበያ ትስስርና ሰንሰለት ክፍተት መኖሩ፤

**ለማሳያ፡-** አከፋፋይ ቴድሮስ መኮንን - የሚያከፋፍልበት የሲሚንቶ ምርት ስም ሙገር ሲሚንቶ የሚል ሆኖ የወሰደው ምርት 400 ኩንታል ሲሆን በተጨማሪ የሀበሻና የኢትዮ ሲሚንቶ ፋብሪካዎች ወኪል/አከፋፋይ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑ፣ ከሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ በገባው ውል ከፍሎ ያልወሰደው/ያላነሳው ሲሚንቶ 30,000 ኩንታል እንደነበረና ይህንን ከ2 ዓመት በፊት ብሩን ከቸርቻሪ ነጋዴዎች የተቀበለ መሆኑና ክስ ሲመሰረትበትም ኩፖኑን ለቸርቻሪዎቹ እንደሸጠላቸው እና ቸርቻሪዎቹ የገዙትን ምርት ያልወሰዱ መሆኑ፤ አከፋፋዩ ቸርቻሪዎቹ ምርቱን እንዲወሰዱ ከፈቀደላቸው በኋላም በስሙ እየወሰዱ ያሉት እነማን እንደሆነ የማያውቅ መሆኑ እና መረጃዎች ከፋብሪካው የማይደርሰው መሆኑ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 940/2015 አዲስ ትስስር ቢያደርግም 12,000 ኩንታል ከፍያው ፈፅመው ምርቱ ያልተሰጠው እና በመጠባበቅ ላይ መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

71.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች በማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ

- ❖ በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ለሚኖረው የገበያ ጉድለት እንዲሸፍኑ የውጭ ምንዛሪ ድጋፍ እንዲደረግ ዕቅድ የማቅረብና የመከታተል ስራዎች የሚሰራ መሆኑና ለማክሮ ኮሚቴ የቀረበ የ2015 እና 2016 በጀት ዓመት የውጭ ምንዛሪ ጥያቄ ዕቅድ መቅረቡ፤
- ❖ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የውጭ ምንዛሪ ድጋፍ እና ሌሎች የግብዓት ክትትል በማዕድን ሚኒስቴር በኩል የሚቀርብ ሲሆን በሚኒስቴር መ/ቤታችን ክትትል የሚደረግ መሆኑ ለማዕድን ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ ከላይ አባሪ ተያይዟል፡፡
- ❖ የስንዴ ምርት ስርጭት የሀገር ውስጥ ምርት አቅርቦት መጨመር ጋር በተያዘው የመንግስት አቅጣጫ መሰረት ለነጻ ገበያ የተተወ መሆኑ፤
- ❖ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ኃላፊነት የተሰጠው ለማዕድን ሚኒስቴር እንዲሁም ሌሎች አምራች ተቋማት (ፋብሪካዎች) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ኃላፊነት መሆኑን ተገልፀዋል፡፡

- የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ምርት አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆኑን በተመለከተ በጸጥታ ችግር፣ በውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ በኃይል መቆራረጥና በመሳሰሉት መሆኑ በአፈጻጸም ሪፖርቶች ላይ ለማክሮ ኮሚቴ ጭምር የቀረበና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ማዕድን ሚኒስቴር ጋር የሚሰራ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

72. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ሀላፊዎች ይህን ቢሉም የመሰረታዊ ሸቀጦች በ2015 እና በ2016 በጀት ዓመት እና የሲሚንቶን ለማክሮ ኮሚቴ የቀረበ የውጭ ምንዛሪ ዕቅድና ጥያቄ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ በመሆኑ፣ የስንዴ ምርት ስርጭት የምርቱ ግብአት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች በሃገር ውስጥ አቅራቢ ከሆኑት ምርቱ እንዲያገኙ የማመቻቸትና ትስስር የመፍጠር ስራ መሰራቱን የሚያሳይ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ እንዲሁም ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት እንዳልሆነ ቢገለፅም በ2014 እና 2015 በጀት ዓመት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች የተጠኑ ጥናቶች ላይ ስራውን እንደሚያከናውንና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሊሰራ የሚገባ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

73. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ ድጋፍ ባለመደረጉ ምርቶቹ ለተጠቃሚው በወቅቱ እንዳያገኙ እና ቀጣይነት ያለው የምርት አቅርቦት የተረጋጋ እንዳይሆንና ፋብሪካዎቹም በሙሉ አቅማቸው አምርተው የህብረተሰቡን ኑሮ በማሻሻል ለሀገር የሚሰጡትን ጥቅም እንዳይሰጡ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

## ሐ/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭት፣ ክፍፍልና አቅርቦትን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማደረጉን መገምገም፤

### የሲሚንቶ እና የዘይት ፋብሪካዎች የመሸጫ ዋጋ ቁጥጥርና ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤

74. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በየስድስት ወሩ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ሊወስን፤ ፋብሪካዎችም የጅምላና የችርቻሮዎች የዋጋ ጣሪያ ማውጣታቸው ሊቆጣጠር፤ የዘይት አቅራቢዎች በየሶስት ወሩ የፋብሪካ ዋጋ ሊያሳውቅ፣ አስመጪዎች /አቅራቢ ድርጅቶችና ለቸርቻሪ ነጋዴዎችም የመሸጫ ዋጋና የትርፍ ምጣኔን መወሰኑና የስርጭት እና የመሸጫ ዋጋ አፈፃፀሙን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

75. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- የሲሚንቶ ምርት የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ በየስድስት ወሩ የሚወሰን ሲሆን የፋብሪካ ዋጋ ታህሳስ 2015 ዓ.ም የወጣ የፋብሪካ ዋጋ ከአንድ ዓመት በላይ የሆነ ቢሆንም ያልተከለሰ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በወጣላቸው ዋጋ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ በተከታታይና ቀጣይነት ባለው መልኩ የማይከታተል መሆኑ፣ የዋጋ ተመኑ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ (ከተተመነ ዋጋ በላይ እየተሸጡ መሆኑ) እና የሚሸጡበት ዋጋ ሲጠየቁ መረጃ የማይሰጡ ፋብሪካዎች መኖራቸው ለምሳሌ ከሃምሌ 2014 እስከ ጥር 2015 ዓ.ም ሲሸጡበት የነበረው ዋጋ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያዎች በመስክ ምልከታቸው ወቅት ሲጠይቋቸው በመስክ ሪፖርቱ ስማቸው ያልተጠቀሰ አራት ፋብሪካዎች መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው መገለፁ፤
- በሲሚንቶ ፋብሪካዎች እና ምርቱን በሚያከፋፍሉ አከፋፋዮች መሀል ደላላዎች መኖራቸው እና በተቀመጠው የምርት ስርጭት ሰንሰለት እየተገበያዩ አለመሆኑ፤ አከፋፋዩችና ቸርቻሪዎች ስራቸውን ከሚያቆሙ ምርቱን ከደላሎችና ከሹፌሮች ያለደረሰኝ እየተረከቡ ያለደረሰኝ እየሸጡ መሆኑ ይህም ምርቱ ወደ ተጠቃሚው ሲደርስ ከፋብሪካው ዋጋ በእጥፍ ዋጋ እየተሸጠ መሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎችና በኦዲቱ ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባስቀመጠው አቅጣጫና በመመሪያ መሰረት የሲሚንቶ ገበያ ፋብሪካዎቹ የራሳቸው አከፋፋይ፣ አከፋፋዮቹም የራሳቸው ቸርቻሪዎችን መርጠው እየተገበያዩ አለመሆኑ እና ፋብሪካዎቹ የተወሰኑ አከፋፋዮች ቢኖሯቸውም እንኳን ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የአከፋፋዮቻቸው የዋጋ ጣሪያ ማውጣታቸውን የማይቆጣጠራቸው መሆኑ፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከተተመነ ዋጋ በላይ ምርቱን ለሚሸጡ እንጂ ለመረጥዋቸው አከፋፋዮች እየሸጡ

አለመሆኑ በተከለሱ ማስረጃዎችና በኦዲቱ ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ላይ የተገለፀ መሆኑ፤

**ለምሳሌ** አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በመጋቢት 20/2015 ዓ.ም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች (ዳንጎቴና ሙገር) የሲሚንቶ ምርት የወሰዱ አከፋፋዮች ላይ በተደረገ ቁጥጥር ከተገኙ ክፍተቶች ለማሳያ፡-

- ✓ ሶፊር ኮንስትራክሽን ማቴሪያል ድርጅት- የሚያከፋፍለው የዳንጎቴ ሲሚንቶ ሲሆን 400 ኩንታል የሲሚንቶ ምርት ከዳንጎቴ የወሰደ መሆኑን ለአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ከተላከ ዝርዝር ውስጥ አንዱ መሆኑ፣ ነገር ግን በተደረገ ማጣራት የሃበሻ ሲሚንቶ አከፋፋይ መሆናቸው፤ የዳንጎቴ አከፋፋይ እንዳልሆነ እና ምርቱም ደርሷቸው የማያውቅ መሆኑ፤
- ✓ ሚክር ትሬድንግ ከዳንጎቴ የሚያከፋፉሉት የዳንጎቴ ሲሚንቶ ሲሆን 400 ኩንታል የሲሚንቶ ምርት ከዳንጎቴ የወሰደ መሆኑን ለአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ከተላከ ዝርዝር ውስጥ አንዱ መሆኑ፣ ነገር ግን አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ባደረገው ቁጥጥር በአዲሱ ትስስር የተባለው ምርት ያልወሰዱ መሆኑ፤
- ✓ የኑስ ወዳጅ መኮንን የሚያከፋፉሉት የሲሚንቶ ምርት የዳንጎቴ ሲሚንቶ ሲሆን 1050 ኩንታል የሲሚንቶ ምርት ከዳንጎቴ እንደተወሰደ ለአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ከተላከ ዝርዝር ውስጥ አንዱ መሆኑ፣ ነገር ግን በቅድመ ክፍያ ገዝተውት የነበር ምርት እንጂ አዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ባደረገው ቁጥጥር በአዲሱ ትስስርና የተባለው ምርት ያልወሰዱ መሆናቸው ፤
- ✓ ዙመናስ ትሬድንግ የሚያከፋፉሉት የሲሚንቶ ምርት ስም ዳንጎቴ፣ የወሰደው ምርት መጠን 750 ኩንታል መሆኑ ከፋብሪካው ለአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ከዳንጎቴ የተላከ ምርት ከወሰዱት ዝርዝር ውስጥ አንዱ መሆኑ ነገር ግን በተባለው ወቅት ግዢ ያልተካሄደ መሆኑ በሰነድ ያመሳከሩ መሆኑ፤

- ❖ የዘይት አቅራቢዎች በየሶስት ወሩ ፋብሪካ በር ዋጋ (የፋብሪካው የመሸጫ ዋጋ) ትመና እየተተገበረ አለመሆኑ፣ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ወቅትን የጠበቀ አለመሆኑ (በአማካይ በ8 ወር ዋጋ የሚተመን መሆኑ) ለምሳሌ የሃመሬሳ

ዘይት ፋብሪካ ዋጋ ትመና በአመት አንዴ መሆኑ፤ አፈፃፀሙን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይከታተል መሆኑ፤

- ❖ የመሰረታዊ ሸቀጦች የትራንስፖርት ወጪ የተወሰነ በደብዳቤ የማሻሻል ሁኔታ ቢኖርም ለአከፋፋዮችና ለቸርቻሪዎች የመሸጫ ዋጋ ስሌት ነባራዊ/ወቅታዊ ሁኔታን መሰረት በማድረግ ያልተከለሰ መሆኑ፣ አከፋፋዮቹ በማስገደድ እየሰሩ መሆኑ እና ልምድና አቅም ያላቸው ሸማቶች ከስራው እየወጡ መሆኑ በቃለ-ጉባኤዎች፣ በጥናቶች፣ በኦዲቱ ወቅት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- ❖ የዘይት ምርት አቅርቦቱ ወጥነት ያለው፤ በተመሳሳይ ጊዜና መጠን ለአንድ ክልል፣ ዞንና ማህበራት እንዲቀርብ ከምርት አምራቾችና አቅራቢዎች ጋር በመሆን እየተሰራ አለመሆኑ፤
- ❖ በመሰረታዊ ሸቀጦችና በሲሚንቶ ምርቶች የትርፍ ህዳግን በሚመለከት ጣራ እንዲኖረው የሚያደርግ ፖሊሲ ወደ ስራ እንዲገባ አለመደረጉ፣

ለመረዳት ተችሏል፡፡

76.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ባወጣው የፋብሪካ በር ዋጋ መሰረት እየተሸጠ ስለመሆኑ ክትትል የተደረገበት ሁለት የመስክ ሪፖርት እና በመመሪያ ቁጥር 940/2014 መሠረት ፋብሪካዎች የራሳቸውን አከፋፋዮች በራሳቸው መርጠው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳወቁ መሆኑ፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የፋብሪካ በር ዋጋን መሰረት በማድረግ የአከፋፋዮችን ዋጋ ተምነው እንዲያሳውቁ ክትትል የሚደረግ መሆኑ፣ የጅምላና ችርቻሮ መሸጫ ዋጋ ያሳወቁ መሆኑ፤ የዘይት የፋብሪካ በር መሸጫ ዋጋን ምርት ማስገባት ሲጀምሩ በሚያቀርቡት መረጃዎች መሰረት ተሰልቶ የሚወሰን መሆኑና የውጭ ምንዛሪ በ2015 በጀት ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ያገኙ መሆኑና በ2016 በጀት ዓመት ምንም የውጭ ምንዛሪ ያልተፈቀደ በመሆኑ ክፍተቱ ትክክል መሆኑ ገልፀዋል፡፡

77.በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ የተተመነ ዋጋ ስለመተግበሩ በመስከረም 2015 ዓ.ም እና የሲሚንቶ ስርጭት መመሪያ አተገባበር በጥር 2015 ዓ.ም የመስክ ምልከታ መደረጉ የሚያበረታታ ቢሆንም ከ2013 እስከ 2015/2016 በጀት ዓመት ሲታይ ግን ካለው የምርቱ የህገ ወጥ ግብይት አንፃር እነዚህ ሁለት የመስክ ምልከታዎች በቂ ናቸው ብሎ ለመውሰድ የማይቻል መሆኑ እና ፋብሪካዎች የራሳቸውን አከፋፋዮች

መርጠው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳወቁ ቢሆንም የተሟላ መረጃ ባለመኖሩ ምላሹ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

78.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዘይት ምርት አቅርቦቱ ወጥነት እንዲኖረውና በተመሳሳይ ጊዜና መጠን በዙር ለአንድ ክልል፣ ዞንና ማህበራት እንዲቀርብ ከምርት አምራቾችና አቅራቢዎች ጋር በመሆን እየተሰራ ባለመሆኑ በሁሉም አካባቢዎች ተደራሽ እንዳይሆን እና የሲሚንቶ ምርትም በተዘረጋለት ሰንሰለትና በወጣው ዋጋ ህብረተሰቡ ምርቱን እንዳያገኝ አድርጎታል፡፡

**የመሰረታዊ ሸቀጦችና የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች በሚያቀርቡት ምርት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን በተመለከተ፤**

79.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችና የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን ዘይት አይነቱን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መጠኑን እና በፓኬጅ ሊለይና ሊወስን እንዲሁም አስመጪው ከአንድ ክልል በላይ በአስመጪነት መወዳደር /መመረጥ እንደሌለበት ሊከታተልን እና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

80.ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን ዘይት አይነቱን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መጠኑን እና በፓኬጅ መለየትና መወሰን ላይ እና አስመጪው ከአንድ ክልል በላይ በአስመጪነት መወዳደር /መመረጥ እንደሌለበት የመወሰን ሂደት ላይ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የማይሳተፉ መሆኑ፣
- የክልልና የከተማ አስተዳደሮች በፋብሪካዎች የሚቀርቡ ምርቶች መጠንና ጥራት እየቀረበ ስለመሆኑ ክትትል የማያደርጉ መሆኑ፤
- የስኳር ምርት ጥራት ችግሮች ያሉበት መሆኑ፤ለምሳሌ ብልሽቶቹም ደረቅ የማይፈረካከስ፣ እርጥበት ያለው፣ ባዕድ ነገር የተቀላቀለበት፣ ጥቁር ብናኝ ያለው፣ ማሸግያው ላይም የተመረተበት ቀን፣ የመጠቀሚያ ጊዜው፣ የባች ቁጥር እና የመጠን መለኪያ የማይገልፅ መሆኑ እንዲሁም በሶስተኛ ወገን

የተጣራ መሆኑ እና ደረጃው ታይቶ 90 በመቶ ፓራሜትሮች ያላሟሉ መሆኑ በተደጋጋሚ የተረጋገጠ መሆኑ፣

- ❖ ስኳር በተደጋጋሚ የሚዛን ጉድለት ያለበት መሆኑ ለምሳሌ ከአንድ ኩንታል በአማካይ 8 ኪሎ ጉደለት እየታየ መሆኑ፤ አከፋፋዮቹ በአንድ ኩንታል ታሽጎ የሚመጣውን ስኳር በራሳቸው መዝነው እንዲወስዱ የማይፈቀድላቸው መሆኑ እና በየሸማቶቹ በየዓመቱ ተከማችቶ ለከፍተኛ እዳ እየዳረጋቸው መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና በቃለ-መጠይቆች፣ ላይ የተገለፀ መሆኑ፤ለማሳያነት ጥራት የሌለው የቀረበ የስኳር ምርት በአባሪ 4 ተያይዘዋል፡፡
- ❖ እንዲሁም የስኳር ፋብሪካዎች በሚያቀርቡት ምርት ላይ በጥራትና በሚዛን ጉድለት ችግሮቹ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ሲሆን ጥብቅ ክትትል እንዲያደርግና ምርቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ እንዳለው አውቆ ከሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች የሚመረቱ እና ከውጪ ለሚገባ ምርት አስፈላጊው የጥራት ደረጃ መስፈርቶች እንዲያሟሉ ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ ለኢትዮጵያ ስኳር እንዱስትሪ (ኦሞ ኩራዝ 2 እና 3 ስኳር ፋብሪካ) በሚያዚያ 12/2015 ዓ.ም በደብዳቤ ያሳወቁ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡
- ❖ ከስኳር ፋብሪካዎች ለሸማቾች የሚቀርበው የተበላሸ የስኳር ምርት ወደ ፋብሪካው እንዲመለስ መደረጉን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገለፀ ቢሆንም ማስረጃው ለኦዲቱ ያልቀረበ መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

81.ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ በአሁኑ ወቅት ያለቀለት የምግብ ዘይት አስመጭዎች በመንግስት የልማት ድርጅቶች ብቻ በገንዘብ ሚኒስቴር ድጋፍ መሰረት የሚገቡ እንጂ በክልል የማይመረጡ መሆኑ፤ እነዚህ የልማት ድርጅቶች በሁሉም ክልል መሸጫ ማእከል ያላቸው መሆኑ፣ የክልልና የከተማ አስተዳደሮች በፋብሪካዎች የሚቀርቡ መጠን ላይ በአግባቡ ክትትል በማድረግ ሪፖርት ማቅረብ ዋነኛ ስራቸው መሆኑና ሪፖርቱ ናሙና ከላይ የተያያዘ መሆኑን እና ሸማቹ የሚቀርበው ስኳር ምርት ጥራቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት የሚታመን ቢሆንም ከጥራት ጋር በተያያዘ ከክልሎች የሚቀርበውን ቅሬታ መሠረት በማድረግ ከሚመለከተው የስራ ክፍል ቦታው ድረስ በመሄድ

ናሙና ተወስዶ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ በማድረግ የጥራት ጉድለት እንዳለበት በመረጋገጡ እንዲቀየርላቸው መደረጉና ሁለት ገፅ ደብዳቤዎች ብቻ ለኦዲተሮቹ የቀረቡ መሆኑ እንዲሁም የስኳር ፋብሪካዎች በሚያቀርቡት ምርት ላይ በጥራትና በሚዛን ጉድለት ችግሮቹ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ሲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስኳር ጥራትን በተመለከተ ጥብቅ ክትትል እንዲያደርግና ምርቱ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ እንዳለው አውቆ ከሀገር ውስጥ ፋብሪካዎች የሚመረቱ እና ከውጪ ለሚገባ ምርት አስፈላጊው የጥራት ደረጃ መስፈርቶች እንዲያሟሉ ክትትልና ድጋፍ እንዲደረግ ለኢትዮጵያ ስኳር እንዱስትሪ (ኦሞ ኩራዝ 2 እና 3 ስኳር ፋብሪካ) በሚያዚያ 12/2015 ዓ.ም በደብዳቤ ያሳወቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

82.በሚኒስቴር መ/ቤቱ በላብራቶሪ እንዲፈተሽ በማድረግ የጥራት ጉድለት እንዳለበት መረጋገጡ ጥሩ ቢሆንም የስኳር ምርት በተደጋጋሚ የጥራት ጉድለት የተከሰተ በመሆኑ በቂ ስራ ተሰርቷል ለማለት የማያስደፍር መሆኑ፤ በጥራት ጉድለት ለፋብሪካዎች ተመላሽ ተደርገዋል ቢባልም በአማራ ክልል ሁለት ቦታዎች በደቡብ ክልል አንድ ቦታ አከፋፋዮች ብቻ እንጂ ለሁሉም (ጥራት የሌለው የስኳር ምርት የወሰዱ) ተመላሽ ያልተደረገ በመሆኑ፤ የሚዛን ጉድለት ችግር አሁንም ያለ መሆኑ እና ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ምርቱ በፋብሪካዎች ከመቅረቡ በፊት መጠንና ጥራት ላይ ክትትል በተወሰነ ደረጃ እያደረገ ቢሆንም እርምጃ እየተወሰደ ባለመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

83.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን ምርት አይነቱን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መጠኑንና ፓኬጁ መለየት ላይ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የማይሳተፉ በመሆኑ፣ በየአከባቢያቸው በቅርበት ክትትል የማያደርጉ በመሆኑ ምርቶች ላይ በተለይ የስኳር ምርት በተደጋጋሚ የጥራት ጉድለትና የሚዛን ጉደለት እንዲከሰት እና በአከፋፋዮቹ /በሸማቾች ማህበራት ተከማችቶ ለእጳ እንዲዳረጉ እና በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

**የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ከተቀመጠው የስርጭት ስርዓት ውጭ በሚሰሩ ተቋማት ላይ እርምጃዎችን መውሰዱን በተመለከተ፤**

84.ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ከተቀመጠው የስርጭት ስርዓት ውጭ በሚሰሩ ተቋማት ላይ በሚያከማቹ፣ በሚያጓጉዙ፣ በሚያሰራጩና ከተወሰነው ዋጋ በላይ የሚሸጡ እና መዛባት ሲኖር ፋብሪካዎች፣ አስመጪዎች /አቅራቢ

ድርጅቶችና ቸርቻሪዎች ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ሊወስድ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- በሲሚንቶ ስርጭት ላይ የሚፈጠሩ የስርጭት መዛባት እርምጃ እየተወሰደ አለመሆኑ፣ ህግ ወጥ ግብይት እየተደረገ መሆኑ እየታወቀ እርምጃ የሚወስድ አካል የሌለ መሆኑ ከቀረቡ ማስረጃዎችና ቃለ-መጠይቆች የተገለፀ መሆኑ፤
- በመመሪያ ቁጥር 940/215 ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ በአከፋፋዮች ላይ እርምጃ የሚወስደው የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ናቸው ቢባልም እርምጃ እየወሰዱ አለመሆኑ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም እርምጃ ስለመውሰዳቸው ክትትል የማያደርግ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከየክፍለ ከተማው የ2015 ዓ.ም የ6 ወር ተሰብስቦ ከተወረሰ የሲሚንቶ ምርት 36,796.5 ኩንታል ውስጥ 7341 ኩንታል ለባለቤቱ የተመለሰ መሆኑ፣ 400.1 ኩንታል የተበላሸ እና 619 ኩንታል ዋጋ ያልወጣለት መሆኑ እና የቀረው 26,662.5 ኩንታል ለልማት ድርጅቶች የተሰጠ ሲሆን የልማት ድረጅቱም ሸጠው ገንዘቡን ለመንግስት ገቢ ማድረግ ቢገባቸውም ንብረቱ ስላለበት ሁኔታ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች (በፍራንኮቫሉታ) ስርጭትና ግብይት ላይ ባጠናቸው ጥናቶች በተገኙ ክፍተቶች ለምሳሌ የምርት በማከማቸት እጥረት እንዲፈጠር በሚያደርጉ፣ በህገወጥ ግብይት፣ ከዋጋ በላይ በሚሸጡት እና የመሳሰሉት ክፍተቶች ላይ መፍትሄ እየሰጠ አለመሆኑ፤ እንዲሁም ቁጥጥርና ምርመራ እየተደረገ አለመሆኑ እና እርምጃም እየተወሰደ አለመሆኑ የተገለፀ መሆኑን፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

86. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ እንዲሁም በመውጫ ስብሰባ በሰጡት ምላሽ የሲሚንቶ አከፋፋዮች በአግባቡ ባለማቅረባቸው ፋብሪካዎች የሚከታተሉና እርምጃ የሚወስዱ ሆኖ ክልሎችና ከተማ

አስተዳደሮችም ህገ-ወጥ የሲሚንቶ ዝውውርና ስርጭት ቁጥጥር የሚያደርጉና እርምጃ የሚወስዱ መሆኑ፣ እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 940/2015 በወጣው ላይ የምርቱ ስርጭት ክትትልና ቁጥጥር ኃላፊነቱ የተሰጠው ለሲሚኒቶ ፋብሪካዎች መሆኑ፣ በፍራንኮቫሎታ የገቡ ምርቶች የመሸጫ ዋጋ የማይተመን መሆኑና የሚያከማቹ አስመጭዎች ከብሔራዊ ደህንነት ጋር በመሆን በመከታተል እርምጃ የተወሰደ መሆኑን የተያዘ ቃለ-ጉባኤ መቅረቡ እና አድራሻቸው ለክልሎች እንደሚላክ ገልፀዋል፡፡

87.በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰሩ ስራዎች ጥሩ ቢሆንም በመመሪያ 908/2014 ሲሚንቶ በአከፋፋዮች ላይ እርምጃ የመውሰድ/የመውረስ/ ሁኔታ የነበር ሲሆን 2013 እና በ2015 ዓ.ም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፣ የሚከታተሉና እርምጃ የሚወስዱ ፋብሪካዎች በመሆናቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮችም ህገ-ወጥ የሲሚንቶ ስርጭት ቁጥጥር የማያደርጉ እና እርምጃ የማይወስዱ መሆኑ ነገር ግን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመመሪያ ቁጥር 940/2015 በተሰጠው ስልጣን መሰረት የምርቱ ስርጭት ክትትልና ቁጥጥር ላይ የተጀመሩ ስራዎች ቢኖሩም በተጠናከረ መልኩ አለመሆኑ፣ እና የፍራንኮ ቫሉታ ለክልሎች የሚላከው መረጃም እንዲያውቁት እንጂ አስመጪው ማግኘት በሚቻልበት ሁኔታ ቲንና ከንግድ ፈቃድ ጭምር ምርቶቹ ሳይሸጡ ወቅታዊ መረጃ የማይላክላቸው መሆኑ፣ምርቶችን የሚያከማቹ፣ ያለ ደረሰኝና ያለ አግባብ ዋጋ በሚጨምሩ እና እጥረት ወዳለበት አካባቢዎች ሂዶ በመሸጡ አስመጭዎች ክልሎች እርምጃ እየወሰዱ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

88.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ከተቀመጠው የስርጭት ስርዓት ውጭ በሚሰሩ ተቋማት ላይ ተገቢውን እርምጃ ባለመወሰዱ ህጋዊ ግብይትና አሰራር እንዳይሰፍን እና ምርቶቹ በተገቢው መንገድ ተሰራጭተው ገበያው እንዳይረጋጋ አድርጎታል፡፡

**በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ለሚሰሩ የንግድ ዘርፍ እና የሸማቾች ማህበራት የግንዛቤ፣ የትምህርትና የስልጠና መስጠቱን በተመለከተ፤**

89.ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ለሚሰሩ የንግድ፣ ዘርፍ እና የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙና የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ የግንዛቤ፣ የትምህርትና የስልጠና መድረኮችን ሊያደራጅ፣ ሊሰጥ እና ለክልሎችም አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

90. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- ❖ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ለሚሰሩ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ከ2013 እስከ 2015/2016 የትምህርትና የስልጠና መድረኮች ስለመስጠታቸው ለኦዲት ቡድኑ ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑ፤
- ❖ ለክልሎችም በ2015 በጀት ዓመት የአዋጅ ቁጥር 813 የማሻሻያ ረቂቅ ላይ የተሰጠ ግንዛቤ ውጪ ከ2013 እስከ 2015/2016 ሩብ ዓመት ስልጠና እና ሌሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ስለመደረጉ የሚያሳይ ማስረጃ አለመኖሩ፤ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2016 በጀት ዓመት ባደረገው አካላዊ ምልከታ በትግራይ ክልል ከጦርነት በኋላ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተገቢው ድጋፍ ለማድረግ ቃል የገባውን ያልፈፀመ መሆኑ፤
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስልጠና ድጋፍ እየሰጠ አለመሆኑ ለምሳሌ የላብራቶር አቅም ክፍተት መኖሩ፤ የማስተማር ስራዎች ያልተሰሩ መሆኑ በዚህ ዘርፍ ያሉ ተቋማት አብረው ከክልሎች ጋር እየሰሩ አለመሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

91. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ የሚሰሩ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ የተቋቋሙትም እንዲጠናከሩ የግንዛቤ፣ የትምህርትና ስልጠና ስለመሰጠቱ ማስረጃ እንዲቀርብ የሚጠይቅ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ላይ ግንዛቤ እና ትምህርትና ስልጠና ለመስጠት እንደ ክፍል የተያዘ ዕቅድ እንደሌለ እና ከመሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች እና ሲሚንቶ ጋር ተያይዞ የተቋቋሙ ማህበራት በስራ ክፍል የተሰራ ስራም ሆነ የተሰጠ ስልጠና የሌለ መሆኑን እንዲሁም ክልሎች የአዋጅ ቁጥር 813 የማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ለማዳበር ሀሳብ አስተያየት መሰብሰብ እንጂ ባልጸደቀ ረቂቅ ማሻሻያ አዋጅ ላይ ስልጠና የማይሰጥ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

92.በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ የሚሰሩ አካላት፣ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ የተቋቋሙትም እንዲጠናከሩ የግንዛቤ፣ የትምህርትና ስልጠና ድጋፎች ባለመሰጠቱ ስርጭቱ በእውቀት የተመሰረተ እንዳይሆን፤ ምርቶቹ ለህብረተሰቡ በማድረስ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ እና ሃላፊነትና ተጠያቂነት የተሞላበት የግብይትና የሥርጭት ሥርዓት እንዳይኖር አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

**መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ኮታ ወቅታዊ ማድረጉና ማሰራጨቱን በተመለከተ፤**

93.ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ኮታ ወቅታዊ እያደረገ ሊወስን፣ ሊያሰራጭና ሊከታተል ይገባል፡፡

94.ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የዘይት ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ኮታ ወቅታዊ የማድረግ ሁኔታ አለመኖሩና ሲላክም ቀጣይነት የሌለው (ለአንድ ጊዜ ብቻ)፣ በአነሰተኛ መጠን መሆኑ እና ስርጭቱ ላይም ክትትል የማይደረግ መሆኑ፤

  ለማሳያ- በኦሮሚያ ክልል ቆላማ የቦረናና ምስራቅ ቦረና ዞኖች በገጠማቸው ድርቅ ምክንያት ለከፍተኛ ችግር የተጋለጡ መሆኑና 10,000 ኩንታል ስኳር እንዲፈቀድላቸው በሚያዝያ 3/2015 በደብዳቤ ቢጠይቁም 5000 ኩንታል ብቻ የተፈቀደላቸው መሆኑ፤
- በትግራይ ክልል የተላከው ዘይትና ስኳር በጦርነት ወቅት ከስድስት ወረዳ በላይ የተፈናቀለውና ወደ ከተማ የገባውን ህብረተሰብ ያላገናዘበ መሆኑ እና ለበርካታ ወራት/የ17 ወራት ያልተላከላቸው መሆኑ በጥር ወር 2016 ዓ.ም በተደረገ የአካላዊ ምልከታ /በመስክ ሪፖርት ላይ የተገለፀ መሆኑ፤
- በአፋር ክልል ንግድ ቢሮ በየካቲት 20/2015 በቁጥር ደከሰ/311/2015 በተፃፈው ደብዳቤ በጦርነቱ ምክንያት የግብይት ስርዓት በመቋረጡና

ከፍተኛ የመሰረታዊ ሸቀጦች እጥረት ያስከተለ መሆኑ፣ የስኳር ምርት 30,000 ኩንታል እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው ሚኒስቴር መ/ቤቱ የካቲት 29/2015 ለኢትዮጵያ ስኳር ኢንዱስትሪ ግሩፕ 9,432 ኩንታል ብቻ እንዲቀርብ የተወሰነ መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

95. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ከመደበኛ ኮታቸው በልዩ ሁኔታ በመመሪያው መሰረት ሲፈቀድ የነበረ መሆኑ፣ መጠኑን በተመለከተ በሚኖረው ምርት አቅርቦት/ክምችት ላይ የሚወሰን መሆኑ፣ መደበኛ ኮታ ባለመሆኑ አደጋዎቹ በተከሰቱ ጊዜ ብቻ ተጠይቆ የሚፈቀድ መሆኑና ተከታታይነት የማያስፈልገው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

96. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች በመመሪያው መሰረት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በመደበኛ ኮታቸው ላይ ለተጎዱ አካላት ግምት በማስገባት ተጨማሪ ምርቶች እንዲሰጣቸው እያደረገ ባለመሆኑ እና አደጋዎቹ በተከሰቱ ጊዜና ችግሩ እስኪቀረፍ ድረስ ድጋፍ መደረግ የሚገባ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

97. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የምርት ስርጭት ባለመላኩ አደጋዎቹ በተከሰተባቸው አከባቢ የሚገኙ ዜጎች ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

**የመሰረታዊ ሸቀጦችና የሲሚንቶ ስርጭት ሴቶችን እና ድጋፍ የሚሹ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረጉን በተመለከተ፡**

98. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን በተመለከተ የሚወጡ ህጎችና ፖሊሲዎች የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች፤ አረጋውያንን እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ እንደሆኑ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋና ሊተገብር ይገባል፡፡

99. ይሁን እንጂ በኦዲት ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ሚኒስትር መ/ቤቶች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ የዘይትና የሲሚንቶ ፋብሪካዎች አከፋፋዮቻቸውና ቸርቻሪዎች

እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ከተደረገ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው፡-

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተዘጋጁ ካሉ ሶስት ረቂቅ ፖሊሲዎች አንዱ ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች ስራ እድል ፈጠራን በተመለከተ ለማካተት የተሞከረ ቢሆንም የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች፤ አረጋውያንን እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ በሚያደርግ መልኩ ያልሆነ እና ያልፀደቀ መሆኑ፣
- ሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ሴቶችንና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ የስርጭትና የተደራሽነት ሥርአት ያልዘረጋ መሆኑ፤ እንዲሁም ከ2013-2016 ሁለተኛው ሩብ አመት እነዚህን ክፍሎች በተለየ ድጋፍ ስለማድረጉ ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ ያልቀረበ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ በመንግስት ድጋፍ የሚቀርቡ መሰረታዊ ሸቀጦች ተደራሽ ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ በዕቅድ እና በአፈፃፀም ላይ ሴቶችና ድጋፍ የሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍና ተጠቃሚ ለማድረግ የተሰራ ሥራ ስለመኖሩ ማሰረጃ ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፤

ለመረዳት ተችሏል፡፡

100. ስለጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በማጠቃለያ መጠይቅና በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ የሲሚንቶ መመሪያ 908/2014 ሲወጣ ለወጣቶች የሥራ እድል ሊፈጥር በሚችል መልኩ የወጣ መሆኑ ገልፀዋል፡

101. የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህንን ቢሉም የሲሚንቶ መመሪያ 908/2014 መሰረት ተደራጅቶ የነበሩ ወጣቶች መመሪያው ሲሻር የተበተኑ መሆኑና እና ቀጣይነት የሌለው ድጋፍ እየተደረገ ባለመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

102. በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን ለማሳለጥ በሚያዘጋጃቸው ህጎችና ፖሊሲዎች፤ የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች፤ አረጋውያንን እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ ችግሮቹ የበለጠ የሚጎዳቸውን የህብረተሰብ ክፍል ለመደገፍ የሚያስችል ስራ እንዳይዘረጋ፣ ትኩረት እንዲነፈጋቸው በማድረግ ስራ አጥነት

እና ችግሮቻቸው እንዲባባስ ከማድረጉም በላይ ፍትሃዊና እኩል ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

# ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

103. በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን በተመለከተ የተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፍራንኮቫሉታ ወደሀገር የሚገቡ ምርቶች ተደራሽ ሆነው የኑሮ ውድነቱ /ገበያው ማረጋጋቱን የሚያረጋግጥ የስርጭት/የግብይት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣ የአስመጪዎቹ ማንነት የሚታወቅበት እና የቁጥጥር ስርዓት ያልተዘረጋላቸው መሆኑ፣ የምርት ሥርጭት ሂደቱም አስመጪዎቹ በሚፈልጉት/ገበያ ባለበት አካባቢ እንጂ በሁሉም ክልሎች በተለይ የመሰረታዊ ሸቀጦች እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች እንዲዳረሱ፤ የአስመጪዎች (ፈራንኮቫሉታ) የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃ ለክልሎች እንዲደርስ፤ ትስስር እንዲኖራቸው እና ቁጥጥርም እንዲደረግ አልተደረገም፡፡
- ❖ የሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦች አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች መመሪያዎች እንዲደርሳቸው፤ የሲሚንቶ መመሪያዎች ሁሉም አካታችና ተግባራዊ እንዲሆኑ እንዲሁም የሲሚንቶ የኮታ መመሪያ እንዲዘጋጅ አልተደረገም፡፡
- ❖ የመሰረታዊ ሸቀጦች እና የሲሚንቶ ምርት አሁን ካለው ፍላጎት፣ አቅርቦትና እጥረት አንፃር ለሁሉም ተደራሽ ለማድረግ ምርቱ፣ አሰራሩና በስርጭቱ እንዲጣጣም አልተደረገም፤ በፍራንኮቫሉታ በጥናት የተለዩ እና በግብይቱ ያሉ ክፍተቶቹ ምርቶች በየዙሩ ግዥ ከተፈፀመ በኃላ ምርቶቹ ሙሉ በሙሉ እንዲገቡ እና ከገቡ በኋላ የአቅርቦትና የግብይት ችግር (ዋጋ መጨመር፣ አየር በአየር መሸጥ፣ ምርቱ ወደ ገበያ አለማውጣትና እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ እና የመሳሰሉት) በርካታ ክፍተቶች ልይ ማስተካከያ እንዲደረግ፤ አስመጪዎቹ የንግድ አድራሻቸው ተለዋዋጭና የማይታወቅ በመሆኑ ወቅታዊ መረጃ እንዲኖር፣ የስርጭት ሰንሰለቱ እንዲታወቅ እና ምርቶቹ ቀጥታ ወደ ህብረተሰቡ ስለመድረሱ ቀጣይነት ያለው ክትትል እንዲደረግ አልተደረገም፡፡
- ❖ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለአከፋፋዮችና ለቸርቻሪዎች በተዘረጋላቸው ሰንሰለት ምርቱን እንዲያገኙ ባለመደረጉ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች ስራቸውን

ከሚያቆሙ ከደላሎች እና ከሹፌሮች ያለደረሰኝ ተረክበው ያለደረሰኝ እየሸጡ እንዲሸጡ፤ የሲሚንቶ ስርጭትን ግልፅ እንዲሆን እና ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ምርቱን ከየት እንደሚመጣ ምንጩ እንዳያውቁ፤ ምርቱ ለረጅም ጊዜ ዘግይቶ የሚደርስ በመሆኑ ከፍተኛ እጥረትና የዋጋ ውድነት እንዲፈታ እና ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የሚቆጣጠር አካል እንዲኖር አልተደረገም፡፡

- ❖ በሲሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አከፋፋዮች አመራረጥና አመዳደብ ከክልል ክልል ቀጣይነት፣ ግልፅና ወጥነት እንዲኖሮው፤ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እያመረቱ ባሉ የስኳር ፋብሪካዎችን ርቀት ሚዛናዊ በሆነ አመዳደብ እንዲኖርና ክልሎች ቅሬታ እንዲፈታ አልተደረገም፡፡ ይህም ምርቱ በወቅቱ እንዳይደርስና ዋጋ እንዲጨምር ተፅዕኖ እንዲፈጥር፤ በሲሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ምርቶቹ በገበያ እንዳይገኙ፤ የዋጋ ውድነት በተለይ በመንግስት ድጋፍ የሚቀርቡ ምርቶች ህብረተሰቡ ጋር በወቅቱ እንዲደርሱ ዋጋቸውም ገበያ ካለው ዋጋ ተመሳሳይንና አልፎ አልፎም ከገበያ ዋጋ በላይ እንዲሆን እና በህብረተሰቡ የቅሬታ ምንጭ እንዲፈቱ አልተደረገም፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ 2001/2003 ዓ.ም የተደለደለ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ እንዲሻሻል፣ የሲሚንቶ ኮታ ድልድል ግልፅና በጥናት የተደገፈ ሆኖ እንዲዘጋጅ፣ መሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ከአመት ወደ አመት እየቀነሰ በመምጣቱ፣ ወጥነት የሌለውና በየተራ ለሁሉም ህብረተሰብ ማዳረስ እንዲቻል አልተደረገም፡፡
- ❖ ከ2011/2012 ጀምሮ የመሰረታዊ ሸቀጦች በፍራንኮቫሉታ የሚገቡ ምርቶች 95 በመቶ እንዲሸፍን የታሰበ ቢሆንም በስርጭቱ ያሉ ክፍተቶች እንዲፈቱና ተደራሽ እንዲሆኑ እና የምርቶቹ እጥረትና የዋጋ ግሽበቱ እንዲቀንስ አልተደረገም፡፡
- ❖ ስንዴ ከውጭ እየገባ የገበያ ጉድለት ሲሞላ የቆየ ቢሆንም ከ2012/2013 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ በመሆኑ ምርቱ በግብአትነት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች በራሳቸው መንገድ ማግኘት ባለመቻላቸው ከጥቁር ገበያ በውድ እየገዙ ካለው ፍላጎት አንፃር ከፍተኛ አለመጣጣም ፈጥሯል፡፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን ጥናቶች ቢጠኑም የተጠቃሚው ፍላጎት በእቅድ በመያዝ እና ተከታታይነት ባለው መልኩ በየዓመቱ ጥናት በማድረግ የአምራቾችንና የአቅራቢዎች እቅድ በእቅዱ የሚያካትትበት እና ምርቶቹ ባለቁ ጊዜ እንዲተኩ የሚያደርግበት የአሰራር አልተዘረጋም፡፡
- ድፍድፍ የምግብ ዘይት ይፈቀድ የነበረው የውጭ ምንዛሬ እየቀነሰ በመምጣት ከ2015/2016 ተቋርጠዋል፡፡ የሸቀጦቹ ዝውውር ላይ ከፍተኛ ችግሮች መኖራቸው በተለይ በፍራንኮቫሉታ ምርቶች እና በስንዴ ግብይት፤ ደላሎች፣ ኬላዎችም በየመንገዱ መኖራቸውና በገበያው ላይ ችግር የሚፈጥር መሆኑና ችግሮቹ የሚፈቱበትን ስራ አላከናወነም፡፡
- ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በተሟላ መልኩ የጋራ እቅድ እንዲኖር፣ የጋራ እቅድ እንዲኖራቸው ክልሎች በየ45 ቀኑ በግብረ-ሀይል ኮሚቴው ስብሰባ ጥያቄ የሚያነሱ ቢሆንም ተግባራዊ እንዲሆን እና የግብረ ኃይል ኮሚቴ ውይይቶችና ግምገማዎች እንደሚደረጉ ቢገለፅም ከኑሮ ውድነት እና ከምርቶች አቅርቦት አንፃር የሚፈለገውን ውጤት እንዲመጣ አልተደረገም፡፡
- የስርጭት ማስረጃዎች ከፋብሪካዎቹ እና ከሚመለከታቸው አካላት በተፈለገው ጊዜና ጥራት እየተገኘ እና ፍራንኮቫሎታ ገበያን እንዲያረጋጋ ተብሎ ቢፈቀድም በጥናት ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡
- የሲሚንቶ እና የመሰረታዊ ሸቀጦች ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት ቢኖርም ምርቶቹ ቀጣይነትና ወጥነት ባለው መልኩ በገበያ እንዲገኙ አልተደረገም እንዲሁም ስንዴ ከመሰረታዊ ሸቀጥነት ለማውጣት በሙያዊ ጥናት ሳይጠና ከመሰረታዊ ሸቀጥነት መውጣቱ ይፋ ሳይደረግ ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች የሚቀርበው ምርት ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡
- የመሰረታዊ ሸቀጦችና የሲሚንቶ ሽያጭ የሚፈጽሙ ተዋንያን በምርቶቻቸው ላይ ዋጋ ለጥፈው እንዲሸጡ የሚያስችል ወጥ የሆነ አሰራር እንዲዘረጋ እና ዋጋውም በህዝብ ማስታወቂያ /በሚድያ እንዲታወቅ አልተደረገም፡፡
- መሰረታዊ ሸቀጦች በልዩ ሁኔታ በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረብ እንዲችሉ ከአስፈጻሚ አካላት (ኢንዱስትሪ ሚ/ር፣ ብሄራዊ ባንክ፣ ንግድ ባንክ፣ ገቢዎች ሚ/ር፣ ጉምሩክ ባለስልጣን ወዘተ) የቅንጅት ስራው የተጠናከረ አይደለም፡፡

- የዘይት አምራች ፋብሪካዎች የራሳቸውን ጥሬ እቃ/ግብዓት አምርተው መጠቀም እንዲችሉ እና የፓልም ዘይት ተክሉ በሀገር ውስጥ በመትከል የውጭ ምንዛሬ የሚያስቀርና ምርቱ በበቂ እና በተፈለገው ጊዜ እንዲደርስ ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አልተሰራም እንዲሁም የሲሚንቶ ምርት ህገ-ወጥ ስርጭት ለመቆጣጠር ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ችግሩን የሚፈታበትና የሚቆጣጠርበት ስርዓት አልተዘረጋም፡፡
- የዘይት፣ የስኳር፣ ዱቄትና የዳቦ እንዲሁም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ የውጪ ምንዛሬ፣ ብድር እና ለግብዓትነት የሚውሉ ምርቶችን እንዲያገኙ፣ ፋብሪካዎች በፀጥታ ችግር ምክንያት 24 ሰዓታት ያመርቱ የነበሩ ለ12 ስዓት ብቻ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች ችግሩ ከሚመለከታቸው አካላት በመሆን እንዲፈታ አልተደረገም፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያዝያ 2014 ዓ.ም ባጠናው ጥናት የቅባት እህል ምርት ለሀገር ውስጥ እንዲመረቱና ለምግብ ዘይት ፋብሪካዎች በግብአትነት መጠቀም እንዲችሉ ቢፈቀድ የሀገር ውስጥ ገበያውን ማረጋጋት እንደሚቻል በጥናቱ ቢገለፅም ተግባራዊ አልሆነም፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በወጣላቸው ዋጋ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ በተከታታይና ቀጣይነት ባለው መልኩ ክትትል ባለመደረጉ ከተተመነ ዋጋ በላይ እየተሸጠ ነው እና የሚሸጡበት ዋጋ ሲጠየቁ መረጃ የማይሰጡ ፋብሪካዎች መኖራቸው እና በየስድስት ወሩ የፋብሪካ የሲሚንቶ የዋጋ ለውጥ መደረግ ቢኖርበትም ከአንድ ዓመት በላይ አልተከለሰም፡፡
- የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በተቀመጠው የስርጭት ሰንሰለት ያለመተግበርና ምርቱ ከደላሎች አከፋፋዩችና ቸርቻሪዎች እንደሚረከቡ፣ አከፋፋዮቻቸው ክትትል እያደረጉ አለመሆኑና ምርቱ በፋብሪካው ከተመዘገቡ አከፋፋዮች ውጪ በፋብሪካዎች ባሉ አካላትና በደላሎች አማካይነት ከፋብሪካ ቀጥታ ለቸርቻሪዎች እንዲቀርብ እና ምርቱ ወደ ተጠቃሚው ሲደርስ ከፋብሪካው ዋጋ በእጥፍ ዋጋ ያለደረሰኝ እንዲሸጥና የዋጋ ተመኑ እንዳይተገበር አድርጓል፡፡
- የዘይት ፋብሪካዎች በየሶስት ወሩ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ትመና እየተተገበረ ባለመሆኑ ዘይት ፋብሪካ ዋጋ ግንባታ እስከ አንድ አመት ሳይተመን፣ የዘይት

ምርት አቅርቦቱ በወጥነት በተመሳሳይ ጊዜና መጠን ለአንድ ክልል፣ ዞንና ማህበራት እንዲቀርብ ከምርት አምራቾችና አቅራቢዎች ጋር በመሆን አልተሰራም፡፡

- ❖ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን ዘይት አይነቱን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መጠኑን እና በፓኬጅ መለየትና መወሰን እና የስኳር ምርት ጥራት ችግር ላይ እንዲሳተፉ እና እንዲከታተሉ አልተደረገም፡፡
- ❖ በሲሚንቶ ስርጭት ላይ የሚፈጠሩ የስርጭት መዛባት እርምጃ አለመውሰድና ህግ አልባ ግብይት እየተደረገ እየታወቀ እርምጃ የሚወስድ አካል እንዲኖር፣ በፍራንኮቫሎታ የገቡ ምርቶች የሚያከማቹ እና ከዋጋ በላይ በሚሸጡት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ፣ በተጠኑ ጥናቶች የተገኙ ክፍተቶች ላይ መፍትሄ እንዲሰጥ እና ቁጥጥርና ምርመራ እየተደረገ እንዲሁም እርምጃም እንዲወሰድ አልተደረገም፡፡
- ❖ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ለሚሰሩ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ ከ2013 እስከ 2015/2016 ሩብ ዓመት የትምህርትና የስልጠና መድረኮች እየተሰጠ፣ ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች ጥራትን ለማረጋገጥ የስልጠና እና አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገ አይደለም፡፡
- ❖ መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች /ክልሎች ኮታ ወቅታዊ እየተደረ አይደለም እናም ሲቀርቡም ቀጣይነት የሌለው (ለአንድ ጊዜ ብቻ)፣ በመጠንም አነሰተኛ እንዲሁም ስርጭቱ ላይም ክትትል እየተደረገ አይደለም፡፡
- ❖ የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞች እና እየተዘጋጁ ያሉት ረቂቅ ፖሊሲዎች ሴቶች፣ ወጣቶች እና አካል ጉዳተኞች ስራ እድል ፈጠራን በተመለከተ የሚገለፅ ቢሆንም የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች፤ አረጋውያንን እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችሉ አይደሉም፡፡

104. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሣቦች

105. የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አፈፃፀም ዙሪያ የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦችና የሲሚንቶ የህግ ማእቀፎች ወቅታዊና ሁሉም አካታች በሆነ መልኩ ሊያዘጋጅ፤ የኮታ መመሪያ እና ያለአግባብ ምርቶች በሚያከማቹ አካላት ላይ እርምጃ የሚወሰድበት የህግ ማዕቀፍ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች በተለያዩ አማራጮች ከውጭ እንዲያስገቡ የተፈቀደላቸው የፍራንኮቫሉታ እና የዲያስፖራ አካውንት ያላቸው ባለሃብት አስመጪዎች ፈቃድ ከመስጠት ጀምሮ በየጊዜው አጠናክሮ ተደራሽነቱንና የኑሮ ውድነት/ገበያው ማረጋጋቱን የሚረጋገጥበት ሁሉን አቀፍ የአቅርቦት፣ የስርጭት /የግብይት ሰንሰለት፣ ትክክል ማንነታቸው የሚታወቅበት፣ ምርታቸው በሁሉም አከባቢ ተደራሽ ሊያደረግ የሚችል እና የቁጥጥር ስርዓት ሊዘረጋላቸው እና ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፤
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች እና የሲሚንቶ የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ ስርዓት በተለይ አሁን ካለው ፍላጎት፣ አቅርቦት፣ እጥረት እና የዋጋ ንረቱና የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ከፍተኛ ልዩነት አንፃር ምርቱ፣ አሰራሩና ስርጭቱ እንዲጣጣም በማድረግ ለሁሉም ተደራሽ ሊደረግበት የሚችል እና በጥናት የተለዩ የህገ-ወጥ ግብይት፣ ያለአግባብ ዋጋ መጨመር፣ ምርቶች በማከማቸት እጥረት እንዲፈጠር ማድረግ ወዘተ ግብይቱ/በስርጭቱ ላይ ያሉ ክፍተቶች የሚፈታበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ❖ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ለአከፋፋዮችና ለቸርቻሪዎች በተዘረጋላቸው ሰንሰለት ምርቱ የሚያቀርቡበት እና በፋብሪካዎች ያሉ ከህግ ውጭ ለሚሸጡ አካላት፣ ደላሎች እና ሹፌሮች በህገ-ወጥ ያለደረሰኝ እየሸጡ ያለደረሰኝ እንዲሰራጭ ለሚያደርጉ ከሚመለከተው አካል በመሆን የሚከላከሉበት ሥራዓት ሊዘረጋ

እና ስርጭቱ ግልፅ፣ በተዘረጋው ትስስር በወጣው ዋጋና በወቅቱ ምርቱ ተጠቃሚው የሚያገኝበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡

- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አከፋፋዮች አመራረጥና አመዳደብ ግልፅ፣ ወጥ፣ ቀጣይ እና አሳታፊ እንዲሆን ሊያደርግ የሚችል አሰራር፤ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እና የስኳር ፋብሪካዎች ርቀት ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ የሚመደቡበት አሰራር፤ ቅሬታዎች የሚያስተናግድበት እና የሚፈታበት የአሰራር ስርዓቶች ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የመሰረታዊ ሸቀጦች 2001/2003 ዓ.ም የተደለደለው ኮታ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሊያሻሻል እና ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በተደለደለላቸው ኮታ የምርት አቅርቦት እንዲኖር ሊያደርግ እንዲሁም የሲሚንቶ ኮታ ድልድል በጥናት የተመሰረተ ግልፅ የሆነ ኮታ ሊያዘጋጅና ምርቱ እንዲሰራጭ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን ዙሪያ እየተጠኑ ያሉ ጥናቶች የተጠቃሚው የፍላጎት በእቅድ ሊይዝና ተከታታይነት ባለው መልኩ በየዓመቱ ጥናት በማድረግ የአምራቾችንና የአቅራቢዎች እቅድ በእቅዱ የሚያካትትበት እና የምርቶቹ ክምችት ባለቁ ጊዜ እንዲተኩ የሚያደርግበት የአሰራር ስርዓት ሊዘርጋ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራና የተደራጅ የጋራ የእቅድ ሰነድ ሊኖረው፤ ክልሎች የመሰረታዊ ሸቀጦች ዕቅድ እንዲያቅዱና በራሳቸው የፋይናንስ ምንጭ እንዲያገኙ ሊያበረታታ፤ ወጥነት ያለው ግምገማ ሊያካሂድና የግብረ-መልስ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ❖ የምርቶቹ የስርጭት ማስረጃዎች ከፋብሪካዎቹ፣ ከአስመጪዎቹ እና ከሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ፣ በተፈለገው ጊዜና ጥራት ማስረጃ የሚገኝበት ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ❖ የመሰረታዊ ሸቀጦች ከፍተኛ የገበያ ፍላጎት በመኖሩ ቀጣይነትና ወጥነት ባለው መልኩ በገበያ እንዲገኙ ሊያደርግ፤ ስንዴ ከፍተኛ ፍላጎትና እጥረት በመኖሩ እና የመግዛት አቅም ጋር ከፍተኛ ያለመመጣጠን ሁኔታ በመኖሩ የስንዴ ግብአት የሚጠቀሙ ፋብሪካዎች የተቋረጠው ትስስር በየክልሉ በሃገር ውስጥ ምርት ትስስሩ እንዲቀጥልና ለህብረተሰቡ የስንዴ ውጤት በተመጣጣ

ዋጋ እንዲያቀርቡ ሊደረግ እና እንዲሁም ምርቱ በመሰረታዊ ሸቀጥነት እንዲቀጥል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሙያዊ ጥናት ሊጠናና ሊሚኒስትሮች ም/ቤት ሊያቀርብና እንዲፈቀድ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- ❖ ከ2013 ዓ.ም በፊት ለህብረተሰቡ ምርቱ ሳይቆራረጥና በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረቡ የነበረ የዱቄት እና የስንዴ ግብአት የሚጠቀሙ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ብቻ 311 ፋብሪካዎች እና በየክልሉ በቁጥር ያልተጠቀሱ ፋብሪካዎች የነበረው ትስስር በሃገር ውስጥ ምርት እንዲቀጥል ወይም ፋብሪካዎቹ በግላቸው በተመጣጣኝ ዋጋ ምርቱ የሚያገኙበት መንገድ ሊያመቻች፤ የመሰረታዊ ሸቀጦችና የሲሚንቶ ሽያጭ የሚፈጽሙ ተዋንያን በምርቶቻቸው ላይ ዋጋ ለጥፈው እንዲሸጡ የሚያስችል ወጥ የሆነ አሰራር ሊዘርጋ እና ዋጋዎቻቸው በሚዲያ እንዲታወቅ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦች በልዩ ሁኔታ ጊዜውን ጠብቀው በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ መቅረብ እንዲችሉ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የውጭና የሃገር ውስጥ ተቋማት፣ ከአስፈጻሚ አካላት እና ወዘተ ሊያስተባብርና የቅንጅት ስራው ሊያጠናክር ምርቱ ወደ ሃገር እስኪገባና እስኪሰራጭ ድረስ ሊከታተል፣ ዓለም አቀፍ ገበያ በሚረጋጋበት ወቅት በርከት ያለ ምርት ለማስገባት እንደሃገር ሊታቀድና የውጭ ምንዛሬ እንዲፈቀድ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የምርቶች ስርጭት የተረጋጋ እንዲሆን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በመሆን የዘይት፣ የስኳር፣ ዱቄትና የዳቦ እንዲሁም የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዲያመርቱ የውጪ ምንዛሬ እና ብድር እንድያገኙ ሊያመቻች እና እንደየምርታቸው ለግብዓትነት የሚውሉ የአረምና የማሽኔሪ ኬሚካል፣ ስንዴ፣ ድንጋይ ከሰል፣ የእህል ቅባቶች የፋብሪካዎቹ ማሽነሪዎች፣ ብቁ ባለሞያዎች (የጥገና፣ መለዋወጫ ወዘተ) እንዲያገኙ እና 24 ሰዓታት እንዲያመርቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በወጣላቸው ዋጋ መሰረት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ቀጣይነት ባለው መልኩ ሊከታተል፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በየስድስት ወሩ እና የዘይት ፋብሪካዎች በየሶስት ወሩ የሚወጣው የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ትመና በወቅቱ ሊከለስ፤ ፋብሪካዎቹም የስርጭት ሰንሰለት ሊተገብሩ ምርቱ በየፋብሪካው ለተመዘገቡ አከፋፋዮች እንዲያከፋፍሉ፣ ዋጋ ጣራ እንዲቀመጥ እና እንዲከታተሏቸው ሊቆጣጠር ይገባል፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን ዘይት አይነቱን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መጠኑን እና በፓኬጅ መለየትና መወሰን ላይ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲሳተፉ እና እንዲከታተሉት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የስኳር ምርት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ሊሟሉ የሚገባውን መስፈርቶችን መሟላታቸውን ሊከታተል እና ጥራቱንና ሚዛኑን የጠበቀ መሆኑን በመከታተል እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶ ስርጭት ላይ የሚፈጠሩ የስርጭትና ግብይት ሰንሰለት መዛባትና ህገ-ወጦች ላይ ቁጥጥርና ምርመራ ሊያደርግ፣ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ለሚሰሩ የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ በየወቅቱ የግንዛቤ፣ የትምህርትና የስልጠና መድረኮች ሊያዘጋጅና ሊሰጥ እንዲሁም ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች ጥራትን ለማረጋገጥ የስልጠና እና አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች /ክልሎች ኮታ ወቅታዊ ሊያደርግ፤ ቀጣይነት ያለውና ተመጣጣኝ ምርት ሊያቀርብ እና ስርጭቱ ላይም ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- እንዲሁም እየተዘጋጁ ያሉት ፖሊሲዎች እና የተዘጋጁ ስትራቴጂዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞች፤ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች ፣አረጋውያንን እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ መሆናቸውን ሊያረጋገጥና ሊተገብር ይገባል፡፡

106. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የሲሚንቶና የዘይት ፋብሪካዎች እና አከፋፋዮቻቸው እና ቸሪቻሪዎች፤ የሸማች ማህበራት/ዩኒየኖች፣ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች፣ ዞኖችና ከተሞች፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1፡- የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria)

**የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት**

**የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:- ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር**

**የኦዲት አካባቢ፡- የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም”**

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| 1. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የአሠራር ሥርዓቶች መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣ | 1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን የሚያሳልጡ የህግ ማእቀፎችን (ፖሊሲ፣ ደንብ፣ መመሪያ፣ ወዘተ) ሊያወጣ እና ሊተገብር ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** አዋጅ ቁጥር 1236/2014 አንቀፅ 22(ሀ)፣ | |
| | 1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አስመጪዎች፣ ቸርቻሪዎችን እና የሲሚንቶ አምራቶች የምርት አቅርቦት መነሻ ያደረገ የስርጭት ስርአት ሊዘረጋ እና በየጊዜው አፈጻጸሙን ሊቆጣጠር ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 8፣ የስሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ ቁጥር 940/2015 ገፅ 3 ና 4፣ | |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| | 1.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ አስመጪዎች/ አቅራቢ ድርጅቶች በመመሪያው መሰረት መመረጣቸውን የሚቆጣጠርበት እና ቅሬታዎችን የሚያስተናግድበት ስርዓት በመዘርጋት ሊተገብር ይገባል፡፡<br>ምንጭ የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 8 | |
| | b. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የሲሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች መጠን/ኮታ ሊደለድል እና የፋብሪካዎች፣ የአስመጪዎች፣ እና አቅራቢ ድርጅቶች የሚያከፋፉሉባቸውን አካባቢዎችን ሊወስንና ሊያሳውቅ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 9 የስሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ ቁጥር 940/2015 ገፅ 3 እና 4 | |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ<br><br>(Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች<br>(Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| | c. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦችን በየዓመቱ ፍላጎት እያጠና የአምራቶችንና የአቅራቢዎች በእቅዱ የሚያካትትበት፣ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ስለሚሰራጩበት፣ ስለሚሸጡበትና ከቦታ ወደ ቦታ ስለሚዘዋወሩበት ሁኔታ ሊወስን እና ባለቀ ጊዜ እንዲተኩ ሊያደርግ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋ ሊተገብር ይገባል፡፡<br><br>**<u>ምንጭ</u>፡-** የንግድ ውድድርና ሸማቶች ጥበቃ ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 813 ቁ 27 ንኡስ ቁጥር 7 | |
| 2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ – የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭት፣ ክፍፍል፣ አቅርቦት ለማከናወን ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን መገምገም ፡፡ | 2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመሰረታዊ ሸቀጦች አቅርቦት ስርጭትን ክልሎችን በማሳተፍ መረጃ ሊሰበስብ፣ የጋራ እቅድ ሊያዘጋጅ እና የአፈፃፀሙን ውጤታማነት ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡<br>**<u>ምንጭ</u>፡-** የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 8፣ የአምስት ዓመትና የመካከለኛ ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 17፣18፣ 8 | |
| | 2.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የስሚንቶና የመሰረታዊ ሸቀጦች | |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| | ስርጭትን የግብይት ሥርዓቱ እንዲዳረስ እና እንዲዘምን ሊያደርግ ይገባል፤<br>**ምንጭ፡-** አዋጅ ቁጥር 1236/2014 አንቀፅ 22 (ለ)፣ የአምስት ዓመትና የመካከለኛ ስትራቴጂክ ዕቅድ ገፅ 17፣18፣ 8 | |
| | 2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ እቅዶችንና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን ለግብረ ኃይል ኮሚቴና ለሚመለከታቸው አካላት ሊያቀርብ፣ መደበኛ የጋራ ውይይት፣ የግምገማና ግብረ-መልስ ሊያደረግ እና የሲሚንቶን መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን በቅንጅት ሊሰራና ሳይቆራረጥ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ** ፡-የዋጋ ንረት፣ ሕገ-ወጥና ኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር በፌደራል ደረጃ የተዋቀረው ግብረ ሀይል የ2015 በጀት ዓመት ማስፈፀሚያ ዕቅድ ገፅ 4ና 7፣ የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 8 እና 9፣ የስሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ 940/2015 ገፅ 3 | |
| | **2.4** ሚኒስቴር መ/ቤቱ የገበያ ፍላጎት የዋጋ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ የመሰረታዊ ሸቀጦች እና ስርጭት ሁኔታ ጥናት ሊያጠና እና ጥናቱም | |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| | ለሚኒስትሮች ም/ቤት አቅርቦ ሊያስፈቅድ፤ ዝርዝራቸውንና ዋጋዎቻቸውን በሕዝብ ማስታወቂያ ሊያወጣ እንዲሁም የዋጋ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**<u>ምንጭ፡-</u>** አዋጅ ቁጥር 1236/2014 አንቀፅ 22(ቀ)፣ የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 መወጣ መመሪያ ገፅ.9፤ የስሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ ቁጥር 940/2015 ገፅ.4፣ | |
| | 2.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና የመሰረታዊ /ሸቀጦች አምራች ኣካላት (ተቋማት) በሙሉ አቅማቸው ማምረት እንዲችሉ፤ ችግር የሚፈቱ አማራጮች እና ውጤታማ የገበያ ትስስርና ሰንሰለት እንዲኖር ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** በሚ/ር መ/ቤቱ በስሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ላይ በ2014ና 2015 በጀት ዓመት የተጠኑ ጥናቶች | |
| 3. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲሚንቶ እና መሰረታዊ ሸቀጦችን ስርጭት፣ ክፍፍልና አቅርቦትን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ማደረጉን | 3.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአስመጪዎች /አቅራቢ ድርጅቶች/ የመሰረታዊ ሸቀጦች ጊዜውን ጠብቀው በተመጣጠኝ ዋጋ ምርቱን ለህብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችላቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ከሚመለከታቸው ተቋማት ድጋፍ እንዲያገኙ | |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| መገምገም፡፡ | (የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት፣ ከቀረፅ ነፃ እንዲገቡ ወዘተ) ሊያደርግ፣ ቅንጅታዊ አሠራርን ሊያጠናክርና ሊተገበር፤ አስፈጻሚ አካላትን ሊያስተባበር፣ ከውጭ ከሀገር ውስጥ ግኙኑነት ሊመሰርት እና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡<br><br>ምንጭ፡- የቅዳሚና እሁድ ገበያን በተቀናጀ መልኩ ለመምራት የተዘጋጀ ማኑዋል ቁ…/2014 ገፅ.4 እና የንግድ ውድድርና ሸማቶች ጥበቃ ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 813 ቁ.30 የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ ገፅ 18፣ 19፣ የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 8፣ በመ/ቤቱ በ2015 በስሚንቶና በመሰረታዊ ሸቀጦች ላይ የተጠና ጥናት፤ የአምስት ዓመት መሪ ዕቅድ (2013 - 2017) ገፅ 18 | |
| | 3.2. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በየስድስት ወሩ የፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ ሊወስን፤ ፋብሪካዎችም የጅምላና የችርቻሮዎች የዋጋ ጣሪያ ማውጣታቸው ሊቆጣጠር፤ የዘይት አቅራቢዎች በየሶስት ወሩ የፋብሪካ ዋጋ ሊያሳውቅ፣ አስመጪዎች /አቅራቢ ድርጅቶችና ለቸርቻሪ ነጋዴዎችም የመሸጫ ዋጋና የትርፍ ምጣኔን መወሰኑና የስርጭት እና የመሸጫ ዋጋ አፈፃፀሙን | |


| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| | ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-**የስሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ 940/2015-ገፅ 3 እና 4፣የመሰረታዊ ሸቀጦች የ2008 መመሪያ፣የዘይት አቅርቦትና ስርጭት መመሪያ 020/2011 ገጽ 8፣6፣7 | |
| | የስሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ 940/2015-ገፅ 3 እና 4 የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 8፣ የምግብ ዘይት አቅርቦት እና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ 020/2011 ገጽ 6፣7 | |
| | 3.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፓልም የምግብ ዘይት አስመጪ ድርጅቶች የሚያስመጡትን ዘይት አይነቱን፣ የጥራት ደረጃውን፣ መጠኑን እና በፓኬጅ ሊለይና ሊወስን እንዲሁም አስመጪው ከአንድ ክልል በላይ በአስመጪነት መወዳደር /መመረጥ እንደሌለበት ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ 8ና የምግብ ዘይት አቅርቦትና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ 020/2011 ገጽ 4 | |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) | የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አስተያየት |
|---|---|---|
| | 3.4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ከተቀመጠው የስርጭት ስርዓት ውጭ በሚያከማቹ፣ በሚያጓጉዙ፣ በሚያሰራጩና ከተወሰነው ዋጋ በላይ የሚሸጡ እና መዛባት ሲኖር ፋብሪካዎች፣ አስመጪዎች /አቅራቢ ድርጅቶችና ቸርቻሪዎች ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም ሕጋዊ አሠራር እንዲሰፍን ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ሊወስድ ይገባል፡፡<br><br>**ምንጭ፡-**አዋጅ ቁጥር 1236/2014፣ የመሰረታዊ ሸቀጦች 2008 የወጣ መመሪያ ገፅ.9 የስሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ ቁጥር 908/2014ና 940/2015 ገፅ 3 እና4፣ | |

| | | |
|---|---|---|
| | 3.5 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሲሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ላይ ለሚሰሩ የንግድ፣ ዘርፍ እና የሸማቾች ማህበራት እንዲቋቋሙ የተቋቋሙትንም እንዲጠናከሩ የግንዛቤ፣ የትምህርትና የስልጠና መድረኮችን ሊያደራጅ፣ ሊሰጥ እና ለክልሎችም አስፈላጊውን ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** አዋጅ ቁጥር 1236/2014፣ የንግድ ውድድርና ሸማቶች ጥበቃ ባለስልጣን አዋጅ ቁጥር 813 ቁ 30 ንኡስ ቁጥር 6፣7 8ና 9፣ በመ/ቤቱ በ2015 የተጠና ጥናት | |
| | 3.6 ሚኒስቴር መ/ቤቱ መሰረታዊ ሸቀጦችን በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተጎዱ የህብረተሰብ ክፍሎች ኮታ ወቅታዊ እያደረገ ሊወስን፣ ሊያሰራጭና ሊከታተል ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** የምግብ ዘይት አቅርቦት እና ስርጭት ማስፈጸሚያ መመሪያ 020/2011 ገጽ 6፣ 7 | |
| | 3.7 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያዘጋጃቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞች፤ በስሚንቶና መሰረታዊ ሸቀጦች ስርጭትን የሴቶች፣ የሕፃናት፣ የወጣቶችን፣ አካል ጉዳተኞች ፣አረጋውያንን እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋላጭ | |

| | | |
|---|---|---|
| | የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጠቃሚ እና ሙሉ ተሳታፊ እንደሆኑ የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡-** አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ 19፣ | |

## አባሪ.2 የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ድርጅታዊ መዋቅር



## አባሪ፡-3. የሲሚንቶ ምርት እጥረት መኖሩና ተቋማት ሲጠይቁ የሚሰጣቸው አንሰተኛ መጠን ለማሳያነት፡-

- ✓ ሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ለአምቦ ዩኒቨርሲቲ እያስገነባ ላለው የፌዴራል ሆስፒታል ግንባታ ስራ የሚውል የሲሚንቶ ምርት ለመጋቢት ወር 30,000 ኩንታል በመጋቢት 6/2013 በቁጥር 02.1.22/922 የጠየቀ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ የፈቀደለት 7500 ኩንታል (25 በመቶ) መሆኑ፣
- ✓ የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የደቡብ ክልል ውሃ ስራዎች በክልሉ እያከናወነ ላለው የተለያዩ የመስኖ፣ግድብ እና የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ግንባታ ስራ የሚውል የሲሚንቶ ግብዓት በመጋቢት ወር 385,599 ኩንታል በመጋቢት 03/2013 በቁጥር 02.1.22/963 የጠየቀ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ 100,000 ኩንታል (26 በመቶ) የተፈቀደ መሆኑ፣
- ✓ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ለአያት አክሲዮን ማህበር ለቤት ግንባታ ስራ የሚውል የሲሚንቶ ምርት 660,468 ኩንታል ነሃሴ 20/2014 በቁጥር 01.1.8.11/35383 የጠየቀ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ የፈቀደለት ግን ከአዲስ አበባ ከተማ ኮታ የሚቀነስ 6,6047 ኩንታል (10 በመቶ) መሆኑ፤
- ✓ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት እና በተለያዩ የሀገር ውስጥ ኤርፖርቶች እየሰራቸው ለሚገኘው ፕሮጀክቶች/ግንባታዎችን ለማከናወን የሚውል የሲሚንቶ ምርት 940,000 ኩንታል ነሀሴ17/2014 በቁጥር 01.1.11/35189 የጠየቀ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ እንዲገዛ የፈቀደለት ግን 117,415 ኩንታል (12 በመቶ) መሆኑ፣
- ✓ ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን ተንዳሆ የወጣቶች መስኖ ልማት፣ ሰመራ ዩኒቨርሲቲ የመሰረተ ልማት ዲዛይንና ግንባታ፣ ጊዳቦ ግድብና መስኖ ግንባታ፣ ሚሌ ጋላፊ መንገድ ግንባታ፣ ጂንካ የመንገድ ግንባታ፣ ጊሸን መገንጠያ መንገድ ግንባታ፣ ያቤሎ አየር ማረፊያ ግንባታ እና ሀላባ አንገጫ ዋቶ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ግንባታ ስራዎች የሚውል የሲሚንቶ ምርት

ኦፒሲ 100,000 ኩንታል  ፒፒሲ 100,000 ኩንታል ሲሚንቶ (አጠቃላይ 200 000) ነሀሴ12/2014 በቁጥር 01-1.8.11/35037 የጠየቀ ቢሆንም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከናሽናል ሲሚንቶ ፋብሪካ እንዲገዛ የፈቀደለት ከሁለቱ ዓይነት 20,000 ኩንታል (10 በመቶ) መሆኑ፤

- ✓ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር በአማራ ክልላዊ መንግስት በሚገኘው ከዲ.ኤም.ሲ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስራ ተቋራጭ ጋር ውል በመግባት የደንበጫ-ፈረስ ቤት አዴት፣ኮንትራት-2 የሰቀላ-አዴት የመንገድ ፕሮጀክት ግንባታ ስራዎች የሚውል የሲሚንቶ ምርት ኦፒሲ 12,000 ኩንታል  ፒፒሲ 28,000 ኩንታል ሲሚንቶ ነሀሴ17/ 2014 በቁጥር 01-1.8.11/35207 የጠየቀ ቢሆንም  ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ እንዲገዛ የፈቀደለት 7,650 ኩንታል (27 በመቶ) መሆኑ፣

## አባሪ፡-4 ጥራት የሌለው የስኳር ምርት ለማሳያነት፡-

- ✓ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በጥር 15/2015 በቁጥር ቸነ/2315/10-6 በአስኳር እንዱስትሪ ግሩፕ በቀረበ የጥራት ቅሬታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በፃፈው ደብዳቤ ያሳወቀበት በኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 02 ሃያት ጣፎ ሽርክና ህብረት ስራ ማህበር በ14/03/2015 በፃፈው ደብዳቤ፡-
- ✓ ከስኳር ኢንዱስትሪ ግሩብ ከገዙት ስኳር ውስጥ 113 (አንድ መቶ አስራ ሶስት) ኩንታል የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈበት እና የተበላሸ መሆኑና የሚመለከተው አካል ችግሩ እንዲፈታው አመልክተው የነበረ መሆኑ እና በከተማ አስተዳደሩም የተረጋገጠ መሆኑና የጥራት ኮሚቴ ሪፖርትም አያየዞ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የላከው መሆኑ፤ ነገር ግን በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዋጅ 1263/2014 በተሰጠው ስልጣን የህገር ውስጥ ንግድና ሽማቶች ጥበቃ እና የጥራት ማረጋገጥ መሪ ስራ አስፈፃሚ ባለሙያዎች በ27/6/2015 በተባለው ቦታ ስኳሩ ፈትሸው የተባለው ችግር እንደሌለ የገለፁ መሆኑ፤
- ✓ በደቡብ ክልል በዲላ እና በጋሞ 1363 ኩንታል 90 በመቶ የተበላሸ መሆኑ እና ዩኒዮኑ በ2014 ዓ.ም 3ኛው ዙር 80ኛ ዙር ከመጣለት 121 ኩንታል ተመሳሳይ ችግር የገጠመው መሆኑ እና እንዲቀየርለት የተፃፈለት ደብዳቤም ኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤ በአርባ ምንጭ የተበላሸ ከተባለው 40 ኩንታል በመጋዘን የተገኘው 5 ከረጢት ብቻ መሆኑና ቀሪው ለሕብረተሰቡ የተሰራጨ መሆኑ፤
- ✓ ለሂዶታ ሰበል አምራች ዩኒዮን 60 ኩንታል፣ ለይርጋ ጨፌ ከላይ የተጠቀሰው 1363 ኩንታል በድምሩ 1463 ኩንታል 90 በመቶ የስኳር ጥራት ብልሽት 26/5/2015 በቁጥር ንግልማ/አ. 27/22/165/15 እና 16/6/2015 ብልሽቶቹም ደረቅ የማይፈረካከስ፣ እርጥበት ያለው፣ ባዕድ ነገር የተቀላቀለበት፣ ጥቁር ብናኝ ያለው፣ ማሸግያው ላይም የተመረተበት ቀን፣ የመጠቀሚያ ጊዜው፣ የባች ቁጥር እና የመጠን መለክያ የማይገልፅ መሆኑ እንዲሁም በሶስተኛ ወገን የጠራ መሆኑ እና ደረጃው ታይቶ ፓራሜትሮች ያላሟሉ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑ በ24/3/2015 ያሳወቀ መሆኑ፣
- ✓ በደቡብ ክልል በየካቲት 22/2015 በቁጥር ንግልቢ/2-27/22/132/15 በፃፉት ደብዳቤ የወላይታ ዞን ንግድና ገበያ ጽ/ቤት በ15/5/2015 በቁ.

ወዞንገልመ/1148/20-31 ዳሞት ገበሬዎች ህብረት ስራ ዩኑዮን 80ኛ ዙር 5119 ኩንታል በመንገድ ላይ ሽጦ ለግል ጥቅም የዋለ መሆኑ እና በሌላ ማህበር እንዲቀርብላቸው የጠየቁ መሆኑ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየካቲት 24/2015 ለኮርፖሬሽኑ ደብዳቤያቸው ማሳወቁ፣ የጥራት ደረጃ የ3ኛ ወገን የምርት ጥራት ሰርተፊኬት እንዲይዙ ብቻ ያሳሰባቸው መሆኑ፤

- ✓ በአማራ ክልልም በን/ዘ/መ/100/049/15 በ16/6/2015 ለሚ/ር መ/ቤቱ በፃፉው ደብዳቤ በ1ኛ ዙር ንግድ ሽራች ኮርሬስን ባሕርዳር ቅርንጫፍ በከፊል ለምዕራብ ጎጃም 3174 ኩንታል የቀረበው ስኳር በሙሉ የተበላሸ መሆኑ፤ 2ኛ ዙር በአድማስ ዩኒዮን ከፊንጫ ስኳር ፋብሪካ ከቀረበው ውስጥ 62 ኩንታል የተበላሸ መሆኑ፤ በ3ኛ ዙር ለማዕ/ጎንደር ዞን በፀሃይ ዩኒዮን ከጣና በለስ ስኳር ፋብሪካ ከቀረበው ውስጥ 427 ኩንታል በአጠቃላይ 3663 ኩንታል የተበላሸ መሆኑ አሳውቀው በ3ኛ ወገን በደረጃዎች አጀንሲ ታይቶ 90 በመቶ ያላማላ /የተበላሸ መሆኑ፤